


«የተቸገሩ ወገኖቻችንን መርዳት የሞራል፣ የማሕበራዊና የስብዕና ግዴታችን ነው»

*ደራሲ ጅሬኛ ባይሳ*

8



የማንነት ጥያቄ፣ መንስዔና ውጤት (ከቅድመ ቅኝ አገዛዝ እስከ ዛሬ)

*በባሕሩ ዘውዴ(ፕሮፌሰር)*

6


# አውራምባ ታይም

ለመረጃ ቅርብ

2ኛ ዓመት ቁጥር 88 ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዋጋ 3.50 ብር




*ኃይሉ ሻውል፡-*

# ፖለቲከኛ? «ልማታዊ» ባለሃብት? ወይስ ሁለቱንም?

▶ «የዲያስፖራ ድጋፋቸውን 99 በመቶ አጥተዋል»

የተለያዩ ድረ ገጾች

▶ «እስከዛሬ ለኃይሉ በሰጠሁት ድጋፍ ይቅርታ እጠይቃለሁ»

አምባሳደር እምሩ ዘለቀ

▶ «የቀድሞው ቅንጅት አፍራሽ ማንነት አሁን ታወቀ»

አቶ ነአምን ዘለቀ



# ቴዲ አፍሮ በአውሮፓ

«ኮንሰርቱ እጅግ ደማቅና ስኬታማ ነበር»

አቶ ሙሉጌታ
በጀርመን የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት አዘጋጅ

ልዩ ሪፖርታዥ

*ከኖርዌይ፣ ስዊድን እና ጀርመን ኮንሰርት አዘጋጆች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ይዘናል*

7

## በውስጥ ገፆች

ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያጋጥሙ ፈተናዎችና እድሎች-በኢትዮጵያ

*በተስፋዬ ሀቢሶ (አምባሳደር)*

ብርቱካን በቃሊቲ (ኢ/ር ኃይሉና ጠ/ሚ መለስ በሽራተን!)

«መርህ ይከበር» የሚሉት የአንድነት አባላት 10ኛውን የቃሌ ምሽት አከበሩ

*አንድ «ወንድ!» ብቻውን ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ! «ወንድ!» ተብሎ የተገለፀው ያታውን ለመጠቆም ነው*

*አቤ ቶኪቻው*

የነዳጅ ድጎማው መነሳት /ከእሳቱ ወደ ረመጡ/

*በውብሸት ታዬ*

የአቶ ስዬ አብርሃ እህት አላግባብ ቤት ፈርሶብኛል አሉ

## ኤዲቶሪያል

# ከሶስቱ ፓርቲዎች ጋር ብቻ ተፈራርሞ «ታሪካዊ» ሁነት ተፈፀመ ሊባል ይችላልን?

አገራችን ኢትዮጵያ ተገቢውን እውቅናና ከበሬታ ሊያገኙ የሚገባቸው በርካታ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሃብቶች አሏት:: ልንንከባከባቸው ልናበለጽጋቸውና ለቀጣዩ ትውልድ ልናስረክባቸው ይገባል:: በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ፣ በትምህርትና ጤና ሽፋን፣ በድህነትና ሙስናን በመዋጋት በኩል ደግሞ ተረባርበን ልንደፍነው የሚገባን ትልቅ ክፍተት አለ:: የፖለቲካው ሥነ-ምህዳራዊ ሁኔታም በዚሁ የሰፊ ክፍት ማዕቀፍ ውስጥ ዋንኛውን ድርሻ ከሚይዙት ህፀፆች የመጀመሪያ ተርታ ላይ እናገኘዋለን:: ልንንከባከባቸውና አበልጽገን ለቀጣዩ ትውልድ የምናስተላልፋቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደህዝብ ልንዋጋቸው የሚገቡን ጉዳዮች ምንድናቸው ብለን በጋራ እንጠይቅ::

ተገቢውን እውቅናና ከበሬታ ሊያገኙ ይገባል የምንላቸው አራት ያህል መንፈሳዊና ቁሳዊ ሃብቶች አሉን:: የመጀመሪያው የተፈጥሮ ሃብታችን ነው:: ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአገራችን እስካሁን አገልግሎት ላይ መዋል ያልቻለ ከፍተኛ መጠን ያለው የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ አለ:: መቼ ነው ውጥቶ የሕዝባችንን የሰቆቃ ኑሮ ታሪክ የሚያደርገው? እንዴትስ ነው አገራችንን ፍትሃዊ የኢኮኖሚው ተጠቃሚ ሊያደርጋት በሚችል ውል ወደተግባር መግባት የሚቻለው? ለቀጣዩ ትውልድ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለማስረከብ የዘርፉ ባለሙያዎች አማራጮችን መፈተሽ፣ ስኬታማ የመርሃ ግብር ጥናቶችን ማካሄድ አለባቸው እንላለን::

የተፈጥሮ ሃብት ስንል ተግባር ላይ ውለው ኢኮኖሚውን መደጎም ያልቻሉትን ማለታችን ብቻ አይደለም:: ተፈጥሮ አትረፍርፋ አድላን በአግባቡ ያልተጠቀምንባቸውን፣ ያልተንከባከብናቸውንና በዚህም የተወሰኑት የጥፋት አደጋ ላይ የወደቁተን ጭምር ነው:: በአገራች ብቻ የሚገኙ እጽዋትና እንስሳት እንዲሁም አራዊቶች «ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ» ተብሎ በሚታወቀው የቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ የሃብት ምንጭ በሆኑ ነበር:: በአንዳንድ አገራት ይህ ዘርፍ በመጀመሪያው የምጣኔ ሃብት ምንጭነት ያገለግላል:: -ለዘያውም የእኛን ሩብ ያህል የቱሪዝም መስህብ በሌላቸው ጭምር ማለት ነው:: ያስቆጫል:: አስቆጭቶ ሰፊ ሥራ ለመስራት ሊያነሳሳ ይገባል:: ያለበለዚያ አሁንም ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ይህ መተኪያ የለሽ ሃብት የመጥፋት አደጋ ተደቅኖበታልና ትኩረት ይሰጠው፤ ስንል አበክረን እናሳስባለን::

የውሃ ሃብታችንም ብዙ የተባለለት «ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል» ይሉትን ብሂል ያስተርተብንና ከረሃብ ገመናችን ጀርባ የተንጣለለ እሴት ነው:: በኬሚካል ያልተበከለ ድንግል መሬት፣ ሰው ያልሰፈረባቸውና ለም ገላጣ አካባቢዎች፣ ወዘተ ተገቢውን እውቅናና ከበሬታ ሊሰጣቸው የሚገቡ ሆኖም እንደፉክክር ቤት ሳይዘጉ የሚያድሩ በሮች ሆነዋል:: እንንቃ፣ እንትጋ እንረባረብ ጥሪያችን ነው::

መንፈሳዊ ሃብቶቻችንን ባህላዊና ታሪካዊ ብለን መመልከት እንችላለን:: በዚህ በኩል ኢትዮጵያ እንደሌሎች አፍሪካዊ ጎረቤቶቿ በቅኝ ግዛት ስር ባለመውደቋ የቀደምት ሥልጣኔ አሻራዋን፣ የባህልና የታሪክ መዋቅሮቿን እንዲሁም ለአፍሪካ መዲናነት ያበቋትን መንፈሳዊ እሴቶች በአበውና እመው ተጋድሎ ለመታደግ ችላለች:: የተረከብናት ኢትዮጵያ በክበረ ስብዕና የተዋቀረች፣ ልጆቿ ተፈጥሯዊ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በስምምነት የሚኖሩባት እንዲሁም አዎንታን በሚገነቡ ጥብቅ የእምነት መሠረቶች የታነፀች ናት::

ለቀጣዩ ትውልድ ተንከባክበንና አበልጽገን ልናስተላልፈው ይገባል የምንለውም ቁሳዊ አሩትን ብቻ ሳይሆን ክቡር የሆነውን መንፈሳዊ እሴት ጭምር ነው:: አንዱን ከሌላው መለየት አንችልም:: ልንለየውም አይገባም:: ልንዋጋቸውና ይበቃል! ልንላቸው የሚገቡን እንደወረርሽኝ እየተስፋፉ የመጡ ችግሮችስ ምንድናቸው? አሁንም በጋራ እንጠይቅ::

ችግሮቹ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሃብቶቻችንን በአግባቡ እንዳንገለገልባቸው፣ እንዳናበለጽጋቸውና ትውልዳዊ ሃላፊነታችንን እንዳንወጣ በመንገዳችን ላይ የተጋረጡ ደንቃራዎች ናቸው:: እንዴትና በእነማን እየተፈፀሙ ነው? እንዴት ነው የምንዋጋቸው?

በዜጎች ላይ እየተፈፀመ ካለ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተወሰኑትን ብቻ እንመልከት ብለን እንደሆነ ከአበውና እመው የተረከብነው የክበረ የስብዕና መገለጫ እየተሸረሸረ አንድ ቦታ ላይ «ይበቃል!» ካልተባለም የውድቀት አደጋ ውስጥ መሆኑን በግልጽ እንገነዘባለን::

ሰብዓዊ መብቶች አንድ ሰው በሰብዓዊነቱ ብቻ የተጎናፀፋቸው የማይደፈሩና የማይገሰሱ መብቶች ሲሆኑ በህይወት የመኖር፣ የአካላዊ ደህንነት መጠበቅና የነፃነት መብቶችን ያጠቃልላል:: የእነዚህ ሰብዓዊ መብቶች መከበር በሕገመንግስቱ ላይ የተደነገገ ሲሆን ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌም ይህንኑ ያጠናክራል:: ማንኛ ውም ሰብዓዊ ፍጡር በህይወት የመኖር መብት አለው፣ የነፃነት መብት አለው፣ ከግርፋት፣ ከድህነትና ከአሰቃቂ ጉዳቶች፣ ከማንኛውም ኢ-ሰብዓዊ ቅጣቶች የመጠበቅ መብት አለው ይላሉ:: የሰብዓዊ መብት አጠቃቀም ምን ይመስላል::

ከጥቂት ቀናት በፊት ከተለያዩ ክልሎች የመጡ «የአንድነት» ፓርቲ አባላት በፖለቲካ አቋማችን የተነሳ ጥቃት ተፈጽሞብናል ሲሉ መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳል:: አንዲት ወጣት ደግሞ የአስገድዶ መደፈር ጥቃት እንደተፈፀመባት

ተገልጿል። ሌሎች ፓርቲዎችም በተለያዩ ጊዜያት ተመሳሳይ መግለጫዎችን ሰጥተዋል። ሕገመንግስታችንን ጨምሮ ዓለም አቀፍ የባህልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን፣ ሰዎች በአገራቸው ጉዳይ ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለጽ፣ በማናቸውም ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ መብትና የመሳሰሉትን ያጎናጽፋሉ።

ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት የመብት ጥሰት ሲፈፀም በገዢው ፓርቲ መታየት ያለበት «ተቃዋሚዎች ስለሆኑ ነው፣ ልማዳቸው ነው? የፈጠራ ክስ ነው፣...» በሚል ሳይሆን የተፈፀመውን በደል በመቀበል ፍትሃዊ እርምጃ በመውሰድና ሕግን በማስፈፀም ሚዛን ብቻ ነው። በዓለም ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከሚፈፀምባቸው አስር ከፍተኛ አገራት አንዷ ኢትዮጵያ ናት የሚለው መግለጫ ገጽታን በማበላሸት ዘርፍ ብዙ ጥቅሞችን እያሳጣን እንዳለ ማስታወስ ይገባል እንላለን። ገጽታ የሚገነባው ደግሞ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን የገዢውን ፓርቲ ተግባራት በማወደስ፣ ስለየትኛው አገር እየተነገረ እንዳለ ውዥንብር ውስጥ የሚከት ዘገባ በማቅረብና በተስፈኝነት ሳይሆን አቅም በፈቀደ መጠን አሉታዊ ጉኖችን ለመቅረፈ በመትጋት ነው።

የሥነ-ምግባር ዝቅጠትም ስር እየሰደደ ነው። ከላይ የተመለከትነው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል አፈር ከእህል ባልለዩ ህፃናት ላይ ጭምር እየተፈፀመ ነው። የሞራል ሚዛን ዋዥቋል። አልባሌ ተግባራት ማህበረሰቡን እየገዘገዙ ነው። ለሞራል ሕጎች ትኩረት ይሰጥ።

መንፈሳዊና ቁሳዊ ሃብቶቻችንን በአግባቡ እንዳንገለገልባቸው፣ እንዳናበለጽጋቸውና ለትውልድ እንዳናስተላልፍቸው የሚያደርጉን ችግሮች በሙሉ ገዢው ፓርቲ ያመጣብን ጣጣ ነው ማለት አይደለም። እንደገዢ ፓርቲነት የኃላፊነቱን ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፤ ጉዳዮቹ ሕግ ከማውጣት፣ ከመተርጎምና ከአስፈፃሚነት ሚና ጋር የቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ናቸው ለማለት ነው። ለአገራዊ ቀውሶች በዋነኛ መንስኤነት የሚጠቀሱት ብልሹ አስተዳደር፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሰራርና ግብታዊነት የተላበሱ ደንብና መመርያዎች ናቸው። እውነቱ ይህ ነው መፍትሔውም እውነታውን መቀየር ብቻ ይሆናል።

ስለዴሞክራሲ ግንባታ፣ ስለሰብዓዊ መብት አጠባበቅና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች ስናነሳ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሚና አይነተኛ ግብዓት መሆኑን በመቀበል ነው። በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በአገራችን ከ90 በላይ ፓርቲዎች በሕጋዊነት ተመዝግበው ይንቀሳቀሳሉ። የተሳትፏቸውን መጠንና አቅም ለጊዜው ትተን ከገዢው ፓርቲ ጋር በሚደረጉ ውይይቶችና ድርድሮች ላይ ያላቸው ሚና ወደጎን የተደረገ የሚያስመስል እርምጃ በቅርቡ ተፈጽሟል። ይህም ከሶስት ፓርቲዎች ጋር ብቻ በመደራደር የተፈረመው የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ ነው። የየፓርቲዎቹን የህዝባዊ ተቀባይነት ነገር ለህዝብ ፍርድ እንተወውና 93 ፓርቲዎች አሉ በሚባልበት አገር ከሶስት ፓርቲዎች ጋር ብቻ ተደራድሮ «ታሪካዊ» ሁነት ተፈፀመ ማለት ሥነ-አመክንዮውን፣ የመርህ

እሳቤውም ግልጽ አይሆንም:: ከተደራዳሪዎቹ ፓርቲዎች የአንዱ መሪ የሆኑት ግለሰብ ገዢውን ፓርቲ «ሰጥቶ ለመቀበል ስስታም ያልሆነበት» ሲሉ ያወደሱት ድርድሩን ለማቋረጥ የተገደዱት ፓርቲዎች «መሠረታዊ ነጥቦች» በማለት ያቀረቧቸው የመደራደሪያ ሃሳቦች በተጣሉበትና ተደራዳሪዎቹም እንደወጡ በቀሩበት ሁኔታ መሆኑ ጥያቄዎችን ይፈጥራል::

ጥያቄዎቹ ሰጥቶ መቀበል ያለስስት የነበረበት ድርድር ጠቃሚና ማንንም ሊጎዱ የማይችሉ ሃሳቦች ቀርበውበት እንዴት ተቀባይነት አጣ? ግለሰቡ ውዳሴውን ያጎረፉለት ገዢው ፓርቲ ከ93 ፓርቲዎች ውስጥ ከሶስቱ ጋር ብቻ ያደረገው ገዥ ስምምነት የዴሞክራሲ መገለጫ ከሆነው የአብላጫ ድምጽ መርህ አንፃር እንዴት ይታያል? የሚሉትና የመሳሰሉትን አለን ለሚሉት ደጋፊያቸውና አባላቸው ግልጽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: «የኡኡታ ፖለቲካ ማካሄድ ፋይዳ የለውም::» የሚለው አገላለጽም የግለሰቦችና ፓርቲዎች አቋም የተከበረ የመሆኑን መሠረት እንደጠበቀ ሆኖ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ይሆናል:: ከጊዜ መቀያየር ጋር አቋምን ማስተካከል ምክንያታዊ ቢባልም ዴሞክራሲውን እንዲገነባ ከተፈለገ ተስተካክለዋል በሚባሉ አቋሞች ላይ ወቅታዊ ማብራሪያዎችን መስጠት ተገቢ ይሆናል እንላለን:: በመጨረሻ ልንገነባቸው በሚገቡን መንፈሳዊና ቁሳዊ እሴቶቻችንን በመሉ ልብ የምንረባረበውን ያህል አሉታዊ መገለጫዎቻችንንም እንነሳባቸው የሚል መልዕክታችንን እናስተላልፋለን::

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

## Verbatim

**«ሰነዱ ሕግ ሆኖ ይፀድቃል:: ኢሕአዴግ ደግሞ ፓርላማ ወስዶ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ከፈለገ እነዛንም አብረው ያሉትንም እኮ አይፈልግም::»**

ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ

*የመድረክ ም/ሊቀ መንበር እና የድርጅት ጉዳዮች ኃላፊ*

*አራት የፖለቲካ ፓርቲዎች በመጭው ምርጫ የሚያገለግላቸው የምርጫ ሥነ ምግባር ሰነድ ላይ ተስማምተዋል:: መድረከ ከድርድሩ ራሱን ስላገለለ የለበትም:: በሰነዱ ለመገዛት ትገደዳላችሁ? ተብሎ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ከሪፖርተር ጋዜጣ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ::*

«የኢሕአዴግ መንግስት አሁን አገርን በራሱ ስሜት እየመራ ነው። ይህ ደግሞ አገርን እየጐዳ እንጂ እየጠቀመ አይደለም። ከዴሞክራሲ አንፃር ህዝቡ መብቱ እየተከበረ አይደለም። ከምርጫ አንፃር ህዝቡ ነፃና ግልጽ ምርጫ እያካሄደ አይደለም፣ ከፕሬስ አንፃር የፕሬስ ነፃነት የለም።»

ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ
የአረና ትግራይ አመራር አባል

«ፖለቲካና ሴቶች፣ ሴቶችና ህውሓት» በሚል ርዕስ ነጋድራስ ጋዜጣ ላይ ካሰፈሩት ጽሁፍ የተወሰደ።

«እንግዲህ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ያስቀየምኳቸው ሰዎች ካሉ አሁን በእግዚአብሔር እጅ ተይዣለሁና ይቅር ብለው የቻሉትን ሁሉ በማድረግ በህይወት የመኖር ተስፋዬን እንዲያለመልሙልኝ ነው የምጠይቀው።»

ድምፃዊት ማናልሞሽ ዲቦ

ለአገራችን ህዝብ ምን መናገር ትፈልጊያለሽ? ተብሎ ከዕንቁ መጽሔት ለቀረበላት ጥያቄ በህመም ላይ የምትገኘው ድምፃዊት ማናልሞሽ ዲቦ የሰጠችው ምላሽ።

## ዜናዎች

# ቴዲ አፍሮ በአውሮፓ

## «ኮንሰርቱ እጅግ ደማቅና ስኬታማ ነበር»

## አቶ ሙሉጌታ

### በጀርመን የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት አዘጋጅ

ጥቅምት 1 ቀን 2002 ዓ.ም በልመና የሚተዳደሩ ወገኖችን መልሶ የማቋቋም አላማ ያለው የሙዚቃ ኮንሰርት በአዲስ አበባ ስታዲየም በማቅረብ ስኬታማ ውጤት ያገኘው እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ከአገር ውጭም በአድናቂዎቹ

ውዳሴ ታጅቦ ሥራዎቹን በማቅረብ ላይ ይገኛል። የአዲስ አበባው ኮንሰርት ከፍተኛ ወጪ ተደርጎበት ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ከተሰበሰበበት በኋላ ያለህጋዊ የመቅረጽ ውል በኤሌክትሮኒክስ ሜዲያው ተለቀቀ በሚል ጉዳዩ ወደህግ እንደሚያመራ ተገልጾ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ድምፃዊውን በመጥቀስ የቀረቡ ዘገባዎች እንደጠቆሙት በቪሲዲና ዲቪዲ የተቀረፁት ሥራዎች 50 በመቶ ሽያጭ ለተቸገሩ ወገኖች እንዲውል ስምምነቶች ተፈጽመዋል። ያልተጠበቁ ውዝግቦች መንፀባረቅ የጀመሩት ግን አዲስ አበባ ላይ ብቻ አልነበረም።

ባለፈው ሳምንት እትማችን በአውሮፓ የተለያዩ ከተሞች ሊያቀርብ ያሰበውን ኮንሰርት ተከትሎ በስዊድን፣ በኖርዌይ፣ በሆላንድና በጀርመን የሚገኙ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የኮንሰርቱን አዘጋጆች «ለገዢው ፓርቲ ቅርበት አላቸው» በሚል በአገራቱ ያሉ ኢትዮጵያውያን በኮንሰርቱ እንዳይገኙ በመቀስቀስ ላይ መሆናቸውን ማስነበባችን ይታወሳል። በዘገባው ላይ የተቃውሞ ሃሳቡ ከሚያራምዱት ወገኖች በተለየ ድምፃዊው የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሃብት በመሆኑ በአዘጋጆች ግላዊ የፖለቲካ አቋም የተነሳ ለምን የውዝግብ ርዕስ ይሆናል? የሚሉ ወገኖችንም አስተያየት ያካተትን ቢሆንም አውራምባ ታይምስን በድረ ገጽ አማካኝነት በየሳምንቱ የሚያነቡ በመላው አለም የሚገኙ አንባቢዎቻችን ከፈረንሳይ፣ ከለንደን፣ ከጀርመን፣ ከስዊድንና ከሌሎች አገራት የተለያዩ አስተያየቶች አደርሰውናል። በአገር ውስጥ ያሉ የጋዜጣችን አንባቢያንም በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች የሚገኙ የኮንሰርቱ አዘጋጆችን አነጋግረን ምላሻቸውን እንድናስነብባቸው በጠየቁን መሠረት በኖርዌይ በስዊድንና በጀርመን የሚገኙ አዘጋጆችን በስልክ አጠር ያለ ቃለ ምልልስ አድርገንላቸዋል። እንደሚከተለውም አቅርበነዋል።

**«በአክራሪ ጽንፈኞች የተጀመረ ቅስቀሳ ነው»**

**አቶ ደስታ ገ/ስላሴን**

**በኖርዌይ ኦስሎ የቴዲ ኮንሰርት አዘጋጅ**

**በመጀመሪያ ያነጋገርናቸው ሕዳር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በኖርዌይ ኦስሎ ለሚቀርበው ኮንሰርት ከድምፃዊው ጋር የስምምነት ውል የፈፀሙትን አቶ ደስታ ገ/ስላሴን ነው። አቶ ደስታ ለቃለ ምልልሱ ቀና ትብብር በማድረጋቸው እያመሰገንን የጥያቄያችን መንደርደሪያ ያደረግነው ቴዲ ኮንሰርቱን በኖርዌይ ለማድረግ በመወሰኑ በዚያ በሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት ምን ተሰማቸው? በሚል ነበር።**

<u>አቶ ደስታ:-</u> በጣም ነው የተደሰቱት። እንደምታውቁት የሙዚቃው አፍቃሪዎች አርቲስቱን ናፍቀውት ቆይተዋል። አገር ቤት ባደረገው ኮንሰርት ላይ በችግር ላይ ላሉ

ወገኖች ያሳየው አጋርነትም እንዲሁ የብዙዎችን ልብ የነካና ለበጎ ተግባር ያነሳሳ በመሆኑ ኮንሰርቱ የበለጠ በጉጉት እንዲጠበቅ አድርጎታል።

**ባለፈው ሳምንት ባቀረብነው ዘገባ ላይ በአውሮፓ የሚደረገውን ኮንሰርት የሚቃወሙ ወገኖች እናንተን «ለገዢው ፓርቲ ቅርበት ያላቸው» በሚል ኢትዮጵያውያን በኮንሰርቱ እንዳይገኙ ጽሁፎችን በድረ ገጾች ላይ በማውጣት እየቀሰቀሱ መሆናቸውን ገልፀናል። በዚህ ላይ የእርስዎ ምላሽ ምንድነው?**

እንደ እውነቱ ከሆነ የሰራችሁትን ዘገባ አንብቤ ቅር ተሰኝቻለሁ። ወደ ነጥቡ ስንመጣ ግን ሁለት ነገሮች ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው እኔ የቢዝነስ ሰው ነኝ። መሰል ኮንሰርቶችንና ሌሎች የቢዝነስ ሥራዎችን ስሰራ ቆይቻለሁ። የፖለቲካ አቋምን በተመለከተ ግን የማንኛውም ፓርቲ አባል ወይ ደጋፊ አይደለሁም። በሌላ አገላለጽ አሁንም የማንኛውም ፓርቲ ተቃዋሚም አይደለሁም። ሁላችሁም እንደምታውቁት የቢዝነስ ሥራዎች በየትኛውም አገር ሲካሄዱ ሥራዎቹ የሚሰሩት ከየአገራቱ መንግስታት ጋር ነው። በዚህ መርህ መሰረት እኛም ከመንግስት ጋር በህጉ መሰረት የምንሰራቸው ሥራዎች ይኖራሉ። ኮንሰርቱን አስመልክቶ ግን ውሉን የሚሰጠው አካል ዝግጅቱን በብቃት ያስፈጽምልኛል ለሚላቸው ወገኖች እንደሆነ ይታወቃል። እና አሁን የሆነውም ይኸው ነው።

**እንግዲህ አሁን የሆነው በዚህ መልኩ ከሆነ ተቃውሞው ከምን የመነጨ ይመስለታል?**

በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች የሚፈጽሙት ተግባር ነው። እንደምታስታውሱት አርቲስቱ ከእስር ሲወጣ የፖሊሶቹ አያያዝ ጥሩ እንደነበር ገልጿል። ይህ ያጋጠመውን በሃቀኝነት ለህዝቡ የገለፀበት መንገድ ነው። ለምን መልካም ነገር ተጠቀሰ በሚል በአክራሪ ጽንፈኞች የተጀመረ ቅስቀሳ ነው። የሚገርመው ግን ህዝቡ አካሄዳቸውን አምርሮ ነው የተቃወመው። እኛንም የካሰን ይህ የህዝቡ አቋም ነው።

**ቀደም ሲል ከአርቲስቱ ወይም ከማናጀሮቹ ጋር ያላችሁ ትውውቅ ምን ይመስላል?**
ከአርቲስት ቴዲ አፍሮም ከማናጀሩ አዲስ ገሰሰም ጋር በቅርበት እንተዋወቃለን። ይህም ጭምር ነው ኃላፊነቱን እንድወስድ ያደረገኝ።

**አቶ ደስታ በኖርዌይ ያለው የኢትዮጵያውያን ብዛት ይታወቃል? ለመሆኑ እስካሁን የኮንሰርቱን ትኬት የገዙት ታዳሚዎችስ?**

በትክክል ምን ያህል ኢትዮጵያውያን እዳሉ ለጊዜው አላውቅም:: ለኮንሰርቱ እስካሁን ትኬት መሸጥ ባንጀምርም ያለው ተነሳሽነት በጣም ከፍተኛ ነው:: ከኖርዌይ ብቻ ሳይሆን ከአጎራባች አገራት ጭምር በርካታ መልዕክቶች እየደረሱን ነው::

**«ገለልተኛ የፖለቲካ አቋም እንዳለኝ እዚህ ያለ 95 በመቶ ኢትዮጵያ ያውቃል::»**

***አቶ ስሜነህ ዋቄ (ኩኩሻ)***
***በስዊድን የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት አዘጋጅ***

**ባለፈው ሳምንት ከቴዲ ኮንሰርቱ ዝግጅት ጋር በተያያዘ የእናንተ ፖለቲካዊ አቋም ከገዢው ፓርቲ ጋር ተያይዞ የተነሳበት አጋጣሚ ነበር ከእነዚሁ መረጃዎች ጋር በተያያዘ ምን የሚሰጡት አስተያየት ይኖራል?**

ስሜነህ ዋቄ (ኩኩሻ) እውነት ለመናገር ይህ ከእውነት የራቀ ነው:: እናንተም ባለፈው ሳምንት ዘገባውን ለአንባቢ ከማቅረባችሁ በፊት ቢያንስ የእኛን አስተያየት ማካተት ነበረባችሁ:: ያም ሆነ ይህ ይህን ያደረጉት ወገኖች ግብታዊ አመለካከት ተገቢ አይደለም:: በአጠቃላይ መግለጽ የምፈልገው ነገር ቢኖር በስዊድን የሚኖረው 95 በመቶ ኢትዮጵያ በፖለቲካ አቋሜ ገለልተኛ መሆኔን ያውቃል::

**በስዊድን ዝግጅቱ ምን ይመስላል?**

በጣም በተሳካ ሁኔታ እየተካሄደ ነው:: በዘርፉ ያሉ አጋሮቻችንም ዝግጅቱ የደመቀ እንዲሆን በርብርብ ላይ ናቸው::

**ኃላፊነቱን እንዲወስድ የተለየ ድጋፍ ያደረጉልዎ ወገኖች አሉ?**

የመጀመሪያው ዝግጅቱን ለማስኬድ ያለን ልምድና አቅም ነው:: ከዚያ በተጨማሪ ግን የተለያዩ ወዳጆቼ ያደረጉት ድጋፍ አለ:: ጋሽ መሐሙድ አህመድ (የትዝታው ንጉስ) የምወደውና «ጠንካራ ልጄ ነህ» በሚል ያደረገልኝ ድጋፍም አለ::

**ምን ያህል የቅስቀሳ ስራ ሰርታችኋል? ምን ያህል ታዳሚስ ይገኛል ብላችሁ ትጠብቃላችሁ**

እየሰራን ነው:: ፖስተሮች ተበትነዋል:: በተለያዩ ድረ ገጾች እያስተዋወቅን ነው:: የኢትዮጵያ ድምጽ ራዲዮም ሽፋን ሰጥቶታል:: በስዊድን ስቶክሆልም በሚካሄደው ኮንሰርት ላይ ከአንድ ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል::

**«ኮንሰርቱ እጅግ ደማቅና ስኬታማ ነበር»**

**አቶ ሙሉጌታ**

**በጀርመን የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት አዘጋጅ**

ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም በጀርመን የተካሄደው ኮንሰርት አዘጋጅ የሆኑት አቶ ሙሉጌታም ከዝግጅቱ በኋላ አነጋግረናቸዋል::

**ኮንሰርቱ ምን ይመስላል? ምን ያህል ታዳሚዎች ተገኙ?**

<u>አቶ ሙሉጌታ</u> ታላቅ ኮንሰርት ነበር:: ከጀርመን ብቻ ሳይሆን አጎራባች ከሆኑት ከፈረንሳይ፣ ከኦስትሪያ፣ ከስዊድንና ከሆላንድ የመጡ ነበሩ:: ቁጥራቸውም ከ1300 በላይ ይሆናል::

**በኮንሰርቱ ላይ የነበረው የታዳሚ ስሜት እንዴት ይገልፁታል?**

ቴዲን በጣም በጉጉት ነበር ይጠባበቁት የነበረው:: እሱም በጣም ተጫውቷል:: ኮንሰርቱ እጅግ ደማቅና ስኬታማ ነበር::

# «መርህ ይከበር» የሚሉት የአንድነት አባላት 10ኛውን የቃሌ ምሽት አከበሩ

*ናፍቆት ዮሴፍ*

ባለፈው አርብ ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም «መርህ ይከበር» የሚለው ወገን 10ኛውን የቃሌ ምሽት በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት በር ላይ አክብሯል:: በእለቱ በኢምፔሪያል ሆቴል

ፓርቲው ባዘጋጀው በዚህ የቃሌ ምሽት ላይ ለመታደም የሄዱትን ሰዎች «የጥሪ ወረቀት አልያዛችሁም» በሚል እንደመለሷቸው እና ጽ/ቤት ውስጥ የሻማ ማብራት ስነ ስርዓቱን ለማከናወን ቢሞክሩም በመከልከላቸው በጽ/ቤቱ በር ላይ ማካሄዳቸውን ለአውራምባ ታይምስ ገልጸዋል::

በጽ/ቤቱ በር ላይ የተካሄደው የቃሌ ምሽት ድንገት በተዘጋጀ ፕሮግራም የተካሄደ እና በፀሎት የተጀመረ ሲሆን ፕ/ር መስፍን ወ/ማራያም የሚከተለውን ፀሎት አሰምተዋል:: «እግዚያብሔር አምላካችን ሆይ፣ በየወሩ የምናስባትን እህታችንን፣ አለቃችንን እኛ እንደምናስባት አንተም አስብልን:: የአሳሪዎቿን ልብ አራርተህመንፈሳቸውን እንድትወጣልን አድርግልን:: እኛም ለእርሷ በትጋት እንድንቆም ጽናትን፣ ብቃትንና መንፈሳዊነትን ስጠን»

በእለቱ የተካሄደውን ፕሮግራም ከፀሎት በኋላ በንግግር የከፈቱት አቶ ወንድሙ የቀድሞውን የኢትዮጵያ ንጉስ አባባል «ሁላችሁም አንድ ከሆናችሁ እንኳን ጠላት ነፋስ አይገባባችሁም» የሚለውን በማስቀደም ለነፃነት ለአንድነተና ለዴሞክራሲ መቆም ከፍተኛ መስዋዕትነት እንደሚጠይቅና ለዚህም መፍትሄው ጽናት እንደሆነ በአጽንኦት ተናግረዋል በመቀጠልም መጣጥፎች ግጥሞችና የጧፍ ማብራት ስነ ስርዓት ተካሂዶ ፕሮግራሙ ተቋጭቷል::

## «እኔና ኢ/ር ኃይሉ በአካል ተገናኝተን ለመነጋገር ባልቻልንበት ወቅት ሌሎች ተደራዳሪዎች የላቀ ውጤት በማምጣታቸው አመሰግናቸዋለሁ::

**ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ**

## «አንዳንዴ ስናፈነግጥ እየኮረኮሙ ለዚህ ስምምነት ያደረሱንን ወዳጅ አምባሳደሮች እጅግ አመሰግናለሁ»

## *ኢ/ር ኃይሉ ሻውል*

***ናፍቆት ዮሴፍ***

ባለፈው ሣምንት ሰፊ ትኩረት ከተሰጣቸው ፖለቲካዊና አገራዊ አጀንዳዎች መካከል ግንባር ቀደም የሆነው የአራቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብ

ስምምነት ላይ መድረስ ነው፡፡ ይሄው ከሁለት ወር በላይ ድርድር የተደረገበት የስነ ምግባር ደንብ ባፈው አርብ በሸራተን አዲስ ሆቴል በአራቱ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተፈርሟል፡፡ ኢህአዴግ፣ ኢዴፓ፣ ቅንጅትና መኢአድ ከሁለት ወር የድርድር ጊዜ በኋላ ስምምነት ላይ ደርሰው የፓርቲዎቹ አመራሮች ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ፣ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል፣ አቶ ልደቱ አያሌውና አቶ አየለ ጫሚሶ ተፈራርመውበታል፡፡ ከያዝነው ሳምንት ጀምሮ ትግበራው እንደሚጀምርም ይፋ ሆኗል፡፡

የእለቱን የፊርማ ስነ ስርዓት በንግግር የከፈቱት በሚ/ር ማዕረግ በፓርላማ የመንግስት ዋና ተጠሪ የሆኑት አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ስምምነቱን ወሳኝ ያሉት ሲሆን መድረክን አስመልክተው «በተሳሳተ አቋም ምክንያት በግል ካልተደራደርኩ በማለት የዚህ ድርድር አካል ሳይሆን ቀርቷል» ብለዋል፡፡ «ሰው በግል የሚደራደረው ለግል ጉዳይ እንጂ ለአገራዊ ጉዳይ በግል የሚባል ነገር የለም» ሲሉም አክለዋል፡፡ በእለቱ በሸራተን አዲስ ላሊበላ አዳራሽ በር ላይ የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ጋዜጠኞችና የየፓርቲዎች ከፍተኛ የአመራር አባላት ቀደም ብለው በመገኘት ሁኔታውን በንቃት ይከታተሉ ነበር፡፡ በመጀመሪያ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ አየለ ጫሚሶ በመቀጠል የኢዴፓ ሊቀመንበር አቶ ልደቱ አያሌው ከጥቂት ቆይታ በኋላ ደግሞ የመኢአድ ሊቀመንበር ኢ/ር ኃይሉ ሻውል ወደሥፍራው ከደረሱ በኋላ ከየድርጅታቸው ስማቸው የተላለፈ ጋዜጠኞችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ወደ አዳራሹ ገብተው ቦታ ቦታቸውን ያዙ፡፡ ይህ ከሆነ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ጠ/ሚንስትር መለስ እስኪመጡ ረዘም ላሉ ደቂቃዎች መጠበቅ ግድ ሆነ፡፡ ጠ/ሚሩ ገብተው ከሶስቱ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ጋር ተቀላቀሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ነው አቶ ሀ/ማርያም ደሳለኝ ስነ-ስርዐቱን በመግቢያችን በጠቀስነው መሠረት በንግግር የከፈቱት፡፡

ከነሀሴ 2001 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ለውይይት የቀረበው የፓርቲዎች የስነ-ምግባር ደንብና የማስፈፀሚያ መመሪያው ከብዙ ውይይቶችና ድርድሮች በኋላ ጥቅምት 17-2002 ሰነዶቹ በተባበረ ድምጽ መጽደቃቸው በመክፈቻ ንግግሩ ከተነገረ በኋላ ቀጥታ ወደ መፈራረም ስነስርዓቱ ተገባ፡፡ ከፊርማ ሥነ ስርዓቱ በኋላ ኢ/ር ሀይሉ ሻውልና ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ ሲጨባበጡ አዳራሹ በጭብጨባ ደመቀ ቀጥሎ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችም እርስ በእርሳቸው ተጨባብጠዋል፡፡

ከዚህ ሥነ-ስርዓት በኋላም አራቱም የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተራ በተራ እንዲናገሩ እድል የተሰጣቸው ሲሆን የመጀመያ ተናጋሪ እንዲሆኑ እድል የተሰጣቸው የቅንጅቱ መሪ አቶ አየለ ጫሚሶ ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ለመናገር እድል የተሰጣቸው አቶ ልደቱ «ይህ ስምምነት ሳይደረግ በፊትም ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የአገሪቱን 70 በመቶ ሸፍነን በምርጫው ለመሳተፍ እና ለመወዳደር በዝግጅት ላይ ነበርን፡፡ ይህ ስምምነት ታሪካዊ ሊባል ቢችልም የመጨረሻው ግብ ግን አይደለም ወደ ትግበራው

ለመግባት ከፍተኛ ትዕግስት ይጠይቀናል» ሲሉ ስምምነቱ ጥሩ ቢሆንም ውጤቱ የሚለካው በትግበራው እንደሆነ የሚጠቁም ንግግር አድርገዋል።

በመቀጠል ንግግር ያደረጉት የመኢአድ ሊቀመንበር የሆኑት ኢ/ር ኃይሉ ሻውል ሲሆኑ «በዚህ ድርጊት ብዙ ተወያይተናል ቅሬታ ቀርቶ በወዳጅነት መተያየት ጀምረናል። ይህን ድልድይ አንዳንዴ 16 አንዳንዴ ደግሞ 12 ከዚያም ሲያንስ 8 እየሆኑ ላመቻቹት ሰዎች ከፍተኛ አድናቆት አለኝ። በሰላማዊ ትግል ከድርድር ሌላ አማራጭ አለ ብሎ የሚያስብ ካለ ተሳስቷል። ይሄ በጐሪጥ የምንተያይበት ሥልጣን እኮ የህዝብ ነው። ዴሞክራሲን የሚገነባው ደግሞ ህዝብ እንጂ እኛ አይደለንም» ካሉ በኋላ ኢ/ር ኃይሉ አክለውም «እርስ በእርስ በመናከስ የኡኡታ ፖለቲካ ማራመድ አይገባንም ሰውም የሚለካው በራዕዩ ነው አንዳንዴ ስናፈነግጥ እየኮረኮሙ ለዚህ ስምምነት ያደረሱንን የኢትዮጵያ ወዳጅ አምባሳደሮች እጅግ አመሰግናለሁ» በማለት የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል።

በመጨረሻም ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ሲናገሩ «እኔና ኢ/ር ኃይሉ በአካል ተገናኝተን ለመነጋገር ባልቻልንበት ወቅት ሌሎች ተደራዳሪዎች የላቀ ውጤት በማምጣታቸው አመሰግናቸዋለሁ። እስካሁን ከመንፈሱ ያልተጋሩ አካሎች (መድረኮችን ማለታቸው ነው) እንደሚጋሩ ተስፋ እናደርጋለን» ብለዋል። ድርድርና ስምምነቱንም ታላቅ ክንዋኔ የሰለጠነ ድርድር ሲሉም አሞካሽተውታል።

ከስነ-ስርዓቱ ማጠቃለያ በኋላ የተወሰኑትን የፓርቲ አመራሮች እንደሚከተለው አነጋግረናል። ለድርድር ካቀረባችኋቸው ሀሳቦች ምን ያህሉ ተቀባይነት አግኝተዋል? ስንል ጥያቄ ያቀረብንላቸው ኢ/ር ኃይሉ ሻውል «አብዛኛው ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ይቻላል» ሲሉ መልሰዋል። ቀደም ሲል ስለፖለቲካ ምህዳሩ መጥበብ በስፋት ሲሟገት የነበረው መኢአድ ነው ከስምምነቱ በፊት ያለፉት ሁለት ወራት ምን ይመስላሉ ኢህአዴግ አሁን የገባውን ቃል ምን ያህል ይጠብቃል ብለውስ ያምናሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄም እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥተዋል።

«እኛ ድርድር ውስጥ በምንገባ ጊዜ ውጤት ይኖራል በሚል ግምት ነው። አሁን በተካሄደው ውይይት ከዚህ በፊት የነበረው የፖለቲካ አንቅስቃሴ ምህዳር ጠቧል ስንል ነው ድርድር ያደረግነው። አሁን ጥረታችን እሱን ለማስፋት ነው። በዛሬው እለት ስምምነት ተፈረመና ምህዳሩ ዛሬውኑ ሰፍቷል ብዬ ብናገር ውሸታም ልትሉኝ ነው። ይሄ ጉዳይ ጊዜ ይፈጃል። ሁላችንም በቀጣይ እንነጋገራለን ችግሮችም በጠረጴዛ ዙሪያ ይቀርባሉ መፍትሄም ያገኛሉ። በዚህ መልክ ነው የምንሄደው።» ይላሉ።

ሌላው የተነሳው ጥያቄ የምርጫ ቦርድን የገለልተኝነት ሁኔታ በጥርጣሬ ስለማየትና በአመራሮቹ አለመለወጥ ዙሪያ ስላለው ጥያቄና በስምምነቱ ውስጥ ምርጫ ቦርድን በተመለከተ ያገኙት ምላሽ ምን እንደሆነ ጥያቄ የቀረበላቸው ኢ/ር ኃይሉ

«በዚህ ዙሪያ በደንብ ተነጋግረን ምላሽ ያገኛል ተብለናል፡፡ የምርጫ ቦርድን ስንል የቦርድ አባላቱንና የአስፈፃሚ አካላትን ለይተን ማየት ይኖርብናል፡ ስለዚህ ድርድሩ እነዚህን ችግሮች ለይቶ መፍትሄ ያመጣላቸዋል፡፡» ሲሉ ድርድሩ በእውነተኛ መንገድ የተገኘ መሆኑንና ኢህአዴግም መስጠትና መቀበል ምን እንደሆነ ያሳየበት ሁኔታ እንደሆነ ጨምረው አስታውሰዋል፡፡

ሌላው ጋዜጠኞች በጋራ ያነጋገርናቸው በፓርላማ የመንግስት ዋና ተጠሪ የሆኑት አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ናቸው፡፡ ኢህአዴግ ለድርድሩ ፈቃደኛ የሆነው የተቃዋሚ ፓርቲዎችን መዳከም አይቶ ነው ይባላል እርሶ በዚህ ይስማማሉ? ተብሎ ከጋዜጠኞች ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱ «ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ስላላዳከመ አሁን ይህን ማውራት አንችልም፡፡ ደግሞም ማን ደካማ ማን ጠንካራ ነው ብለን ተቃዋሚዎችን አልገመገምንም ራሳቸውን የሚያወቁት ራሳቸው ተቃዋሚዎች ናቸው እኛ ዋናው አላማችን ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምርጫ እንዲካሄድ እና ይህቺ አገር ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምርጫ ልታካሂድ እንደምትችል ማስመስከር ነው በዚህ ጊዜ ተቃዋሚዎች ጠንካሮች ወይም ደካሞች ሊሆኑ ይችላሉ ያ የውስጥ ጉዳያቸው ነው ሊሆን የሚችለው» በማለት በአጽንኦት ተናግረዋል፡፡

አሁን የተደረገው ስምምነት ተቃዋሚዎችን የሚያጠናክር ነው? ለተባሉት አቶ ኃ/ማሪያም ሲመልሱ «ልንገምት እንችላለን፡፡ እያንዳንዱ ፓርቲ የራሱ ሂደት አለው የእኔ ፓርቲ እዛ ቁጭ ብሎ እየተደራደረ ነው በሚል ሞራል ይሰማዋል፡፡ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም በተመሳሳይ መልኩ ይነሳሳሉ፡፡ ይሄ ስምምነት የሚጠቅመውና የሚያጠነክረው ሁላችንንም ነው ብለን እናምናለን» ይሄ የስነ ምግባር ደንብ የሁሉም ፓርቲዎች ገዢ ነው? የሚል ተጨማሪ ጥያቄ ተነስቶ «በህግ ሲቀረጽ አዎ ገዢ ነው፡፡ አንድ የሀገሪቱን ህግ ለማክበር ዜጎችም ፓርቲዎችም ይገደዳሉ፡፡ አላማችን ወደ ህግ መውሰድ ስለሆነ በህግ ሲቀረጽ ማንንም ዜጋ ህጉ ያስገድዳል፡፡»

የመድረክን ጉዳይ በተመለከተም ጥያቄ አቅርበንላቸው ነበር፡፡ አቶ ሀይለማርያም በሰጡት ምላሽ፡፡ መድረክ ለመደራደርም ላለመደራደርም የሚወስነው ራሱ ነው እና ግን እስከመጪው ምርጫ ለመደራደር ዝግጁ ነን በራችንም ክፍት ነው አሁንም በአጽንኦት የምናገረው በአገራዊ ጉዳይ በግል አንደራደርም የምንደራደረው ጥቂት ሰዎች ነን ስለዚህ በግል ብለን አንዱን ሁለት ወር ሌላውን አራት ወርና ከዛ በላይ እያልን ጊዜ የምናባክንበት ምክንያት የለም» በማለት ምላሻቸውን ቋጭተዋል፡፡ በእለቱ የነበረው የፊርማ ስነ-ስርዓት ከላይ ለመዳሰስ የሞከርነውን የሚመስል ሲሆን በተለይ ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ እና ኢ/ር ሃይሉ ሻውል በሚጨባበጡበት ቅጽበት በታዳሚው የፊት ገጽታ ላይ የነበረው ፈገግታ ለአፍታም አይዘነጋም፡፡

# የአቶ ስዬ አብርሃ እህት አላግባብ ቤት ፈርሶብኛል አሉ

## «ቤቱ የፈረሰው ህገ ወጥ ግንባታ በመሆኑ ነው»

የየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 19/ሎቄ ዋና ስራ አስፈጻሚ

በኤልያስ ገብሩ

ወ/ሮ ብዙነሽ ገ/መድህን የተባሉት የአቶ ስዬ አብርሃ እህት ለ25 ዓመት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይኖሩበት ከነበረው የቀበሌ ቤት መካከል የዛሬ ዓመት ገደማ በብሎኬት እድሳት አድርገው የሚኖሩበትን ሁለት ክፍል ቤት አግባብ ባልሆነ ሁኔታ የየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 19/ሎቄ ስራ አስፈፃሚና ደንብ አስከባሪዎች ቤቱ እንዲፈርስ እንዳደረጉባቸው ለአውራምባ ታይምስ በአዘኔታ ገልፀዋል፡፡

ወ/ሮ ብዙነሽ የቀበሌ ቤቱን ከ1977 ዓ.ም (ከደርግ ዘመን) ጀምሮ ከፈረሰና ከወደቀበት አንስተው በማደስ ለ2 ዓመት ያህል በነፃ ከተገለገሉበት በኋላ እስካአሁን ድረስ ተገቢውን ክፍያ ለመንግስት እየከፈሉ እንደሚገኙ ተናግረው ከአመት በፊት ጭቃ የነበረውን ሌላ 2 ክፍል ቤት የማቴሪያል ለውጥ በማድረግና በማደስ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው እየኖሩበት ነበር፡፡ ሆኖም በ17/03/2001 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ደንብ ተላልፈዋል በሚል 500.00 ብር ቅጣት መክፈላቸውን አስረድተዋል፡፡ «ባለፈው ሳምንት በእለተ ሰኞ ከቀኑ 11:30 ላይ በነጋታው ቤቱ እንዲፈርስ የሚል ደብዳቤ ከቀበሌ ደረሰኝ በማግስቱ ጥዋት 2:30 ላይ መሳሪያ የያዙ ስምንት ደንብ አስከባሪዎችና የቀበሌው የስራ አስፈፃማዎች መጥተው ቤቱ መፍረስ አለበት ተባልኩኝ፡፡ እሺ ግቢ ውስጥ አትግቡ እኛው ራሳችን እናፈርሳለን ብለን ራሳችን ቤቱን ለማፍረስ ተገድደናል፡፡» ይላሉ፡፡ ለአምስት አመት ያህል የቀበሌው አስተዳደር እንደነበሩ የሚገልጹት ወ/ሮ ብዙነህ አያይዘውም «ይሄ የተደረገው በቂም በቀል ነው፡፡ ሌሎች ከኛ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ቤቶች እስካሁን አልፈረሱም፡፡ እኔ 12 ቤተሰብ ይገፔና ቤቱን ለማደስ 45 ሺ ብር ገደማ አውጥቼ እንደዚህ አሳዛኝ ነገር በመደረጉ እጅግ አዝኛ ለሁ፡፡ አሁን አሁን ወደ ቀበሌው መታወቂያ ለመቀየር እንኳን ስንሄድ ፋይላችሁ ጸረ ሙስና፣አቃቢ ህግና ክፍለ ከተማ ሄዷል በአዲስ ፋይል ተቀበሏቸው ነው የምንባለው፡፡ይሄ ለምን ይሆናል?» ብለዋል፡፡

ስለጉዳዩ አውራምባ ታይምስ ጥያቄ ያቀረበላቸው በየካ ክ/ከተማ የቀበሌ 19/ሎቄ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተባበር አበበ የተባለው ቤት መፍረሱን አምነው ቤቱ የፈረሰበት ዋነኛ ምክንያት ህገ ወጥ ግንባታ በመሆኑና በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ተፈፃሚ ሊሆን መቻሉን ተናግረዋል፡፡ «ባለፈው አመት ቤቱ በህገወጥ መንገድ በመታደሱ 500 ብር ተቀጥተዋል፡፡ ይህ ቅጣት ደንብ በመተላለፋቸው ብቻ የተወሰነባቸው እንጂ ቤቱን ከመፍረስ አያድነውም፡፡» ብለዋል፡፡ አቶ ተባበር አያይዘውም «ወ/ሮ ብዙነሽ በወቅቱ

ከሰሰው ፍ/ቤት ቤቱ እንዳይፈርስ አግዶ የነበረ ቢሆንም ከ15 ቀን በፊት ቤቱ በህጋዊ መንገድ ባለመታደሱ እንዲፈርስ ውሳኔ በመስጠቱና ለኛ በደረሰን የፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት 15 ቀን ጠብቀን ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በህጉ መሰረት እንዲፈርስ ተደርጓል፡፡» ብለዋል፡፡ ቤቱ የፈረሰው በቂም በቀል ነው መባሉን አስመልክተው በሰጡት አስተያየት «ቂምበቀል የሚባለው ነገር ግለሰባዊ ሊሆን ይችላል፡፡ እኔ ግን በግሌ ከቤተሰቡ ጋር ቤተሰባዊና ሰላማዊ ግንኙነት አለኝ፡፡ እንዲሁም ከነሱ በፊት 3 ቤቶች የፈረሱ ሲሆን አሁንም በቀጣይ የሚፈርሱ ቤቶች እንዳሉ መግለጽ እወዳለሁ» ብለዋል፡፡

## ኮሜንተሪ

## ኃይሉ ሻውል፡-

# ፖለቲከኛ? ልማታዊ ባለሃብት? ወይስ ሁለቱንም?

**በውብሸት ታዬ**

በጣት ከሚቆጠሩት ኢትዮጵያውያን 'ባለጸጋዎች' አንዱ ናቸው፡፡«ሻውል ኮንሰልቲንግ» የሚባለውና መቀመጫውን በአዲስ አበባ ያደረገው የቤተሰባቸው ግዙፍ ኩባንያ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር በስኬት እየገሰገሱ ካሉ ጥቂት ኩባንያዎች የፊት መስመር ላይ ይገኛል፡፡ የላፍቶው ግዙፍ ማዕከል ብቻውን ባለሃብቱ የተወጣጡበትን ከመንግስት ሰራተኝነት እስከ መልቲ ሚሊየነርነት ያደረሳቸውን በሰምና ወርቅ የተባጀ መሰላል ጠቋሚ ነው፡፡ በአንድ የአገራችን ክልል የአውሮፕላን ማረፍያ ደረጃን የማሳደግ ኮንትራት መፈራረማቸውን መረጃዎች ይፋ አድርገዋል፡፡ በሚኒሶታ ደግሞ ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጣ ዘመናዊ መኖሪያ ቤት አላቸው፡፡ እኚህ አዛውንት ብዙዎች በ«ሩቁ» በሚሉት የተቃውሞ ፖለቲካ መድረክ በተለይ አንፀባራቂ ኮከብ ሆነው ከተከሰቱበት የ97 ምርጫ ወዲህ ባለፈው አርብ ከገዢው ፓርቲና ከሌሎች ሁለት ፓርቲዎች ጋር በጋራ ሲወያዩበት የቆዩትን ድርድር ከተፈራረሙ በኋላ ግን በርዕሳችን ላይ የተመለከተው መጠይቅ ጎላ ብሎ መቅረብ ጀምሯል፡፡ ወደኋላ አምስት አመታት በትውስታ ልውሰዳችሁና ይህ ጥያቄ የሚቀርብበትን ነፅሮት አብረን እንይ፡፡

**የሰኔ 8/97ቱ ቃለ ምልልስ**

ቦታው ሻላ መናፈሻ አካባቢ የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ዋናው ጽ/ቤት፣ እለቱ ሰኔ 8 ቀን 1997 ዓ.ም ቃለ ምልልሱ የተደረገው በሊቀ መንበሩ ቢሮ ውስጥ ነበር፡፡ ይህ ወቅት በኢህአዴግ በቅንጅትና በሕብረቱ አማካይነት የሶስትዮሽ ስምምነት የተካሄደበት፣ ኢ/ሩና የባለፈውን አርብ የድርድር ፊርማ በጋራ ያሳረፉት አቶ ልደቱ በአውሮፓ ህብረት የአደራዳሪነት ጫና ነፃ ወጡ የተባለበት፣ «የእኛ መታሰርና

መታገት ልዩነት አያመጣም፣ የምንታገለው የሕዝብን ድምጽ ለማስከበር እንጂ ለፓርላማ ወንበር ማሞቅ አይደለም!» በሚል መሬት አንቀጥቅጥ መግለጫ የሚሰጥበት ነበር። በዚህ ዕለት ከባልደረባዬ ጋር በመሆን ተፈፀመ በተባለው እገታ፣ በግል ደህንነታቸውና በአገሪቱ ውስጥ  እየተካሄደ በነበረው የፖለቲካ ውጥረት ጉዳይ ላይ በቆይታ አነጋግረናቸው ነበር። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ስኬትን እየተቀዳጁ የመጡትና «ቅሬታ ቀርቶ በወዳጅነት መተያየት ጀምረናል» በሚል የገዢውን ፓርቲ ሰጥቶ ለመቀበል ሆደ ሰፊ መሆን ያወደሱት ኃይሉ ሻውል ሰጥተውት የነበረውን ምላሽ ማንሳቱ ጥያቄ የሚቀርብበትን ነፀሮት ለመረዳት ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

«ታሰርን፣ ተፈታን.... በምንሰራው ስራ ላይ ምንም ለውጥ አይመጣም። አሁን እየተደራደርን ያለነው ይህን ያለመግባባት በሰላማዊ መንገድ መፍታት ይቻላል ወይስ አይቻልም? በሚለው ጉዳይ ዙሪያ ነው። የእነሱ ፍላጎት ግን ይህን ሁሉ ሕዝብ ግራ አጋብተው የሚሉትን ብቻ እንዲቀበል ነው። እኔን አስረው ስለለቀቁ አልያም ልደቱን ስለፈቱ የምንቀበለውና የምንሸረው ነገር አይኖርም። - የቆምነው ለሕዝብ ነው።» ነበር ያሉት።ጥቂት ዘግይቶ፤ በድህረ ምርጫ ቀውሱ ሰበብ ታሰሩ፣በመጨረሻ ሁላችንም እንደምናስታውሰው ይቅርታ ጠይቀው ተፈቱ። የእስሩ ጉዳይ እልባት ያገኘው በገደብ የመሆኑ ነገር እንዳለ ሆኖ ከእስር በፊትና በኋላ እንዲሁም ከድርድሩ መፈረም ማግስት ያሉትን ምዕራፎች ፖለቲካውን በቅርብ የሚከታተሉ፣ ደጋፊዎቻቸውና ከአገር ውጭ ያለው ማሕበረሰብ በሶስት ከፍለው የሚመለከቷቸው ሲሆን በርዕሳችን ላይ  ያለውን «ኢ/ሩ ልማታዊ ባለሃብት? ፖለቲከኛ? ወይስ ሁለቱንም አጣምረው የሚጓዙ?» ብለው እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል። ከዚህ አንጻር በውጭ የሚኖሩ ታዋቂ ኢትዮጵያውያንን አስተያየትና  የአገር ውስጥ አንባቢዎቻችንን ሃሳብ በአጭሩ ስንዳስሰው የሚሰጠን የጠራ ምስልም ይኖራል።

**«እስከዛሬ ለኃይሉ ሻውል በሰጠሁት ድጋፍ ይቅርታ እጠይቃለሁ»**

አምባሳደር እምሩ ዘለቀ

ታዋቂው ዲፕሎማትና ለመኢአድ ከፍተኛ ድጋፋቸውን በመስጠት በግንባር ቀደምትነት ስማቸው የሚነሳው አምባሳደር እምሩ ዘለቀ ከፊርማ ክንውኑ በኋላ «እስከዛሬ ድረስ ለኃይሉ ሻውል በሰጠሁት ድጋፍ ይቅርታ እጠይቃለሁ።» ሲሉ ተደምጠዋል። አምባሳደሩ የተፈረመውን  ስምምነት ሙሉ ሃሳብ በጥንቃቄ ማንበባቸውን በመግለጽ የኢ/ሩን አቋም ተችተዋል።  «እንዲያውም የቀድሞ ድጋፌን የሰጠሁት ለመኢአድ እንጂ ለግለሰቡ አልነበረም።» ሲሉም ደምድመዋል።

**«የቀድሞው ቅንጅት አፍራሽ ማንነት አሁን ታወቀ»**

አቶ ነአምን ዘለቀ

የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ተሚጋችና ፀሐፊ የሆኑት አቶ ነአምን ዘለቀ «በምርጫ 97 ወቅት የትግል አጋሮቻቸው የሆኑ አመራሮች በምስጢር ከገዢው ፓርቲ ጋር የሚደራደሩ በማስምሰል ሃሜት ይነዙ ነበር:: አሁን የተፈፀመው ውልና ገዢውን ፓርቲ ማሞካሸት ወደኋላ መለስ ብለን የቀድሞውን ቅንጅት ያፈረሰው ማን እንደሆነ በግልጽ አሳይቶናል::» ብለዋል::

*«99 በመቶ የዲያስፖራ ድጋፋቸውን አጥተዋል»*

**የተለያዩ ድረ ገጾች**

እነዚሁ ድረ ገጾች በስፋት ከዘገቡት ክንውን አንዱ ይኸው የምርጫ ስነ ምግባር ሰነድ መፈረም ጉዳይ ሲሆን በኢ/ሩ ላይ የሰሉ ትችቶችን አስተናግደዋል:: «በዲያስፓራው ያላቸው ድጋፍ ከአንድ በመቶ በታች እንዲሆን አድርገዋል» ብለዋል:: ይህ ሁሉ የተቃውሞ ቁጣ ይቀስቀስ እንጂ ድጋፋቸውን ካላነጠፉ ወገኖች አንዱ የኃይሉ ሻውል የቅርብ ወዳጅና በኒውዮርክ የመኢአድ ድጋፍ አሰባሳቢ የሆኑት አቶ አባተ ካሳ ብቻ የማንዴላን 'በድርድር ሰላም የመፍጠር ተሞክሮ' በማንሳት አነፃጽረዋቸዋል::መከራከርያቸው «ፍየል ወዲህ...» በሚል አስተረተባቸው እንጂ::በእርግጥ አንዳንድ የአገር ውስጥ የህትመት ውጤቶችም «ታሪካዊ!»ብለውለታል::

**የአገር ቤቱ የተቃውሞ መሰረት**

በርካታ አንባቢዎቻችን እየደወሉ «የምናውቃቸው ኃይሉ ናቸው ወይም ሌላ?» በሚል መንደርደሪያ ስለ 93 ፓርቲዎች በሚነገርበት አገር አራት ሆነው የፈጸሙት ስምምነት ሁሉንም የሚገዛ በሆነበት ውል፤ ስምምነቱን ሰጥቶ መቀበል የተትረፈረፈበት ሲሉ ማሞካሸታቸው ከፖለቲከኝነታቸው ይልቅ ለሚያካሂዷቸው የኢንቨስትመንት ስራዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት የዴሞክራሲ ዘውግ የሆነውን የብዙሃን እሳቤ ወደጎን አድርገው ግለኛ አቋም የወሰዱ አስመስሎባቸዋል ሲሉ ነቀፌታቸውን አቅርበዋል::

***«የኡኡታ ፖለቲካ...»***

*«የኡኡታ ፖለቲካ ማቆም አለበት::» የሚለው ቁርጠኝነት የተንጸባረቀበት አገላለጽ «አንዳንዴ ስናፈነግጥ 'እየኮረኮሙ' ለዚህ ስምምነት ያደረሱን አምባሳደሮች አሉ::» በሚለው ማሰናሰያ ታጅቦ መቅረቡ የኢ/ሩን አዲሱንና ሰላማዊ አማራጭን ብቻ በመከተል ከማረሚያ ቤት ፈርመው ለወጡበት ውል ተገዥ መሆናቸውን በተግባር ያሳዩበት ነው የሚል ዝና ሳያጎናጽፋቸው አልቀረም:: ይህም ፖለቲከኛ? ልማታዊ ባለሃብት? ወይስ ሁለቱንም? በሚል ለሚቀርበው አንክሮ ፖለቲካንም ኢንቨስትመንትንም በተረጋጋ ሁኔታ ለማካሄድ የሚጠይቀውን የመጀመሪያ እርምጃ በመውሰድ ፈር መቅደዳቸውን አሳይተዋል:: ቀጣዩ ማን ይሆን?...*

# አንድ «ወንድ!» ብቻውን ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ!

***«ወንድ!» ተብሎ የተገለፀው ያታውን ለመጠቆም ብቻ ነው::***

**አቤ ቶኪቻው**

**abeto2007@yaoo.com**

«ሰርከስ በኢትዮጵያ ለወጣቶች እና ማህበራዊ ልማት» የተባለው ድርጅት በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች በርካታ ወጣቶችን እያሰለጠነ የተለያዩ አስደናቂ ትርኢቶችን ማሳየት ከጀመረ አስራ ስምንት ዓመት እንደሞላው የሚያስረዳ ዘገባ ከአንድ ወዳጄ ጋር ቁጭ ብለን እየተመለከትን ነው:: በዘገባው መሃከል ወጣቶቹ የተለያዩ አስደናቂ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ሲያሳዩ እኔ በመደነቅ እና በተመስጦ መከታተሌን ተያያዝኩት:: ይሄን ጊዜ ወዳጄ ዘገባውንም፣ የወጣቶቹን ቅልጥፍናም የእኔን መደነቅም በሚያጣጥል የፊት ገፅታ «ይሄ ምን ይገርማል?» አለኝ:: እኔም ይህ ማድነቂያ ክፍሉ የተበላሸበት ወዳጄን በአግራሞት እያየሁት «ይህ የወገብ ቅልጥፍና አይደንቅህም?» አልኩት ወደ ወጣቶቹ እያሳየሁት:: እሱም እኔን በአግራሞት እያየኝ «ከእነርሱ የወገብ ቅልጥፍና የእኔ ሆድ ቻይነት አይደንቅህም?» አለኝ:: እኔ በጠየኩት ዜማ:: ቀጠል አደረገናም «እኔም መድረኩን ባለማግኘቴ እንጂ ኑሮዬን በሰርከስ መልኩ ባሳይ ዓለም ያደንቀኝ ነበር::» ሲል «አልገባኝም::» አልኩት:: «እነርሱ ወገባቸውን መተጣጠፍ ማለማመድ ሲጀምሩ እኔም ሆዴን ያም ማለማመድ ጀመርኩኝ፤ ይኸው ዛሬ እነርሱ እዚህ ቅልጥፍና ላይ ሲደርሱ እኔም ያለምግብ እና ያለመጠጥ ቁጥሩ ለማይታወቅ በርካታ ቀናት የመቆየት ችሎታ ባለቤት ሆኛለሁኝ:: ከዚህ የበለጠ ሰርከስ ከየት ይመጣል?» አለኝ:: «በደህና ነው?» አልኩት ድምፄን ዝግ አድርጌ:: «ምን ደህንነት አለ እነ አጅሬ ደህንነቱን ለእናተ ድህነቱን ለእኛ ሰጥታችሁን በደህና ነው? ብላችሁ ስትጠይቁ አታፍሩም?» አለኝ:: አሁን ገባኝ፣ ወዳጄ «ያለምግብ ያለመጠጥ በመቆየት ችሎታዬ ሰርከስ አሳያለሁኝ» የሚለው ድህነቱት፣ በኑሮ ውድነት መንሳቆሉን ለማስረዳት ነው:: በሆዬ አንድ አንዱ ሰው አለቅጥ ያጋንናልና! ብዬ እያሰብኩኝ ሌሎች የተጋነኑ ብሶቶቹን ላለመስማት ጆሮ እና ፊት ነሳሁት::

ወዳጄ እርስዎ እንዴት ሰንብተዋል? ኑሮ «አሸወይናና!» እንደሆነ አይጠረጠርም:: ይመችዎት! እንዲህ ዓይነቱ የፍስሃ እና የጥጋብ ጊዜ ታይቶም አይታወቅም:: አሁን አሁንማ ጥጋቡ አላላውስ አላንቀሳቅስ ብሎናል:: (በቅንፍ «ጥጋብ» የሚለው ቃል ውርስ ትርጉም ባልታተመው አዲሱ መዝገበ ቃላት ላይ እነደሰፈረው ከሆነ ሳይበሉ ሳይጠጡ «ተመስገን ጌታዬ የባሰ አታምጣ!» የሚለውን የዘወትር ፀሎት በመፀለይ መትጋት:: የሚል ትርጓሜ አለው::) እህስ ታድያ ጥጋቡ እንዴት ይዞታል? ይበርቱ ጥጋብን የመሰለ

ነገር ምን አለ? «ለዚህ ጥጋብ ያበቁንን ሰዎች ውለታ መላሽ ያድርገን።» ብለው ይመርቁ።

ብሶት ትጥቁ፣ ብሶት ስንቁ የሆነው ወዳጄ ፊት እና ጆሮ ልነሳው ሙከራ ባደርግም እርሱ ግን ዝም አላለም። ቆይ አንድ ጊዜ ዝም አላለም ስል ትዝ ያለኝን አንድ ጉዳይ ላውጋዎ እና ወደ ወዳጃችን እመልስዎታለሁኝ (ወዳጃችን መስመር ላይ ጠብቀን አንድ ጨዋታ አየር ላይ ነው። አየር ላይ ያለው ጨዋታ ይቀጥላል።) «ዝም አንልም!» ያሉት የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ አባላት ጉዳይ ምን ደረሰ? በሚለው ጉዳይ ላይ ከወዳጆቼ ጋር ጨዋታ አንስተን ስናወጋ አንዱ «የታገዱት» አባላት «ከእንግዲ ዝም አንልም!» ካሉ በኋላ በየመድረኩ እየቀወጡት መሆኑን፤ አባላቱ በውስጣቸው ስላለው ብልሹ አሰራር በሥልጣን ብልግና እና አምባ ገነንነት፣ ሎሌነት እና ከዚህ በፊት ሰምተናቸው የማናቅ በርካታ ነገርነቶች ጋር አብረው መኖራቸውን በበርካታ መገናኛ ብዙሃን ላይ ሲያቀርቡ እየሰማን ነው።» ካለን በኋላ «እኔ የምለው...» ሲል ቀጠለ። እርሱ እሚለው... «ልክ እነርሱ «ዝም አንልም!» ማለት ሲጀምሩ እነዛኞቹም «አናዳምጥም!» ብለው ነው? ወይስ ምንድነው እንዳይደማመጡ ያደረጋቸው? ምናለ ለእግዜሩ ሲሉ፣ ለደጋፊዎቻቸው ሲሉ፣ ሌላው ሁሉ ይቅርና ለታሰረቺቱ ዳኛ ሲሉ... አንድ አፍታ ሰብሰብ ብለው «አፉ» ቢባባሉ?» አለን። ሌላው ንግግሩን በመደገፍ ቀጠለ «እውነት እውነት እላችኋለሁኝ ለዚህ ህዝብ የሚጠቅመው «አፉ!» መባባል ነው!» ሌላውም አከለ «የሚበላ ከአፉ ላጣ ህዝብ መሪዎቹ «አፉ» ብትባባሉ ተስፋ እንዲሆነው አታውቁምን?» እኔም ጨመርኩኝ «ሞፈሩን ያዙና ይቅር ተባባሉ!» (የኔዋ ልማታዊ ምክር ናት አይደል?)

ወደ ዋናው መስመር ስንመለስ «ብሶት ትጥቁ፣ ብሶት ስንቁ የሆነው ወዳጄ ፊት እና ጆሮ ልነሳው ሙከራ ባደርግም እርሱ ግን ዝም አላለም።» ብዬ ነው ያቆምኩት። ቀጠለ ወዳጄ «ኑሮዬ የሰርከስ ትርኢትን ያስንቃል! እውቅና ይሰጠኝ፣ ሳይበሉ ሳይጠጡ የመኖር ትርኢት ማሳየት እችላለሁኝ! ይህን ያስለመደኝ ፀሐዩ መንግስቴ ፀሐይ ይውጣለት!» አለኝ። ዝም አልኩት፤ ቀጠለ። «ሰሞኑን ከሰማኋቸው ዜናዎች በሙሉ እጅግ በጣም የወደድኩትን ዜና ልንገርህ?» አለኝ አሁንም ዝም አልኩት እርሱ ግን አንዴ «ዝም አልልም» ብሏልና ዜናውን ነገረኝ።

«አንድ «ወንድ!» ብቻውን ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ!» ሲለኝ «ወንድ!» የሚለውን ጠበቅ አድርጎ ነበርና ኮስተር ብዬ «ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ወንድነት ነው እንዴ?» አልኩት ወድያው መለስ ብሎ «የኔ ጌታ እኔ ነገር አልፈልግም «ወንድ!» ያልኩት ፆታውን ለመጠቆም ነው።» አለኝ። ቀጥሎ «ወጣት ነው፣ የሰላሳ ዓመት ወጣት «የነዳጅ ዋጋ ጭማሪን መሸከም አልቻልኩም፣ ኑሮ ከብዶኛል የሰሚ ያለህ... ብሎ ኡኡታውን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ እና የነዳጅ ዋጋን በመጨመር አንጀታችንን ለሚያነደው አንድ ቢሮ አቤቱታውን አስገብቷል። ይህ «ወንድ!» ወጣት መሪዬ ነው!» አለኝ። እንዴት? አልኩኝ ንግግሩን እርሱም እንዳይክድ እኔም እንዳልረሳው ማስታወሻ እየያዝኩኝ። «እኔ

ጎስቋላ ሰው ነኝ። ይህ ሰው የጮኸው ጩኸት የእኛ የጎስቋሎቹን ኡኡታ! ነው። እኛም ፍርሃት አጥሮን እንጂ ኡኡ! ማለት ሳያሰኘን ቀርቶ አይደለም። ስለዚህ ይህ «ወንድ!» የፖለቲካ መሪዎቻችን ያልጮሁልንን ጩኸት ኡኡ! ስላለልን ክብር ይገባዋል፤ በበኩሌ መሪዬ ነው።» አለኝ።

ስለ ኡኡታ! ካነሳን አይቀር ሰሞኑን አንድ ንግድ እና ፖለቲካን አጣምረው የያዙ «የተከበሩ» ፖለቲከኛ «የኡኡታ ፖለቲካ ማካሄድ ፋይዳ የለውም!» የሚል ድንቅ ንግግር ተናግረው በደስታ ሲያሳክሩን ቆይተዋል። ንግግሩ የተሰነዘረው በ «ሰጥቶ መቀበል» መርህ ላይ የተመሰረተው የአራቱ ፓርቲዎች ስምምነት በተፈረመበት እለት ሲሆን ሌሎችም የፖለቲካ መሪዎችም የተናገሯቸው ንግግሮች እጅግ በጣም ጣፋጭ ከመሆናቸው የተነሳ «ትንሽ ዜማ ተጨምሮላቸው በሲዲ ሁላችንም ብንዘፍነው መልካም ነው።» የሚሉ አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ነው።

ድርድሩ ምንም እንኳ ከዘጠና ሶስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሶስቱ ብቻ የተሳተፉበት ቢሆንም፣ (በነገራችን ላይ ዘጠና ሶስት ስላችሁ ዓመተ ምህረቱ እንዳይመስላችሁ በሀገሪቱ ውስጥ በተቃዋሚነት የተመዘገቡ የፓርቲዎች ብዛት ነው።) እናም ከዚህ ሁሉ ፓርቲ ሶስቱ እና ገዢው ግንባር ሲጨመር አራት ሆነው ያወጡት የምርጫ ስነምግባር ደንብ «ሰጥቶ በመቀበል» መርህ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ «ስልጡን ፖለቲከኞች» የሚያደርጉት ነው። ስለሆነም እውነትም ማነው ስማቸው እንዳሉት «የኡኡታ ፖለቲካ ማካሄድ ፋይዳ የለውም!»፣ እናም ስምምነታቸው የሚወደድ ነው የሚል አስተያየት ስሰነዝር የሰማኝ አንድ ወዳጄ «እውነት ብለሃል የኡኡታ ፖለቲካ ፋይዳ የለውም ግን ከአቅም በላይ የሆነ ጉልበተኛ ሲመጣብህ ኡኡ ከማለት ውጪ ምን አማራጭ አለህ? ይሄ ህዝብ እኮ የኡኡታ ሱስ የለበትም። ሲበዛ ሲመረው እንጂ «ዝምታ ወርቅ ነው ብሎ ዝም የሚል ህዝብ ነው።» አለኝ። ከዚህ በፊት ከአቅም በላይ ሆነ ብላችሁ «ኡኡ...» ስትሉ ምን ተጠቀማችሁ? ብሎ መጠየቅ። ማ? እኔ። ወዳጄ የሚመልሰው አጥቶ «እሱማ...» እያለ ፀጉሩን ማከክ። በዚህ መሃል ሌላ ወዳጃችን ጣልቃ ገብቶ «ኡኡታማ ጥቅም አለው፣ ወዳጅ ጠላት ለመለየት ማን እንደ ኡኡታ!» አለን። ለመውረግረግ እየቃጣው። ታዲያ በቀደመው ጩኸት ማን ወዳጅ ማን ጠላት ሆኖ ተገኘ? ብዬ ብጠይቀው «የኔ ጌታ ከተደራዳሪዎቻችን አታቀያይመኝ። ስም አልጠራም» አለን።

የሆነ ሆኖ ባለፈው ምርጫ የነበረው «የኡኡታ ፖለቲካ ግማሹን ለእስር ግማሹ ለ «ነውጥ» እንዲሁም ምክር እና ቅጣቱ በደንብ የገባቸውን ደግሞ ለድርድር ይበቁ ዘንድ አድርጓቸዋል። በእኔ አስተያየት ስምምነትን የመሰለ ነገር የለምና እሰየው ብያለሁኝ።

**በመጨረሻም:-**

አንዲት ወዳጄ በቅርቡ የቤተዘመድ ልጅ ክርስትና አስነስታ ነበር ታድያ በዕለቱ እጅግ አስገረመኝ ብላ ያወጋችኝ የሚከተለውን ይመስላል።

ባህለ ብዙ ነን እና አንድ ህፃን ክርስትና ተነስቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ በሰፌድ ላይ እንጀራ ተዘርግቶ ይጠብቀዋል:: ታድያ ህፃኑ ያለ ሃሳብ በእንጀራው ላይ እንዲንከባለል ይደረጋል:: (ስንጠረጥር ይህ ባህላዊ ክንውን የሚደረገው ህፃኑ ወደፊት የጥጋብ ዘመን ይመጣለት ዘንድ ለመመኘት ነው::)

ወዳጄ ይህንን ባህላዊ ድርጊት ከተመለከተች በኋላ «የዘመኑን የጤፍ ዋጋ ከግንዛቤ ያላስገባ ድርጊት ነው፤ በተወደደ እንጀራ ህፃኑ እንዲንከባለልበት መደረጉ አንገብግቦኛል::» ስትል በቁጭት አወጋችኝ:: እኔም እውነትም ሰዉ ሆድ ብሶታልና ስል ለወዳጅነታችን በማሰብ ባህሌን አብሬ ኮነንኩኝ:: (ይቅር ይበለኝ) ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዱ ወዳጄ ዘወትር የሚያበሳጨው አንድ የቴሌቪዥን ማስታወቂያ አለ:: ማስታወቂያው የሳሙና ማስታወቂያ ነው:: አለቃ ገብረ ሃና ሰው ፊት እንዲቀርቡ ያደረጋቸውን ፀአዳ ልብስ ወጥ ሲያልሱት ይታያል:: «የሚያሳዝነው...» ይላል ወዳጄ «ተረቱ የሚተረተው ነብስ ላላወቁ ህፃናት መሆኑ ነው:: በዚህ ኑሮ ወጥ ቆጥቡ እንጂ ልብስ ቀቡ ብሎ እንዴት ይመከራል?» ሲል በጣም አምርሮ ይናገራል::

ይህን ይህንን ስንመለከት ይሄ ኑሮ የሰዉን አመል ቀያይሮታል ያሰኛል:: ይሄው ብቻውን የተቃውሞ «ሰልፍ» የወጣው:: ሰውስ «ኑሮ ከፋኝ አይደል ያለው::» ኧረ ጎበዝ፣ ቻል ማድረግ ነው የሚሻለው አለበለዛማ የተቸገረ ሁሉ ደብዳቤ ይዞ ወደ ቤተ መንግስት ካመራ እኮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቤተመንግስቱ በወረቀት ሊሞላ ነው:: የሰማ ሰውስ ምን ይላል፤ ለመልካም ገፅታችንስ አይታሰብም እንዴ?

ይብቃህ ይበሉኝ ወዳጄ፤ እናም እንሰነባበት!

አማን ያሰንብተን!

# የነዳጅ ድጎማው መነሳት

## /ከእሳቱ ወደ ረመጡ/

**በውብሸት ታዬ**

*ረቡዕ ማለዳ ማለትም ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም ክቡር ሚ/ሩ በሚሰጡት የመንግስትን የሥራ እቅድና አቋም የሚተነትን ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ለመገኘት ሳቀና አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ስላላት ህንድ እያብሰለሰልኩ ነበር:: የኢትዮጵያ መንግስት ቃል አቀባይ የሆኑት ሚ/ር በሚሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ተሳታፊ ለመሆን የሚጓዝ ዜጋ በተለይ ስለህንድ እንዲያብሰለስል ያደረጉት ነገሮች ምንድናቸው? ብሎ መጠየቁ ተገቢና የሚጠበቅ ይሆናል:: መጀመሪያ እስኪ ስለ ህንድ በጣም በጥቂቱ ለመመልከት እንሞክር::*

## አንፀባራቂው ተሞክሮ

ከላይ የተመለከተው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት ህንድ ጥንታዊና ምሉዕ የሚሰኝ ህገ መንግስት ያላት ሲሆን የአገሪቱ ጠ/ሚ/ር ከፍተኛውን የአስፈፃሚነት ስልጣን ተቀዳጅቷል:: ህገ መንግስቱ ህንድ ሉአላዊት፣ ሶሻሊስት፣ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩባት እንዲሁም ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ መሆኗን ይደነግጋል:: የምዕራባውያን ፓርላሜንታሪ ስርአት ታራምዳለች:: ፌዴራላዊ አደረጃጀት ቢኖራትም የማዕከላዊ መንግስት ኃይል ግዙፉን ድርሻ (የፈላጭ ቆራጭነቱን) ይይዛል:: ይህ ሁኔታ ግን በዘርፈ ብዙ የእድገት መንስኤዎች እየተቀየረ መጥቷል:: የማህበራዊ መስተጋብሮች መበልፀግ፣ የምጣኔ ሃብት በተጨባጩ ማደግና የሰለጠነ ፖለቲካ ህንድን እየቀየሯት ነው::

በአንድ ወቅት በድህነት፣ መሐይምነትና በፈላጭ ቆራጭ መንግስታዊ አስተዳደር አይነተኛ ምሳሌ ተደርጋ የምትቆጠረው ሕንድ «አረንጓዴው አብዮት» ተብሎ የሚታወቀውን የግብርና ምርታማነት ተጠቅማ ራሷን በምግብ እህል ራሳቸውን ከቻሉ አገራት የመጀመሪያ ተርታ አሰልፋለች:: እንደ «ስዩመ እግዚአብሄር» ይቆጠሩ የነበሩ መሪዎች ፈላጭ  ቆራጭነት ዛሬ ታሪክ እየሆነ ሄዷል:: ሕዝቡን የሚፈራ መንግስት ተፈጥሯል:: ህጎችና ፖሊሲዎች ተረቅቀው እስኪፀድቁ ድረስ ከፍተኛ ውይይት ይካሄድባቸዋል:: «ሕዝቡ ምን ይለናል?» በሚል ሞራላዊ ተጠየቅ ፖሊሲዎች ይፈተሻሉ፣ ይከለሳሉ፣ ይሻሻላሉ:: በቅርቡ በዓለም ላይ የተከሰቱትን የፋይናንስ ቀውስ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት ማሽቆልቆል እና የዋጋ ግሽበት ተከትሎ በርካታ አገራት ይበጃል ያሉትን እርምጃ ሲወስዱ አሁንም ህንድ ቆም ብላ የውሳኔዎቹ አንድመታ የሚያስከትለውን መዘዝ «ህዝቡ ምን ይላል?» በሚል እሳቤ መርምራለች:: አንድ ተጠቃሽ ነገር በነዳጅ ዘይት ድጎማ ማንሳት ላይ የተያዘው አቋም ነው:: አብዛኞቹ አገራት ድጎማውን ማንሳታቸውን ሲገልፁ በህንድ እንደ ፌዴሬሽን ም/ቤት የሚያገለግለው «ራጂያ ሳብሃ» ድጎማው ቢነሳ የሚከተለውን የፖለቲካ ቀውስና የዋጋ ግሽበት መርምሮ ድጎማው እንዲቀጥል ወስኗል:: ሌሎች አንፀባራቂ ተሞክሮዎች በማንሳት ህንድን ማወደስ ይቻላል:: የውዳሴዎቹ መሰረት የሆነው ግን አገሪቱ እየተከተለችው ባለው ፖለቲካዊ አቋም የዜጎች ባህላዊና ሞራላዊ እሴቶች በእጅጉ እየተጠበቁ ነው፣ ኢኮኖሚውን የሚነኩ ፖሊሲዎችና ህጎች የሚኖራቸው ውጤትና ሊያስከትሉ የሚችሉት ፖለቲካዊ ሁነት ጥናት ሳይደረግበት አይተገበርም፣ ወዘተ::

«የሀበሻ ቀጠሮ» የሚል ጭማሮ ካልተደረገለት በስተቀር ክቡር ሚ/ሩ መግለጫውን ይሰጣሉ ተብሎ የሚጠበቀው (የተባለው) 3.00 ሰዓት ላይ በመሆኑ ወደዚያው የሚያዳርስ ታክሲ መጠባበቁን ተያያዝኩት:: ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎች ተደርድረዋል:: በሙሉ የሚጠሩት ግን አንድ መስመርን መርጠው ብቻ ነው:: «ተራ አስከባሪዎች» የሚባሉ አሉ:: - ታክሲዎች እየሞሉ ሲሄዱ «የተራ» በሚል ከሚቀበሏት ሳንቲም ውጪ ለሚጉላሉት ዜጎች ግድ አይሰጣቸውም:: እንዴት ተቋቋሙ? ለምን ተቋቋሙ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል::

የትራንስፖርቱ ዘርፍ በዘፈቀደ ሲሰራ «ህዝቡ ምን ይለናል?» በሚል ተጠየቅ አሰራሩን የሚገመግም፣ ችግሩን የሚፈታ ወገንስ የለም? ያስብላል:: «የቀጣና ስምሪት ተጀምሮ ታሪኩ ተረት ይሆናል» እየተባለ የሚፎከረውስ እስከመቼ ይሆን? እንዲህ እያለ፣ እየተጉላላ፣ እንደእጣ በሚቆጠር ሁኔታ ታክሲ አግኝቶ የተሳፈረ ደግሞ ወዲያው የሚገጥመው ያልተጠበቀ ሁኔታ አለ::

«ታሪፍ ጨምሯል» ይባላል:: በየስንት ጊዜው? ድጎማው እንኳ ቢቀር በየ15 ቀኑ? ምናልባት ወደፊት በየሳምንቱ? በየቀኑ? እንዲህ ላለማለት ዋስትና የሚሆን ነገር የለም:: ረቡዕ ማለዳ ማለትም ጥቅምት 19 ቀን 2002 ዓ.ም በመንግስት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዩች ጽ/ቤት ክቡር አቶ በረከት በሚሰጡት መግለጫ ላይ ለመገኘት ሳቀና የሕንድ «ሕዝቡ ምን ይለናል?» ስለሚለው አንፀባራቂ ተሞክሮ በአንክሮ ማብሰልሰል የያዝኩትም ለዚህ ነበር:: በመልካም ነገር ደግሞ የድጎማው መነሳት ጉዳይ ለሚ/ሩ ቀርቦላቸው:: የሚ/ሩን ምላሽ በኋላ ላይ እንመለስበታለን:: ከዚያ በፊት አንዳንድ ሰበር ክንውኖችን እንመልከት::

## ለአይ ኤም ኤፍ የተላከው ጦማር

የገንዘብና ኢኮኖሚክ ልማት ሚ/ር የሆኑት አቶ ሶፍያን አህመድ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ የሆኑት አቶ ተክለወልድ አጥናፉ 2008 ላይ ለአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በፃፉት ጦማር መንግስት ሲያደርገው የቆየውን ለነዳጅ ዘይት የሚደረግ ድጎማ ማንሳቱን ገልፀዋል:: ምክንያቱ አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ተቀምጧል:: አገሪቷ ያሰሉባትን እዳዎች በዋንኛነትም ለነዳጅ ድጎማ በሚል የወጣችውን ለመቀነስ የተወሰደ እርምጃ መሆኑ ተጠቅሷል:: ድጎማው እስከሚነሳበት ጊዜ ድረስም መንግስት እስከ 2008 ሰባት ቢሊዮን ብር መደጎሙ ተወስቷል:: ይህ እርምጃ በመላው ዓለም የሚገኙ በርካታ አገራት ድጎማ ሲያደርጉ የኖሩትና እያደረጉ ያለው ለምን ነበር ወይም ነው? ኢትዮጵያ ራሷ ድጎማውን ስታነሳ ቀደም ሲል ድጎማውን ለማድረግ አስገዳጅ የነበሩት ሁኔታዎች ተነስተዋል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች በጠራ መንገድ መመለስ አለባቸው::

## ድጐማ ለምን?

የኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ አገራት በጣም መሰረታዊ በሚባሉ ፍጆታዎች ላይ ድጎማ ያደርጋሉ:: በዋንኛነትም የነዳጅ ዘይት፣ የምግብ እህሎች መድሃኒትና ማዳበሪያን የመሳሰሉት ይገኙበታል:: በእነዚህ መሰረታዊ ፍጆታዎች ላይ የሚደረገው ድጎማ ዋንኛ ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደው /እንደየአገራቱ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ/ በቅንጦት እቃዎች፣ በአልኮል መጠጦች፣ በትንባሆ ውጤቶችና በመሳሰሉት ላይ ከፍተኛ ግብር /እስከ 90 በመቶ/ በመጣል ነው::

ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ፍጆታዎች በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን /አብዛኛውን የሕዝብ ክፍል ዜጎች ሕይወት በቀጥታ የሚነካ ነው:: በመግቢያችን ላይ የጠቀስናት ህንድ የነዳጅ ድጎማን ማንሳት የፈጠረውን «ህዝብ ምን

ይለናል?» አንድምታ አስመልክቶ የምጣኔ ሃብት ባለሙያና «ሎክ ሳብሃ» ተብሎ የሚታወቀው ፓርላማ አባል የሆኑ ተወካይ ሁኔታውን ያብራሩበት መንገድ በምሳሌነት ይጠቀሳል:: «ህንድ በህዝብ ቁጥር በአለማችን በሁለተኛ ደረጃ ትገኛለች:: ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግብር የሚጣልባቸውን ሸቀጦችም የመጠቀም ልምድ አለ:: የነዳጅ ድጎማ ቢነሳ በእያንዳንዱ የሸቀጥ ምርት ላይ ጭማሪ ስለሚኖርና ይህም ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከኢኮኖሚው (ከህዝቡ) ላይ ገንዘብ ስለሚሰበስብ ግሽበት ይከሰታል:: ግሽበቱ ከሚያስከትለው ቀውስ ከኢኮኖሚው ላይ ወጭ የሚደረገው ድጎማ ይሻላል::» ብለዋል::

የኢትዮጵያ መንግስት ድጎማውን ከማንሳቱ ቀደም ሲል በነበረው አንድ አመት ሰባት ቢሊዩን ብር ማውጣቱ የተገለፀ ሲሆን እንደ ኢንዶኔዢያ ያሉ አገራት ደግሞ እስከ 15 ቢሊዮን ዶላር ይመድባሉ:: ከላይ በተመለከትነው መንገድ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ከአፍሪካ የሁለተኛነት ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የነዳጅ ዋጋ መጨመርን ተከትሎ በዘፈቀደ በሚደረጉ የአገልግሎትና የሸቀጥ ዋጋ ጭማሪዎች ላይ ያለው የመከላከል አቅምና ስልት ደካማ ነው:: በኢ-ፍትሃዊ የአገልግሎትና ሸቀጥ ዋጋ ጭማሪ በተደጋጋሚ በግሽበት የተመታንበት ሁኔታ ሲኖር ድጎማው የሚያስከፍለንና በኢ-ፍትሃዊ የገበያ ስርአት ከህዝቡ በሚሰበሰበው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ማጤን ያስፈልጋል:: የኢኮኖሚ እድገት ሁኔታም እዚህ ላይ ሳይነሳ አያልፍም::

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ኢኮኖሚያቸው በማደግ ላይ ያለና የበለፀጉ አገራት ሕዝቦች የኢኮኖሚ ለውጡን ተከትሎ ከፍተኛ ግብር የሚጣልባቸውን ሸቀጦች የመገልገል ሁኔታ ስላለ በየጊዜው የሚዋልለውንና የሚያሻቅበውን የነዳጅ ዋጋ ተከትሎ በሚፈጠረው ግሽበት አይነኩም:: በከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ ያሉት ዜጎች ሸክሙን የሚሸከሙትና ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል እፎይታ የሚያገኝበት የኢኮኖሚ ስርአት አለ:: ወደአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ተመልሰን ኢህአዴግ ለተከታታይ አመታት ስለመመዝገቡ የሚያበስረን እድገትም ከዚህ እሳቤ የዘለለ አይደለም:: የኢኮኖሚ ፖሊሲውን ተከትሎ በማካሄድ ኢንቨስትመንቶችና ግብይቶች የላይኛው የሕብረተሰብ ክፍል ስኬትና የአብዛኛው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ሕዝብ ስነ ምጣኔያዊ መስተጋብር በኢኮኖሚያዊ ህጎችና ጥናቶች ጥላ ስር የሚወድቅ መሆን አለበት:: ለአመታት የተደረጉት ድጋፎች ትርጉም ባለሙ መንገድ መነሳት በሚያስፈልጋቸው ጊዜና ሁኔታ ላይ መገኘታችንን የሚያረጋግጥ መሠረት የለም::

እንመለስበታለን ወዳልነው የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትሩ መግለጫ እናምራ:: የዋጋ ክለሳው የጊዜ ስሌት ገበያውን የተከተለ ብቻ እንደሚሆን አቶ በረከት ስምኦን በጥቅምት 19ኙ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አስታውቀዋል:: የአለም አቀፉን የዋጋ ተመን ተከትሎ (ገበያ መር) ይቀጥላል ብለዋል:: ደረጃ በደረጃ ሲደረግ የቆየው የድጎማ ማንሳት እንዳበቃለት የገለፁበት አጋጣሚ ነው:: ለድጎማው መደረግ ምክንያት የነበሩት

ሁኔታዎች ተወግደዋል ወይ/ የግብር አሰባሰቡ በአዲስ መልክ በጀመረበትና በዚህም በአንፃራዊ ሁኔታ የመንግስት ገቢ ጨምሮ አያለ የተወሰደው እርምጃ መሰረቱ ምንድን ነው? የነዳጅ ዋጋው ገበያ መር ይሁን ስንል ካለው በየእለቱ የማሻቀብ ሁኔታ አንፃር የዋጋ አከላለሱ ከሶስት ወር ወደ አንድ ወር በቅርቡም በ15 ቀን እየተተገበረ በኢ-ፍትሃዊነት በዜጎች ላይ የሚቆለለውን የዋጋ ጭማሪ የምንቆጣጠርበት ዘዴ የታል? እና የመሳሰሉት::

በሳንቲሞች የነዳጅ ዘይት ዋጋ ጭማሪ የተነሳ በብዙ እጥፍ በሚንረው የሸቀጦች ዋጋ የልተነካ የሕብረተሰብ ክፍል አለ ቢባል ምላሹ «የላይኛው» የሚል ብቻ ይሆናል:: «እንዴት ነው ነገሩ?» ከሚለው ይልቅ የነዳጅ ማደያዎችን የሚያጣብበው ይበዛል:: ክለሳው የዋጋ ብቻ ሳይሆን የአቋምም መሆን እንዳለበት ሊታወስ ይገባል:: የሚኒስትሮች ም/ቤት የነዳጅ ዋጋ የመተመን ስልጣንን ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር የሰጠ ሲሆን የውሳኔው ውጤት የሚያስከትላቸውን ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች መርምሮ ማሻሻያዎችን የማያደርግ ከሆነ የዋጋ ግሸበቱ ያልተጠበቁ ክፍያዎችን ሊያስከፍል ይችላል:: እንደ 50 በመቶ ድጎማ አይነት አማራጮች እንኳ የራሳቸውን ገበያውን የማረጋጋት አቅም አላቸው:: እንደሚታወቀው ሁሉ ኬሮሲንን በስፋት እየተጠቀምን ነው:: ኬሮሲንን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች እየመጡ ሲሆን አሁን ከሚደረገው በላይ መጠኑን ጨምሮ የመቀላቀል እድልም አለ:: ከዚህ በተጨማሪም አሁን ያለው የነዳጅ ዋጋ ቀደም ሲል ከነበረው ከ90 በመቶ በላይ ቀንሷል:: በዓለም ላይ በተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ፣ በዋጋ ግሸበትና በአገራችን አጋጥሞ የነበረውን የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ተከትሎ ከተዘጉና ከከሰሩ ድርጅቶች የተቀነሱ፣ እንዲሁም የምግብ እህል እርዳታ የሚጠብቁ ዜጎች እጣ ምን ሊሆን ይችላል?

# እርቅን የሚጠሉ ከጸብ የሚያተርፉ ናቸው

**በታምራት ታረቀኝ**

ጊዜው 1996 ዓም ነው:: በግዮን ሆቴል ለተከሄደው የሠላምና ዕርቅ ሀገራዊ ጉባኤ ድጋፍ ለመስጠት እና ኢህአዴግን ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ለመጠየቅ በመስቀል አደባባይ በተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተናል:: «ክፈት በለው በሩን የሰላሙን» እየተባለ ይዘመራል ይጨፈራል:: ለዚህ ዋና ምክንያቱ ደግሞ «ሰላም በሰፈነበትና የተጣላ በሌለበት የሰላምና የዕርቅ ጉባዔ» በማለት ከኢህአዴግ ሰፈር የተሰጠው ምላሽ ነበር::

ከአጠገባችን የተቀመጡ አንድ አዛውንት «እንዴት ዕርቅ ይጠላል» በማለት በቁጭት ይናገራሉ:: በዚሁ አባባላቸው ተስበን ከእሳቸው ጋር ጨዋታ ጀመርን:: ይህች ሀገራችን ተጠይቀው አይደለም ራሳቸው ጠይቀው የሚታረቁ መሪዎች ነበሯት:: እረኛ ምን አለ

ብለው ጠይቀው አጠያይቀው መፍትሄ የሚፈልጉ ፈሪሐ እግዚአብሔር የነበራቸው መሪዎችም ነበሩ፡፡ መቼም የተጻፈ አንብባችሁ ይህን ሳታውቁ አትቀሩም አሉን፡፡ አዎንታችንን ገልጸንላቸው ወጋቸውን ለማዳመጥ ያለንን ጉጉት በገጻችን አሳየናቸው፡፡ ስለ ወሎው ንጉስ ሚከኤል ሰምታችኋል አሉና ቀጠሉ፡፡ ንጉሡ በግዛታቸው ወረሂመኖ አውራጃ የሚኖር ገበሬ ያቅራራባቸዋል ማለትም ለጠብ ይከጅላቸዋል፡፡ ባለሟሎቻቸው ይህን ቢሰሙም ንቀው አልነገሯቸውም፡፡ ታዲያ ተደብቆ የሚቀር ነገር የለምና ወሬው ንጉሡ ዘንዳ ሲደርስ ባለሟሎቻቸውን ሁሉ ይሰበስቡና «አንድ ገበሬ እንዳቅራራብኝ ሳትሰሙት የቀራችሁ አይመስለኝም ምን ትመክሩኛላችሁ» በማለት ይጠይቃሉ፡፡

የመጀመሪው ተናጋሪም ሁሉም መስማታቸውን ያረጋግጥና «ንጉስ አንድ ገበሬ አቅራራ ብለው እንደ ምን ይጨነቃሉ፡፡ እረ አርፈው ይቀመጡ፡፡ አንድ መናጢ ገበሬ ምን ሊያመጣ ብለው ነው ይላል፡፡» በተከፈተ ቦይ መፍሰስ የተለመደ ነውና የሁሉም መልስ ተመሳሳይ ይሆናል፡፡ በነገሩ የተገረሙት ንጉሥ ሚከኤልም «በቃ ይሄ ነው ምክራችሁ፡፡ ይሄ ገበሬ ሌላ ማድረግ ባይችል እንደምንም ተሹለክልኮ መጥቶ ይህችን ቤቴን ቢያቃጥላት የንጉሥ ሚካኤል ቤት የተቃጠለ ጊዜ እያላችሁ የዘመን ማስሊያና የልጆቻችሁ እድሜ መቁጠሪያ ልታደርጉኝ ነው፡፡ በምክራችሁ አልስማማም፡፡ ያንን ገበሬ ፈልጋችሁ አምጡልኝ እኔ እታረቀዋለሁ» አሉ፡፡ ፈጸሙትም በማለት ነበር አዛውንቱ ያወጉን፡፡

አቶ መለስ ፓርላማ ቀርበው ከኦብነግ አመራር ጋር እርቅ ለማውረድ በግላቸው ሳይቀር ምን ያህል እንደ ደከሙ ሲናገሩ ሰምተናል፡፡ ለእሳቸው መንግስት የሚቀርብን የዕርቅ ጥያቄ ግን ሲያጣጥሉና እንከን ሲያወጡለት እንጂ ሲቀበሉ አላየንም አልሰማንም፡፡ ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም በእነ ፕ/ር መስፍን አማካኝነት ለቀረበላቸው የሰላምና የእርቅ ጥያቄ «የባልና ሚስት ጉዳይ አይደለም» ብለው አናንቀው ነው ሀገሪቱን ለውርደት ራሳቸውን ለስደት የዳረጉት፡፡

ተቀዋሚዎችም ኢህአዴግ የእርቅ ፍላጎት የለውም፡ ለዕርቅ ዝግጁ አይደለም እያሉ እየወቀሱ እነርሱ በሚመሩት ፓርቲ ውስጥ ችግር ተፈጥሮ ተወያዩ፡ ችግሩን በዕርቅ ፍቱት ሲባሉ እነርሱም እንደ አቅሚቲ የተቀመጡባት ወንበር ሥልጣን ሆኖ ጥያቄውን ያናንቃሉ አቃቂር ያወጡለታል፡፡ በሀሳብ የተለዩዋቸውን ብቻ ሳይሆን ተነጋገሩ ብለው የሚጠይቋቸውንም ሆነ ሽማግሌ ሆነው ሊያስታርቁ እላይ ታች የሚሉትን ሳይቀር ይፈርጇቸዋል፡፡ በሀሰት ይወነጅሏቸዋል፡፡ ይህም አድራጎት በሁሉም ቤት የተሰበሰቡት ባለሟሎች (አማካሪዎች) በንጉሥ ሚካኤል ቤተ መንግሥት የነበሩት አይነት መሆናቸውን ነው የሚያስገነዝበን፡፡

ከ1889--1974 እንደኖረ የሚነገርለትና በአንድ ሀገር አመራር ውስጥ የተቀናቃኝ የፖለቲከ ድርጅቶች ተቀውሞ አስፈላጊነትን አበክረው ከአሳሰቡት ዕውቅ ሰዎች አንዱ የሆነው ዋልተር ሊፕማን «ቀዳማዊ ናፖሊዎንና ሳልሳዊ ናፖሊዎን ሊጠገን የማይችል ስህተት የፈጸሙት እነሱ (መሪዎቹ) የተናገሩት ሁሉ ትክክል ነው በሚሉ ሰዎቻቸው ነው» ማለቱ ተጽፎለታል:: እነርሱ እንደ ንጉስ ሚካኤል መሆን ባለመቻላቸውም ብለን ልናክልበት እንችላለን:: ወይ ጥሩ መካሪ ወይ እንደንጉሥ ሚካኤል ጥሩ አሳቢ መሆን ያልታደሉ በየትኛ ውም የኃላፊነት ቦታ ላይ የሚገኙ ሰዎች መጨረሻቸው ውድቀት ነው::

ያለፈን አስታውሶ ትንሽ ሀሳብ ለመሰንዘር መነሻ የሆነኝ ሰሞነኛው የአንድነት ፓርቲ ጉዳይ ነው::ችግር አለ:አመራሩ በስልጣን እየባለገ ነው የፓርቲ ደንብ እየተጣሰ የፖለቲከ ውሳኔ እየነገሰ ነው የሚሉት ወገኖች ይሄው ችግር በውይይት ሊፈታ: በመነጋገር ሊስተከከል እንደሚችል ሲገልጹ :ከፓርቲው ወንበር ላይ የተቀመጡት ግን የምን ውይይት በማለት አሻፈረኝ ብለዋል:: ተነጋገሩ በማለት በጨዋ ደንብ የጠየቋቸውንም «ወያኔዎች ናቸው» ሲሉ ጥረታቸውንም የሴራ ሽምግልና ብለውታል:: የአንድነት ችግር በውይይት እንዲፈታ የሚሻ ይህም መሻቱ እውን ሆኖ ለማየት እንዲበቃ ፊርማውን አኑሮ ጥያቄ የሚያቀርብ «ወያኔ» ከተገኘ በእውነት ሀገራችን ተለውጣለች ማለት ነው::

አንድነት ጥቂት በማይባሉ ሰዎች ዘንድ የማይወደድበትና የማይፈለግበት ቢያንስ ሶስት ምክንያቶች አሉ:: የቅንጅት ወራሽ መሆኑ: ሕብረ ብሄራዊ አደረጃጀትና ዓላማ ያለው መሆኑ:አንድነት የሚል መጠሪያ መያዙ:: በመሆኑም ችግሮችን በውይይት ፈትቶ በመነጋገር መቻቻል አስፍኖ ተጠናክሮ እንዲወጣ ስለማይፈለግ የንጉሥ ሚከኤል ባለሚሎችን አይነት ምክር የሚሰጡ ሰዎች በአመራሩ ዙሪያ ተኮልኩለዋል:: የምን ውይይት ነው: ከእነርሱ ጋር ደግሞ ንግግር ከማለት አልፈው አመራሩ በሚወስደው ርምጃ አበጀህ በርታ እያሉት ነው:: እንደውም አንዳንዶቹ አንሷል ይጨመር  የሚል መልዕክት እያስተላለፉ ነው:: የአንድነት አመራሮች ወይ ደግ መካሪ ባለማግኘታቸው ወይ እንደ ንጉሥ ሚከኤል የምትመክሩን መልካም አይደለም ብለው ራሳቸው ወደ መልከሙ ጎዳና መግባት የሚያስችል ማስተዋል በማጣታቸው አንድነት በእጅጉ እየተጎዳ ነው::

በአንድነት ውስጥ ውይይት ባህል ቢሆን: የችግር መፍቻው ዋናው መሳሪያ መነጋገር ቢሆን መቻ ቻል ቢዳብር የህግ የበላይነት ተከብሮ ተጠያቂነት ያለው አሰራር ቢሰፍን የሚጎዱ ሰዎች አሉ:: ምክ ንያት እነዚህ አንድነትን የሚያጠናክሩ ናቸውና:: ስለሆነም እነዚህ ሰዎች የሚያተርፉት ከጸብ እንጂ ከእርቅ አይደለምና አንድነት ውስጥ የተፈጠረው ችግር እንዲባባስ መተማመን ጠፍቶ አባሉ ሁሉ የጎሪጥ እንዲተያይ አጥብቀው እየሰሩ ነው:: «በየሆቴሉ እየተሰበሰቡ ፓርቲያችሁን ሊያፈርሱ የሚን ቀሳቀሱ ወጣቶች አሉና ተጠንቀቃችሁ

ፓርቲያችሁን ጠብቁ»ተብሎ በአባላት ስብሰባ ላይ በአደባባይ በዶ/ር ያዕቆብ የተነገረውና በውስጣችን ያሉ ባዕድ አከላት በሚል አቶ አስራት ጣሴ በአውራ አምባ ታይምስ ጋዜጣ የተናገሩት ነው በአባላት መከከል የመጀመሪያውን መጠራጠር የፈጠረው።ዛሬ አን ድነት ውስጥ አመራሮቹ ሊሰሙት ከሚፈልጉት ውጪ ደፍሮ የሚናገር ከተገኘ ርዝራዥ ይባላል። አመራሩን ደግፎ ከልተናገረ ደግሞ ከየትኛው ወገን ነህ ተብሎ ይጠየቃል። ቆም ብሎ ለማስተዋል ጊዜ፡ ሰከን ብሎ ነገሮችን ለመመርመር ትግስት ጠፍቶ ነገሮች ሁሉ በከአፈርኩ አይመልሰኝ ስሜ ትና በእብሪት እየተፈፀመከ እለት እለት ችግሮቹ እየተባባ ነው።

22 ሰዎች ናቸው የሚቃወሙን በማለት አዋሳ መድረክ ላይ የተናገሩት ኢ.ር ግዛቸውም 141 ሰዎች ተፈራርመው ተነጋገሩ በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው «ወያኔዎች» ናቸው አሉ። በዙሪያቸው ያሉ ባለሚሎቻቸውም አበጀህ ልክ ነህ አሏቸው።ንግግራቸውን ደግፈው አበጀህ ያሏቸው ሰዎች ወሬውን ነገሯቸው እንጂ መረጃ ሊያቀርቡላቸው ስላልቻሉ ኢ/ሩ ለሀፍረት ተዳረጉና ወያኔ ያሉዋቸውን ሰዎች መዋጮ ስላልከፈሉ አባል አይደሉም የሚል ሌላ ሰበብ አመጡ ።ማን በማን ላይ ይከሰሳል ተብሎ እንጂ ፍ/ቤት ቢቀርቡ ደግሞ ቅሌታቸውን ይከናነቡ ነበር። አንድነትን ተጠናክሮ ማየት የማይሹ ሰዎች «ጅብን ሲወጉ በአህያ ተከልሎ» እንዲሉ በእነ ኢ/ር ግዛቸው ተከልለው መልከም መካሪና ለአንድነት ተቆርቋሪ መስለው በመቅረብ አንድነትን እየገደሉት ነው። ኢ/ር ግዛቸው ደግሞ ሁለተኛ ሰው ሆኖ አንድነትን መምራት ከመጀመሪያውም ያልተቀበሉት ነበርና እርሳቸው መሪ ተብለው የማይጠሩበት ፓርቲ ተጠናክሮ ማየት የሚሹ አይመስሉም። አንድነት በምን አይነት አማካሪዎች እንደተከበበና አመራሩም በየራሱ መንገድ እየሄደ መሆኑን በየዕለቱ አንዱ የሚናገረውን ሌላው በማስተባበል ሥራ መጠመዳቸው ከበቂ በላይ ያሳያል። ዛሬ የተናገሩትን ነገ መች አልኩና ማለትም የተለመደ ሆኗል።

አጉል መከሪ ወደ ገደል ገፍቶ ከአፋፍ ሆኖ ይስቃል እንጂ አስቀድሞ ለማዳንም ሆነ ኋላ ከገደል ለማውጣት አይታትርም። የሚያተርፈው ከጸብ ነውና የእርቅ መንገዶችን ሁሉ በመዝጋት የዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል አይነት ተግባር ነው የሚፈጽመው። በፓርቲው መሪ ላይ ተደጋጋሚ ክህ ደት ሲፈጸም አበጃችሁ፡ የሥነ ሥርዓት መመሪያ ሲሰረዝና ሲለወጥ ግፋበት፡ የአንድነት መሰረታዊ ዓላማዎች ሲሸረሸሩ ትክክል፡ አባላት ሲባረሩ ሲያንስ ነው የሚሉ መከሪዎችን ለአንድነት በጎ የሚ ያስቡ ናቸው የሚል ጤነኛ አእምሮ አይኖርም።

ታላቁ መጽሀፍም«ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች እያሳቱና እየሳቱ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ» ይላል፡ (2ጢሞቲዎስ 3.13)

# ብርቱካን በቃሊቲ

## ኢ/ር ኃይሉና አቶ መለስ በሸራተን!

በግርማ ካሳ (ቺካጎ)

ትዝ ይለኛል ከሁለት አመታት በፊት ከአንድ ኢህአዴግን ከማደግፍ ወዳጄ ጋር የተነጋገርኩት:: የቅንጅት መሪዎች ከእስር ቤት ተፈተዋል:: ወደ ሁለተኛው ሚሊየንም ለመሸጋገር እየተዘጋጀን ነው: አቶ መለስ ዜናዊ፣ ኢንጂነር ኃይሉ ሻወል፣ ወ/ት ብረቱካን ሚደቅሳ፣ አቶ ስዩም መስፍን ... ሁሉም በአንድ ላይ ጎን ለጎን ቆመው፣ እንደ ወንድማማቾች፣ ለኢትዮጵያ ሕዘብ የሰላም፣ የፍቅር፣ የእርቅና የአንድነት መልእክት በቴሌቭዥን ቢያሰሙን በጣም ጥሩ ይሆን እንደነበር ለዚሁ ወዳጄ ገልጩለት ነበር::

በነሐሴ 2000 ዓ.ም «እኔም ሕልም አለኝ» በሚለውና አውራምባ ታይምስ ላይ በታተመው ጽሁፌ «እኔም ሕልም አለኝ፣ አቶ መለስ ዜናዊ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ አቶ ኃይሉ ሻወል፣ አቶ ልደቱ አያሌው፣ አቶ ገብሩ አስራት... እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ መሪዎች ወደ ልቦናቸው ተመልሰው፣ እንደ አንድ አገር ልጆች፣ እንደ አንድ ቤተሰብ እንደሚነጋገሩና ካለንበት የፖለቲካ እሽክርክሪት ቀውስ እንደምንላቀቅ» በማለት የፖለቲካ መሪዎቻችን መቀራረብና መከባበር በአገራችን ትልቅ ምእራፍ እንደሚከፍት ለማሳየትም ሞክሬ ነበር::

ጥቅምት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሼራተን ሆቴል በአቶ መለስ ዜናዊና በአቶ ኃይሉ ሻወል መካከል የተደረገው መጨባበጥ «በኢሕአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል መቀራረብ መኖር አለበት:: መነጋገር ያስፈልጋል» ብለን እንከራከር ለነበርነው ዜጎች ትልቅ ደስታ ሊፈጥር እንደሚችል መቼም አንዳንዶች የላይ ላዩን በማየት ሊገምቱ ይችላሉ ብዬ አስባለሁ::

ነገር ግን እየሆነ ያለውን በጥልቀት ለሚከታተል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የዚህን እንደ ትልቅ ታሪካና ጠቃሚ ክስተት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባው የነበረውን የሼራተኑ ዜና፣ የሸፈነ አንድ ትልቅ ጋሬጣ እንዳለ መረዳቱ አይቀርም:: ይህንን ጋሬጣ አቶ ኃይሉ ሻወልም ሆነ አቶ መለስ ዜናዊ ብዙ ቦታ የሰጡት አይመስለኝም::

«ጠጅ በብርሌ፣ ነገር በምሳሌ» እንደሚባል ምሳሌ በማቅረብ ሃሳቤን የበለጠ ለማብራራትና ለማስፋት እንደሚከተለው እሞክራለሁ::

አንድ ሰው የዶሮ ወጥ በጣም ይወዳል:: በአንድ ምግብ ቤት በኩል ሲያልፍ የቀይ ወጥ ሽታ አፍንጫውን አወደው:: በቀጥታ ወደ ምግብ ቤቱ ገባ:: «አንድ እንጀራ በዶሮ ወጥ ከአንድ ጣሳ ውሃ ጋር አቅርቢልኝ የኔ እህት» ብሎ አስተናጋጇን በትህትና አዘዘ:: ምራቁን እየዋጠ ነው:: ትንሽ እንደቆየ ሰፋ ባለ ትሪ ምን የመሰለ ዶሮ ወጥ ከአንድ እንቁላልና ከአንድ ፈረሰኛ ጋር ቀረበለት:: ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተነሳ::

ወደ ሽንት ቤት ሄዶ እጅን ታጠበ:: እንደተመለሰም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ብሎ ምግቡን ባረከ:: አንድ ሁለት ጉርሻ እንደጎረሰ ቀና ብሎ አይኑን አፈጠጠ:: ሁለት አይን የሚያክሉ ዝንቦች በወጡ ውስጥ ቁጭ ብለዋል:: ሊያስመልሰው ሆነ:: እጁን ወደ ታጠበበት ሽንት ቤት እየቸኮለ ሄደ:: የጎረሰውን እንዳለ አስወጣው:: አስመለሰው::

ይህ በነ አቶ ኃይሉ ሻወልና በነአቶ መለስ ዜናዊ መካከል የታየው መጨባበጥና መፈራረም በጣም መልካም ነገር ነበር:: ከላይ እንደጠቀስኩት ሁላችንም የምንመኘውና የምንደግፈው፣ ከዚህ በፊት መሆን የነበረበት፣ ለአገር የሚበጅና የሰለጠነው ጥቅም ያለው ነበር:: ሰውዬው የዶሮ ወጡን ለመብላት እንዳስቸኮለውና እንደተመኘው ሁሉ፣ ያየነው መጨባበጥና መቀራረብ፣ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሊያስደስትና ሊያስፈነጥዝ የሚገባው ክስተት ነበረ:: በእርግጥ በኢትዮጵየ ታሪክ ውስጥ እንደ ትልቅ አዎንታዊ እርምጃ ሊወሰድ የሚገባው ነበር::

ነገር ግን «ነበር» ብቻ ሆኖ ቀረ:: መሆን አንደነበረበት ሊሆን አልቻለም:: አቶ መለስ ዜናዊና ኢ/ር ኃይሉ ሻውል ያቀረቡልን መዓድ ምንም እንኳን ሽታው የሚያውድና የሚጥም ቢመስልም፣ ልንመገበው አልቻልንም:: ቦታም አንሰጠውም:: አልተደነቅንበትም:: መጨባበጡና መፈራረሙ የተደረገበትን ቀን እንደ ታሪካዊ ቀንም አናየውም::

አስቡት ከአራት አመታት በፊት «እነ አቶ ኃይሉ ሻውል» በሚል ፋይል የተከሰሱ የቅንጅት መሪዎች በሙሉ፣ የእድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶባቸው ነበር:: አንደ አቶ መለስ ዜናዊ አባባል፣ የታሰሩት የቀድሞ ቅንጅት መሪዎች «ወንጀል» ፈጽመዋል:: (ወንጀል የሚለውን ቃል በቅንፍ ያደረኩት እንደ እውነቱ ከሆነ የቅንጅት መሪዎች አንዳች ወንጀል ፈጸሙ ብዬ ስለማላምን ነው) የነዚህ የቅንጅት አመራር አባላት ሊቀመንበር ደግሞ አቶ ኃይሉ ሻውል ነበሩ::

አቶ መለስ ዜናዊ የ«ወንጀለኞች» መሪ ከነበሩት ከአቶ ኃይሉ ሻውል ጋር በአንድ በኩል ሲጨባበጡና ሲሞጋገሱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአቶ ኃይሉ ሻውል ምክትል የነበረችዋን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን፣ የአቶ ኃይሉ ሻውል ምክትል ሆና በነበረበት ጊዜ ተሰራ በተባለ፣ አቶ ኃይሉ ሻውልም እራሳቸው አንዲፈረድባቸው ባደረገው «ወንጀል» ምክንያት፣ በግፍ ቃሊቲ እስር ቤት እንድትታሰር አድርገዋል:: ታዲያ ይህን የታዘበ ሰው፣ በእውኑ የተደረገው ስምምነት ቅንነት ያለው ስምምነት ነው ብሎ ሊያስበውና ትልቅ ግምት ሊሰጠው ይችላልን? ጆክና ቀልድ ነው ብሎ ቢያጣጥለው ያስደንቃልን?

የቅንጅት መሪዎች ይቅርታ ጠይቀው እንደተፈቱ በሰፊው ተዘግቧል:: ይቅርታ የጠየቁትም ተገደው በኃይል (Under duress) እንደሆነ አቶ ሀይሉ ሻውል በሬዲዮ አንድ ወቅት ተናግረውም እንደነበረ ሁላችንም የምናስታውሰው ነው:: ሌሎች በቃሊቲ እስር

ቤት ታስረው የተፈቱ የቀድሞ እስረኞችም በሽምግልና ወግና ስርዓት መሰረት ይቅርታ ጠይቀው እንደተፈቱ በግልጽ አስታውቀዋል።

እንግዲህ አቶ ኃይሉ ሻውልም ሆነ ሌሎች የቅንጅት መሪዎች ከተናገሩት የባሰ ወይንም የተለየ ነገር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ምን ብትናገር ነው ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር አቶ ኃይሉ ሻውል የ«ወርቅ መቀመጫ» ላይ እንዲቀመጡ ሲደረግ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በቃሊቲ ሌትና ቀን የምትማቀቀው?

አቶ መለስ ዜናዊ «የሕግ ጉዳይ ነው። ይቅርታ አልጠየኩም ብላለች» ይላሉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን የሽምግልና ስርዓትና ወግን መሰረት ያደረገ ይቅርታ እንደጠየቀች በጋዜጣ ላይ ለሕዝብ ይፋ አድርጋለች። ታዲያ በይፋ ይቅርታ የጠየቀችን እህት ይቅርታ አልጠየቀችም ብሎ ማሰቃየት ምን ይባላል? ሀቁና እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ፣ አንድ «ወንጀለኛ» እንደ ወዳጅ የሚታይበት፣ ሌላው «ወንጀለኛ» ደግሞ እሥር ቤት የሚማቅቅበትስ ምክንያቱ ምንድን ነው?

በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እንዳየነው በአቶ ኃይሉ ሻውልና በአቶ መለስ ዜናዊ መካከል የነበረውን መቀራረብ በመርህ ደረጃ አልቃወመውም። ከላይ እንደገለጽኩት መቼም ቢሆን ኢትዮጵያዊያን ልዩነቶቻችንን በኃይልና በጥይት ከመፍታት ይልቅ ቁጭ ብለን በንግግር ብንፈታ የሚመረጥ መንገድ ነው።

ነገር ግን ምንም ጥፋት ያላጠፋች፣ የአገሪቱን ሕግና ሥርዓት ጠብቃ ትንቀሳቀስ የነበረች፣ «ወያኔ ጠላት አይደለም» ብላ የነአቶ መለስ ዜናዊ ጠበቃ ሆና በአደባባይ የተከራከረች፣ እንደ አብዛኞቻችን በባእድ አገር ኑሮዋን አድርጋ በኢኮኖሚ የተመቻቸ ኑሮ መኖር ስትችል አገሬንና ሕዝቤን አገለግላለሁ ብላ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ለማድረግ የቆረጠች፣ በአገር ባህል ወግ መሰረት በሽምግልና ይቅርታ እንደጠየቀች በግልጽ በማስቀመጥ እውነቱን ያልካደች፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ጠንካራ አቋም ያላት፣ የሰላምና የፍትህ ደቀ መዝሙርና የመጀመሪያዋ የሴት ፖለቲካ መሪ የሆነችው ብርቱካን ሚደቅሳ ከሶስት መቶ ሰባት ቀናት በላይ በአሰቃቂው በቃሊቲ እስር ቤት በግፍ እየተሰቃየች ባለችበት ሁኔታ ነው የሼራተኑ ስምምነት ምንም ግፍ እዳልተደረገና ሁሉ ነገር ሰላም እንደሆነ ተደባብሶ ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት እንዳለ የተዘገበልን። በአገራችን የብዙሃን ፓርቲ ዲሞክራሲ አንድ እርምጃ ወደፊት እየሄደ እንደሆነ ነው የተሰበከልን።

ይህንን ልንቀበለው የማንችለውና የማይዋጥልን ነገር ነው። የተደከመበትን ያህል ዶሮ ወጡን ብንመገበው ደስ ይለን ነበር። ይቅርታ ያድርጉልንና ወጡ ውስጥ ግን ዝምብ ገብቶበታል።

አቶ ኃይሉ ሻውል ሊመጣባቸው የሚችለውን ትልቅ ተቃውሞ እያወቁም ደፍረው ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ለመጨባበጥ መድፈራቸው በአንድ በኩል የሚያስደንቅ ነው። በመንም አይነት መለኩ አቶ ሃይሉ ሻወል ከአቶ መለስ ጋር በመጨባበጣቸው

ሊያስወቅሳቸውና ሊያስነቅፋቸው አይገባም:: በዚህም ምክንያት እርሳቸውን በዚህ ጽሁፍ ላይ ልዘልፍ አልፈልግም:: አይገባምም::

ነገር ግን የርሳቸው ምክትል ሊቀመንበር የነበረችዋን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ በቃሊቱ እሥር ቤት በስቃይ እንዳለች እያወቁ፣ የርሷን ጉዳይ ወደ ጎን ማድረጋቸውና እርሷን መርሳታቸው አሳዝኖኛል:: ከአንድ ትልቅ አባት በጭራሽ አይጠበቅም ባይ ነኝ::

እንግዲህ የተሰራው ተሰርቷል:: የሆነው ሆኗል:: ትችቱንና ተቃውሞውን እዚህ ላይ ላቁምና ከአሁን በኋላ ምን እናድርግ ወደሚለው ልሂድ::

አሁንም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ጋር አብረው በጋራ የአገራችን ኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: በመሆኑም ይህ የአቶ ኃይሉ ሻውልና የአቶ መለስ ዜናዊ መቀራረብና ተፈረመ የተባለውም ሰነድ፣ በአሁኑ ወቅት ትልቅ ቦታ ባንሰጠውም፣ ከአሁን በኋላ ባለው ጉዞ ለሁላችንም በሚበጅ መልኩ፣ ከተቃና ትልቅ ጥቅም ሊያመጣ ይችላል ባይ ነኝ::

አቶ ኃይሉ ሻውል፣ ይህ ከነአቶመለስ ዜናዊ ጋረ ያደረጉትን ስምምነት ሕዝብ እንዲቀበለውና ለሕዝብ መሸጥ ከፈጉ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ እንድትፈታ አቶ መለስ ዜናዊን በግልጽ እንዲያነጋግሩና እንዲያሳምኑ ያስፈልጋል:: (አሁን ጓደኞሞች ስለሆኑ)

አቶ መለስ ዜናዊም ቢሆኑ በሼራተን እንደተናገሩት፣ በአገራችን የሚደረገው የ2002 ምርጫ ነጻ ፍትሃዊና ዲሞክራሰያዊ እንዲሆን ከፈለጉ፣ በርግጥ ድርጅታቸው ለዚህ ቁርጠኝነት ካለው በሥራ በተግባር ሊያሳዩን ዘንድ ይገባል:: ከአቶ ኃይሉ ሻውልና ከሌሎች ጋር የተደረገው ስምምነት የበለጠ ዳብሮ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል ስምምነት እንዲሆንና በሕዝብ የበለጠ ተቀባይነት አግኝቶም ውጤት እንዲያመጣ፣ ተጨባጭ ስራዎች በኢህአዴግ መሰራት አለባቸው:: ኢህአዴግም ተቃዋሚዎችንም ሁሉ የሚጠቅም ስምምነት እንዳይኖር ጋሬጣ የሆነውን ነገር መግፈፍ ያሰፈልጋል፡ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በአስቸኳይ መፈታት አለባት::

በርካታ የሕግ ምሁራን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች፣ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ የውጭ ዲፕሎማቶች፣ የኢህአዴግን አቋም በማንጸባረቅ የሚጽፉ የኢህአዴግ ደጋፊዎችም ሁሉ ሳይቀር (እነ አቶ ኃይማኖት ላቀው፣ አቶ ጌታቸው መኳንንት፣ አቶ ተስፋዬ ሃቢሶ፣ የሲቪሊቲ ፓልቶክ ክፍል ሃላፊው አቶ አባ መላ...) የብርቱካን ሚደቅሳ መፈታት ቁልፍና አፈላጊ እንደሆነ ከመምከር አልፈው እንድትፈታ ግፊት እያደረጉ ናቸው:: ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችበት የሕግ መከራከሪያ አጨቃጫቂና ግልጽነት የጎደለው አወዛጋቢ እንደሆነ መጠቆም፣ ሰብዓዊነትን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በአስቸኳይ ብርቱካን ሚደቅሳ መፈታት እንዳለባት አስገንዝበዋል::

ስለሆነም አቶ መለስ ዜናዊ በዚህ ጉዳይ ላይ አስቸኳይ ትኩረት ሰጥተውበት ወ/ት ብርቱካን ማደቅሳን በአስቸኳይ የምትፈታበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ በአክብሮች እጠይቃለሁ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በታሰረችበት ሁኔታ የሚደረግ ምርጫ ፈረንጆች ሊቀበሉት ቢችሉም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግን አይቀበለውም። ኢትዮጵያውያንም ይህንን ምርጫ አክብረው ይሳተፉታል ብሎ አይጠብቅም።

የሼራተኑን ስብሰባ የፈረሙ ተቃዋሚዎች የተባሉትም በምንም መልኩ ሕዝቡን እንደማይወክሉ መቼም አቶ መለስ ዜናዊ በሚገባ የሚያውቁት ይመስለኛል። የሕዝብ ድጋፍና ልብ ያለው ቃሊቲ በመሆኑ ከሕዝብ ጋር መታረቅ ከተፈለገ፣ ምርጫው ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ቁርጠኝነት ካለ ሥራው የሚጀምረው ብርቱካን ሚደቅሳን አሁን በመፍታት ነው፡

እግዚአብሄር ልቦና ለሁላችንም ይስጠን። አቶ መለስ ዜናዊ ከአቶ ኃይሉ ሻወል ጋር እንደተጨባበጡትም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጋር ቁጭ ብለው የሚወያዩበትንና የሚጨባበጡበትን ቀን ያሳየን!

# የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ሲዳሰስ

**በግዛው ለገሰ**

በ1980 ዓ.ም ሰንደቅ ዓላማን በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 3/1980፣ እንዲሁም ዓርማን በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 4/1980 የተሰኙ ሁለት የተለያዩ ሕጎች ተደንግገው የነበረ ሲሆን የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በ1987 መጽደቅን ተከትሎ በ1988 ሁለቱም በአዲስ ሕግ ተሽረዋል። ሁለቱን አዋጆች በግልጽ የሻረው ሕግ «የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ ቁጥር 16/1988» ይሰኛል። ይህ አዋጅ በ1989 በወጣው «የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 48/1989» አማካኝነት በሁለት አንቀጾቹ ላይ ማሻሻያ ተደርጐባቸዋል። /ማሻሻያው በክብ ሰማያዊ መደብ ላይ የተቀረፀው ብሔራዊ ዓርማ በሰንደቅ ዓላማው መሀከል ላይ የሚያርፈው የክቡ ዙሪያ የአረንጓዴውንና የቀዩን ቀለማት ቁመት አጋማሽ አካሎ መሆኑን የሚደነግግ ነበር።/

ሆኖም ከላይ የተጠቀሱት ሕጐች ያልሸፈኗቸው ጉዳዮችን ለመሸፈንና ዝርዝር ጉዳዮችንም ለመወሰን የሚያስችል፣ በአብዛኛው የቀደሙትን ሕጐች አጠቃልሎ የያዘ አዲስ አዋጅ ባለፈው ዓመት ፀደቀ። ነሐሴ 22 ቀን 2001 በነጋሪት ጋዜጣ የወጣው «የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001» አዳዲስና መሠረታዊ ጉዳዮችን አካትቶ የመጣ ቢሆንም በሻራቸው አዋጆች ውስጥ የነበሩትን አብዛኛዎቹን ድንጋጌዎች (ቃል በቃል ማለት ይቻላል) ደግሟቸዋል። ለምሳሌ ያክል፣ የሰንደቅ ዓላማ ምንነት፣ የሰንደቅ

ዓላማው ቀለማትና ቅርጽ፣ የሰነደቅ ዓላማው ቀለማት ትርጉም፣ እንዲሁም የዓርማው ትርጉም በአዲሱ አዋጅም ሆነ በተሻረው የ1988 አዋጅ ውስጥ የቃላት ልዩነት እንኳን የላቸውም:: ይሁንና አዲሱ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ አጠቃቀምን በተመለከተ ዝርዝር ሥነ-ሥርዓቶችን፣ የተከለከሉ ተግባራትንና ተያያዥ ቅጣቶቻቸውን የደነገገ ሲሆን በተሻረው አዋጅ በተለየ መልኩ የተገለጹና ያልነበሩ መሠረታዊ አንቀጾችንም ጨምሯል::

ይህ ፅሁፍ የተከለከሉ የባንዲራ አጠቃቀም ተግባራትን ለህብረተሰቡ የማሳወቅ ቀዳሚ ዓላማ ሲኖረው፣ በተወሰኑ የአዋጁ አንቀጾች ላይ ብቻ በማተኮርም ሊጠቀሱ የሚገባቸውን ጉዳዮች ይዳስሳል::

## የሰንደቅ ዓላማ ቀን

የሰንደቅ ዓላማ ቀን የአዲሱ አዋጅ ትውፊት ነው:: በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት በመላው ሀገሪቱ በየዓመቱ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ይከበር ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ተደንግጓል:: «ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን /ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን" እየተባለ የሚጠራ/ በየዓመቱ መስከረም ሁለተኛ ሳምንት ሰኞ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል::» ይላል አንቀጹ:: የዚህ አንቀጽ የአማርኛ ድንጋጌ የመስከረም ወር ሁለተኛ ሳምንት ውስጥ የሚገኘው ሰኞን የሚያመላክት ቢመስልም እንግሊዘኛውን ስንመለከት የመስከረም ወር ሁለተኛው ሰኞ ቀን ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን እንደሆነ እንገነዘባለን::

አዲሱን አዋጅ በመመርኮዝ በያዝነው ዓመት በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው የሰንደቅ ዓላማ ቀን በመስከረም 25 የተከበረ ቢሆንም አዋጁን የተከተለ ግን አልነበረም:: ምክንያቱም ከላይ ባስቀመጥነው አንቀጽ መሠረት፣ እንደ አማርኛው ድንጋጌ መስከረም 4 ወይም እንደ እንግሊዝኛው ድንጋጌ ደግሞ በመስከረም 11 የዚህ ዓመት የሰንደቅ ዓላማ ቀን ተከብሮ ሊውል ይገባ ነበር:: በርግጥ ሕጉ ከደነገገው ውጪ ስለመከበሩ የተሰጠ ምክንያት ነበር::

## ሰንደቅ ዓላማ እና አርማ

የኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ሰባተኛው እትም (2006) ሰንደቅ ዓላማ ወይም «Flag» በልዩ ቀለም (ቀለማት) የተዋቀረ የአንድ አገር ወይም ድርጅት ምልክት ወይም የሆነ ትርጉም ያለው ጨርቅ እንደሆነ ያስረዳናል:: በሌላ በኩል ይኸው መዝገበ ቃላት አርማ ወይም «Emblem» አንድ አገርን ወይም አንድ ድርጅትን የሚወክል ንድፍ ወይም ስዕል መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በምሳሌነትም አሜሪካ ብሔራዊ አርማዋ ንስር ስለመሆኑ ጠቅሷል::

የኢፌዴሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ለአዲሱ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅም ሆነ አዲሱ አዋጅ ለሻራቸው የ1988 እና የ1989 የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጆች መነሻዎች ናቸው:: ከሁለቱ የሕገመንግስቱ ድንጋጌዎች የመጀመሪያው፣ «የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሀል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሀሉ ብሔራዊ ዓርማ ይኖረዋል:: ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ::»

የሚል ነው:: ይህ ንዑስ አንቀጽ የኢትዮጵያ ባንዲራ ሦስቱ ቀለማትን የያዘ እንደሆነ ከነገረን በኋላ መሀሉ ላይ ግን ብሔራዊ ዓርማ እንደሚኖረው በግልጽ አስቀምጧል:: ድንጋጌው በአዲሱ አዋጅ  አማካኝነት መልስ የተሰጠበትን ጥያቄ ይፈጥራል - ኢትዮጵያ ዓርማው ያላረፈበት ሰንደቅ ዓላማ አላት?

ሁለተኛው የሕገመንግስቱ ድንጋጌ «ከሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ ይሆናል::» የሚል ሲሆን ተመሳሳዩን ጥያቄ እንድናንሰላስል ያደርገናል:: በዚህኛው ንዑስ አንቀጽ ላይ «ከሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ» የሚለው ሀረግ አርማ አንድ ነገር ሆኖ ሰንደቅ ዓላማ በሚባል ሌላ ነገር ላይ የሚቀመጥ መሆኑን ያመላክታል:: ከሁለቱም ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ እና አርማ አላት፤ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ::

## ክብ ሰማያዊ ቀለም (መደብ)

በአዲሱ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ በአንቀጽ 16 ላይ የኢፌዴሪ ሰንደቅ ዓላማ አንድ ዓይነት ብቻ ስለመሆኑ ተደንግጓል:: ይህ ሰንደቅ ዓላማ ምን ዓይነት እንደሆነ ከድንጋጌው እንመልከት:- «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ ከዚህ በላይ በተደነገጉት አንቀጾች መሠረት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይና ክብ ሰማያዊ ቀለማት ኖሮት በመሀከሉ በዚህ አዋጅ የተዘረዘረው ዓርማ ያለው ብቻ ነው::» ይህ የአዋጁ አንቀጽ «ክብ ሰማያዊ» ቀለም የአርማው አካል ሳይሆን የሰንደቅ ዓላማው አካል አድርጐ በማስቀመጡ ከራሱ ከአዋጁ አንቀጾች መካከል ቢያንስ ከአንቀጽ 7 እና 8 ጋር የሚጋጭ ከመሆኑም ባሻገር ከሕገመንግስቱ አንቀጽ 3 (1) ጋር ይጣረሳል::

የአዋጁ አንቀጽ 7 የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማት በመዘርዘር የቀለማቱን ትርጉም አስቀምጧል:: በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ሦስት ቀለማት ብቻ ተዘርዝረው ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል - አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ:: ይህ አንቀጽ ስለክብ ሰማያዊ ቀለም የሚያነሳው ባለመኖሩ የሰንደቅ ዓላማው አካል አለመሆኑን ይገልፃል:: እንዲሁም አንቀጽ 8 የዓርማውን ትርጓሜ ሲያብራራ የመጀመሪያው ንዑስ አንቀጽ «ክብ የሆነው ሰማያዊ መደብ ሰላምን ያመለክታል» ማለቱ ክብ ሰማያዊ ቀለም የዓርማው እንጂ የሰንደቅ ዓላማው አካል አለመሆኑን ይበልጥ ይገልፃል:: የሕገመንግስቱ አንቀጽ 3(1) በበኩሉ «የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሀል ቢጫ ከታች ቀይ ሆኖ በመሀሉ ብሔራዊ ዓርማ ይኖራል» በሚልበት ጊዜ ከተጠቀሱት የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ውስጥ ሰማያዊ ቀለም አይገኝም::

ይህ ከሕገመንግስቱ ጭምር ይቃረናል የምንለውና ከሰደንቅ ዓላማ ቀለማት መካከል ክብ ሰማያዊ ቀለምን በመጨመር ዓርማው ኮከብ የሰሩት እኩል መስመሮች እና የሚፈነጥቁት ቢጫ ጨረሮች ብቻ መሆኑን የሚያመላክተው የአዋጁ አንቀጽ 16 የፌደል

ግድፈት ይኖርበት ይሆን? በ1988 የወጣው የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ ቁጥር 16/1988 በአንቀጽ 12 ላይ ያሰፈረው ድንጋጌ አሁን ከምናወራው የአዲሱ አዋጅ ድንጋጌ ጋር የአንዲት ፊደል ልዩነት እንኳን የላቸውም፤ ቃል በቃል የተደገመ ነው:: እንግዲህ የ88 አዋጅ የዓርማውን አቀማመጥ በተመለከተ (ማለትም የዓርማው ክበብ ከአረንጓዴና ከቀይ ቀለማቱ አጋማሽ የሚጀምር መሆኑን አስመልክቶ) በ1989 በሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ ቁጥር 48/1989 አማካኝነት ማሻሻያ ተደርጐበታል:: እንዲህ ያለ መሠረታዊ የፊደል ግድፈት ያን ጊዜ ሊስተካከል ይገባ ነበር:: ሆኖም ተመሳሳዩ ድንጋጌ በአዲሱ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ በተመሳሳይ መልኩ ሲደገም የፊደል ግድፈትነቱን ጥርጥር ውስጥ ያስገባዋል:: ለማለት የተፈለገው:- የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አንድ ዓይነት ብቻ ስለመሆኑ የሚደነግገው የአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 16 ኢ-ሕገመንግስታዊነት (unconstitutionality) የሚንፀባረቅበት ስለሚመስል ልብ ሊባል ይገባ ነበር ወይም ይገባል::

## የተከለከሉ አጠቃቀሞችና ቅጣቶቻቸው

ባንዲራን አላግባብ መጠቀም ሊያስቀጣ መቻሉ እንግዳ ሊሆንብን አይገባም:: በሌሎች ዓለማት ባንዲራን ማቃጠልም ሆነ የባንዲራን ክብር መንካት የተከለከለና ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ አዲስ አይደለም:: ለምሳሌ፣ በአሜሪካን ሀገር እ.ኤ.አ ከ1923 ጀምሮ ተግባራዊ ነበር:: እንዲያውም በ1968 ባንዲራን በአደባባይ ያቃጠለንም ሆነ በሌላ መንገድ የባንዲራን ክብር ያጐደለን የአንድ ዓመት እስራት ወይም የአንድ ሺህ ዶላር ቅጣት ወይም ሁለቱንም ሊያስቀጣ የሚችል ሕግ ወጥቶ ነበር - በአሜሪካ::

በኛም ሀገር የቀደሙትን አዋጆች በመሻር የወጣው አዲሱ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ የተከለከሉ የባንዲራ አጠቃቀሞችንና ተያያዥ ቅጣቶችን የሚዘረዝሩ ድንጋጌዎች አስተዋውቆናል:: በአዋጁ አንቀጽ 23 ላይ የባንዲራ አጠቃቀምን በተመለከተ አስራ አንድ (11) የተከለከሉ ተግባራት ተዘርዝረዋል::

ሰንደቅ ዓላማው ላይ ቃላቶችን መፃፍ፣ ሌሎች ምልክቶችን ወይም አርማዎችን ወይም ስእሎችን ለጠፎ መገልገል፤ ያረጁ፣ የተበላሹ፣ ቀለማቸው የደበዘዘና የተቀዳደዱ ሰንደቅ ዓላማዎችን መጠቀም፣ ሰንደቅ ዓላማው በወጣበት ሰንደቅ /ምሰሶ/ ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ ያለ አግባብ ሌሎች ሰንደቅ ዓላማዎችን ወይም አርማዎችን ጨምሮ ማውለብለብ ወይም መገልገል፤ ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ሰንደቅ ዓላማውን በጽሁፍ ወይም በቃላት፣ ወይም በድርጊት ወይም በሌላ በማናቸውም አኳኋን መድፈር ወይም ማዋረድ ወይም ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ፤ የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማት ቅደም ተከተል እንዲሁም የብሔራዊ አርማውን መጠን ሳይጠብቁ ማዘጋጀትና መገልገል፤ ሰንደቅ ዓላማውን በአዋጁ ከተጠቀሰው የማውረጃ ጊዜ በላይ ማቆየት፤ በስብሰባ ወይም በማናቸውም መሰል ክንውኖች ሰንደቅ ዓላማውን የጠረጴዛ ሽፋን አድርጐ መጠቀም፤ ሰንደቅ ዓላማን የህንፃ ወይም የሌሎች ቁሳቁሶች መሸፈኛ ማድረግ፤

ሰንደቅ ዓላማውን በማንኛውም ንግድ ማስታወቂያነት መጠቀም፤ እና ሰንደቅ ዓላማው በሚሰቀልበትና በሚወርድበት ጊዜ ተገቢውን ክብር አለመስጠት በአዋጁ መሠረት እስከ ሶስት ሺህ ብር ቅጣት ወይም እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ እስራት ያስከትላል፡፡

ከላይ ለመዘርዘር የሞከርነው አስሩን የተከለከሉ ተግባራት ሲሆን በዚሁ አንቀጽ 23 ላይ በንዑስ አንቀጽ (1) «ሰንደቅ ዓላማውን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ዓርማውን ሳያካትቱ መጠቀም» የተከለከለ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህ ተግባርም ቅጣቱ ከሌሎቹ ከፍ የሚል ሲሆን ሰንደቅ ዓላማውን ያለአርማው የተጠቀመ ሰው አምስት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም አንድ ዓመት ከስድስት ወር በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡ ተግባሩን የፈፀመው የሕግ ሰውነት ያለው አካል ወይም ድርጅት ከሆነ ደግሞ የገንዘቡ ቅጣት ከሁለት እጥፍ ያላነሰ ይሆናል፡፡

ይህ ከሁሉም ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትለው የተከለከለ ተግባርም ሆነ ሌሎቹ አብዛኛዎቹ ተግባራት ከባንዲራ አጠቃቀም ጋር የተየያዙ ናቸው፡፡ በርግጥም በአዋጁ አንቀጽ 12 ላይ በተዘረዘሩት ቦታዎች እና ሰንደቅ ዓላማው መሰቀል በሚገባበት ቦታዎች ላይ አርማ የሌለውን ሰንደቅ ዓላማ መጠቀም ማስቀጣቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ ባለፈ የተከለከለው ተግባር መፈጸሙን እንጂ ጥፋተኛ የሚያስብለው አርማው የሌለበትን (ወይም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ብቻ ያሉበትን) ሰንደቅ ዓላማ እንደባንዲራነት የመጠቀምና ለኢፌዴሪ ሰንደቅ ዓላማ ቦታ ያለመስጠት የዓይምሮ ዓላማ (intent) መኖሩ ይሁን በቸልተኝነት መፈጸሙ በግልጽ አልተቀመጠም፡፡ ለምሳሌ በዚህ ዓመት የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን ሲከበር በዓረማው ላይ ስህተት ያለባቸው ባንዲራዎች በከተማው ተበትነው ነበር፡፡ በሚዲያ ይቅርታ የተጠየቀበት ሁኔታ ቢኖርም ይህ ተግባር ያለ ቅጣት የታለፈው በምን የሕግ መሠረት ነው? አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማት ያሉት «ሻርፕ» ለብሶ መሄድ ያስቀጣ ይሆን? ሻርፑን የለበሰው ሰው እንደባንዲራነት እየተጠቀመው መሆኑ ሳይረጋገጥ ጥፋት ይባል ይሆን?

ለማንኛውም፣ አዲሱ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ሰንደቅ ዓላማውና ዓርማው የባንዲራ አጠቃቀምን በተመለከተ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን በግልጽ አስቀምጧል፡፡ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማት ብቻቸውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ እንደማይሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በሌላ አገላለጽ ዓርማው የሰንደቅ ዓላማው አካል መሆኑን ያሳስባል፡፡ በዚህ አዋጅም ሆነ በተሻሩት «የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መልክ» ሲገለጽ አርማውም ተካትቶ እንመለከታለን፤ የተሻሩት የ1988 እና የ1989 አዋጆች «የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ» የሚል ስያሜ ሲኖራቸው አዲሱ አዋጅ «ዓርማ» የሚለውን ቃል አስቀርቶ «የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ» ብቻ መባሉ ለዚሁ ይሆን?

# የማንነት ጥያቄ፣ መንስዔና ውጤት

# (ከቅድመ ቅኝ አገዛዝ እስከ ዛሬ)

**በባሕሩ ዘውዴ (ፕሮፌሰር)**

*የማንነት ጉዳይ በሰዎች ማሕበረሰብ ውስጥ በጣም ማዕከላዊነት ይዞ የቆየ ነው። የበርካታ አርቲስቶችንና ጸሐፊዎችን የፈጠራ ጥረቶች ዘመን አይሽሬነት አላብሷል። በይበልጥ በአሉታዊ ገጽታው ሲታይ፣ ዓለምን ለዓመታት ያመሷት አብዛኞቹ ግጭቶች መንስዔ በመሆን የሚጠቀስ ነው። ሌላው ቀርቶ በቅርብ ዓመታት የተከሰቱ ብዙዎቹን ግጭቶች ብንመለከት፣ ምን ያህሎቹ በማንነት ጉዳይ ላይ ማጠንጠናቸውን እንገነዘባለን። ምናልባት መፍትሄ ለመስጠት በጣም አስቸጋሪ ከሆኑትና በዩናይትድ ኪንግደም የተረጋጋ ሕይወት መምራት አስቸጋሪ አድርጓል ተብሎ የሚተቀሰው የአየርላንዳውያን የማንነት ጥያቄ ለክፍለ ዘመን የቆየ ነው። ባስኮች ከስፔን ለመገንጠል ለበርካታ ዓመታት ሲዋጉ ቆይተዋል። በኢሲያ፣ በሕንድና በፓኪስታን መካከል ያለው ሁኔታም፣ የቻይናና የታይዋን ከግማሽ ክ/ዘመን በላይ የቆየ አለመግባባት እና በካናዳ በእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች እና በፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች (በኩቤካውያን) መካከል የሚነሳው ተመሳሳይ ጥያቄ በማንነት ላይ የሚያጠነጥን ነው። በአፍሪካም ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው።*

*የመበታተን ፖሊሲን እና የእርስ በእርስና ድንበር ዘለል የግጭት ታሪክን ማስወገድ የፓን-አፍሪካኒዝም ታላቁ መርሆው ነበር። ይህንንም ፖሊሲ ከመፀነሱ ጀምሮ ያራመደውና አፍሪካውያን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ያወጁትን ትግል ያበሰረውም ንቅናቄው ነበር። ለንቅናቄው መፀነስ አፍሮ-አሜሪካውያን እና አፍሮ-ካረቢያውያን የቀድሞ የትውልድ ማንነታቸውን መልሶ ለማግኘት የጀመሩት አሰሳ እንደምክንያት የሚጠቀስ ነው። መላ ትውልደ-አፍሪካውያን ጭቁን ሕዝቦች የሚጋሩት የጋራ እጣ ፈንታ ያላቸው በመሆኑ የጋራ ጠላታቸው የሆኑትን ቅኝ-አገዛዝና ዘረኝነትን በሕብረት መፋለም አለባቸው የሚለው ጽኑ እምነት የንቅናቄው የማዕዘን ድንጋይ ነበር።*

*ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የፓን-አፍሪካ ንቅናቄ፣ በአፍሪካዊ ብሔርተኞቹ ጆሞ ኬንያታና ኩዋሜ ንክሩማህ ቀዳሚነትና መሪነት ተቀባይነት በማግኘቱ፣ አሕጉራዊ ትኩረትና አቅጣጫ እንዲይዝ አስችለውት ነበር። አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነፃነታቸውን ባገኙ ከሶስት ዓመታት በኋላ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ1963 ለመመስረት ችሏል። የድርጅቱ መመስረትም የነፃነት እና የአሕጉራዊ አንድነት መርህዎች ውህደትን ያስከተለና ያጠናከረ ነበር። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ያስመዘገባቸው ስኬቶች በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ባይኖራቸውም፣ ይህን ድርጅት የተካው የአፍሪካ ሕብረት ስራውን የጀመረው በጎ ተስፋዎችን በመሰነቅ ነበር። ድርጅቱ አለመረጋጋት በአህጉሪቱ ሲከሰት ክልላዊ ጣልቃ ገብነትን የሚፈቅዱ አካላት ያሉት ሲሆን በተጨማሪም መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋንያንም በአሕጉሪቷ ጉዳዮች ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚፈቅዱ የተወሰኑ እርጃዎችን ወስዷል። ይህም መሆኑ ድርጅቱ የአፍሪካ*

ርዕስ-መስተዳደሮች ስብስብ ብቻ ነው የሚለውን ገጽታ ለማስወገድ ያስቻለ ነው ተብሎ የሚጠቀስ ነው::

በአሁኑ ወቅት ደግሞ፣ የማንነት ጉዳይ ያለው ወሳኝነትና ታሪካዊ ጥልቀት የብዙ የታሪክ ጸሐፊዎችን፣ ተመራማሪዎችንና አጥኝዎችን ትኩረት የሳበ ነው:: ጉዳዩም የአፍሪካ ታሪክ አጥኝዎችና አፍሪካዊ የታሪክ ተመራማሪዎችንም ትኩረት ቆንጥጦ የያዘ ነው:: በዚህም ምክንያት፣ የአፍሪካ የታሪክ አጥኝዎች/ ተመራማሪዎች ሕብረት በ2007 በተካሄደው ስብሰባ ላይ፣ *«Society, State and Idenity in African History»* በሚል ርዕስ ጭብጥ ዙሪያ እንዲያጠነጥን ውሳኔ አስተላልፎ ነበር:: ከተካሄደውም ጉባዔ፣ *የአፍሪካ ታሪክ አጥኝዎችና አፍሪካዊ የታሪክ ተመራማሪዎች*፣ የማንነት ጉዳዮችን ከታሪካዊ ዳራ አንፃር የሚቃኙ ስራዎች እንዲያቀርቡ፣ እውቀታቸውንና ምሁራዊ አመለካከታቸውን ለማሰባሰብ ተስፋ አድርጎ ነበር::

ለጉዳዩም ትኩረት ለመስጠት ተብሎም፣ የሚከተሉት ንዑስ ጭብጦች በሀሳብ ደረጃ ቀርበው ነበር:- የቅድመ ቅኝ-አገዛዝ ማንነቶች፣ ስደትና የባሕል ስብጥሮሽ፣ የቅኝ-አገዛዝ ድንበሮች መፈጠር፣ ቅኝ-አገዛዝና ማንነት፣ የከተማ መስፋፋትና የተለያዩ ማንነቶች፣ አንዱ ሌላኛውን እንዴት እንደሚመለከትና የሌላ ባሕል ወይም ማንነት ጥልቅ ጥላቻ፣ ክልላዊ ታሪኮችን የመፃፍ እንቅፋቶች፣ ፌዴራሊዝምና ኃላፊነትን መሸከም፣ ድንበር ተሸጋሪና የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ *ሥነ-ጽሑፋዊ* አገላለፆች፣ ከክልላዊ ውህደቶች የተቀሰሙ ትምህርቶች እና መላ አፍሪካውያንን የሚወክል ማንነት ለመፍጠር ስላሉ እንቅፋቶች ናቸው::

ጉባዔው የተካሄደው በአዲስ አበባ በግንቦት 22-24 2007 ነበር:: ከላይ በተጠቀሱት ጭብጦች ዙሪያ ለተደረገው ጥሪ የተሰጠው ምላሽ አዘጋጆቹ ከጠበቁት በላይ ነበር:: ፍላጎቱ የነበራቸው 170 ምሁራን የጥናት ውጤቶቻቸውን አቅርበው የነበሩ ሲሆን ከቀረቡት ስራዎች ውስጥም በጉባዔው መቅረብ ያለባቸውን ጽሑፎች ለመምረጥ የተዋቀረ አንድ ኮሚቴ፣ ጥልቅ የመረጣ ስራ ካከናወነ በኋላ በመጨረሻ ከ170ዎቹ ውስጥ 67ቱ ተመርጠው በጉባዔው ለመነበብ በቅተዋል:: እናም፣ በዚህ የመግቢያ ጹሑፍ የሚዳሰሱት ማንነትን የተመለከቱ ጉዳዮች፣ በዚያ ወቅት ከተነበቡት ስራዎች የተወሰዱ ናቸው::

**ቅድመ ቅኝ-አገዛዝ ማንነቶች**

በቅድመ ቅኝ-አገዛዝ የአፍሪካ ታሪክ፣ በቀዳሚነት በጉልህ ታይቶ ከነበሩት መካከል የሕዝቦች ከአሕጉሪቷ አንድ ክፍል ወደሌላኛው ያካሄዱት እንቅስቃሴ ይጠቀሳል:: ፍልሰቶች እና ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ያደርጉ የነበረው እንቅስቃሴ ተደጋጋሚ የነበረ መሆኑ ከፍተኛ የታሪካዊ ምርምርና ጥናት ትኩረት ለመሳብ ችለዋል:: ከእነዚህ መካከል የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመላ ምዕራብያዊ፣ ማዕከላዊና ደቡባዊ አፍሪካ እንዳካሄዱት ዓይነት እንቅስቃሴ፣ በይበልጥ ዘላቂ ትርጉም የነበራቸው ጥቂቶች ናቸው::

በውጤቱም፣ እነዚህ ክልሎች አሁን የያዙትን የቋንቋ ቅርጽ እንዲይዙ ምክንያት የሆነ ነው:: በ16ኛው መ/ክ/ዘ፣ የኦሮሞ እንቅስቃሴ የአፍሪካ ቀንድን የሕዝብና ባሕል ቅርፅ የለወጠ ነበር:: በ19ኛው መ/ክ/ዘ፣ በደቡብ አፍሪካ የዙሉ መስፋፋት፣ በታሪክ «Mfecane» ተብሎ የሚጠራ የሕዝብ እንቅስቃሴን ያስከተለ ነበር («Mfecane»፣ «አስቸጋሪ ወቅቶች» ወይም «መቋጫ የታጣለት ጦርነት» የሚያመላክት ቃል ነው::):: ይህም፣ ስዋዚላንድ እና ሌሴቶ፣ እንዲሁም በአሁኗ ዝምባቡዌ ውስጥ የነበረውን ማታቤሌላንድ ንጉሣዊ ሥርዓት እንዲፈጠር ያስቻለ ነበር:: የዚህ ሕዝብ እንቅስቀሴ ድርብ ድርብርብ ተጽዕኖ፣ እስከ ምስራቅ አፍሪካ የሀይቀ ክልልን ጭምር የሸፈነ ነበር:: በመጨረሻ፣ በሰሜን ናይጀሪያ የተጀመረው የፉላኒ ጂሃድ፣ የሶኮቶ ካሊፋትን ከመፍጠሩ በተጨማሪ እስከ ሴኔጋምቢያ ድረስ መላ ምዕራብ አፍሪካን ለማዳረስ የተቻለው ነበር:: ጅሃድ በተፈጥሮው ግጭት ማስከተሉ የማይቀር ነው:: የእነዚህ ሕዝቦች እንቅስቃሴ፣ በአብዛኛው በጥፋትና በመፈናቀል የታጀቡ ነበሩ:: ነገር ግን፣ በመጨረሻ፣ በጊዜ ሂደት፣ አዳዲስ ማንነቶችን መፍጠሩ ወይም ነባሮቹን ማዋሀዱ የማይቀር ነው::

ሌላው የቅድመ ቅኝ-አገዛዝ ጉልህ ገጽታ፣ የረዥም ርቀት ንግድ ወሳኝ እንደ የነበረ መሆኑ ነው:: የንግድ መስመሮቹ፣ ትናንሽ ግዛቶችን ጨምሮ ሰፋፊ ንጉሣዊ ሥርዓችንም ያዳረሱ ነበሩ:: ከነዚህ መካከል በይበልጥ ይታወቅየነበረው፤ የሰሜን አፍሪካን (ማግርብ ክልል) ከምዕራብ አፍሪካ ያገኛኝ የነበረውና እስከ 20ኛው መ/ክ/ዘ የመጨረሻዎቹ 25 ዓመታት ድረስ ታላቅ የነበረው «ትራንስሰሃራ» (የሰሃራ በርሃን የሚያቋርጠው) የንግድ መስመር ነው:: በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ሌላኛው ወሳኝ የንግድ መስመር፣ ከጠረፍ ወደ መሃል የሚዘልቀው ነው:: ስዋሂሊ የተሰኘ የተለየ ቋንቋና ባሕል እንዲፈጠር ምክንያት የሆነ ነበር:: የኢትዮጵያ ንጉሳዊ ሥርዓት ከደቡብ ምስራቅ አስከ ቀይ ባህር ጠረፍ (ምጽዋ) የሚዘረጋ ሌላው የረዥም ርቀት የንግድ መስመር ነበር::

ሌላው ተጠቃሹ የንግድ መስመር፣ የጋና አሻንቲን በሰሜን ናይጀሪያ ከሚገኘው ካኖን ጋር የሚያገናኘው ነበር:: የእነዚህ የንግድ መስመሮች ዘለቄታዊ አስተዋጽኦ የነበረው ምንድነው፣ ለሰላማዊ የሃሳቦችና የሰዎች ፍሰት ይቻል ዘንድ እንደ መተላለፊያነት ማገልገላቸውና እንዲሁም በተጨማሪ ከመስመሮቹ የተጠቀሙና ንግዱን ለመቆጣጠር ፍላጎት የነበራቸው መንግስታት እንዲመሰረቱ ማስቻላቸው ነው:: የተለያዩ ባሕሎችን ያቀፉ የነጋዴ ቡድኖች መጠናከርም ሌላው የሚጠቀስ አስተዋጽዖአቸው ነው:: ለተለያዩ ባሕሎችና የፖለቲካ ሥርዓቶች መገናኘት እንደ ድልድይነት ካገለገሉት መካከል፣ ሃውሳ (በምዕራብ አፍሪካ)፣ ጃባርቲ (በኢትዮጵያ) እና ስዋሂሊ (በምስራቅ አፍሪካ) የሚጠቀሱ ናቸው::

ሌላው በጉልህ የታየው ሶስተኛው ክንውን፣ የተለየዩ ሕዝቦችንና ግዛቶችን በጋራ የፖለቲካ ጥላ ስር ያሰባሰቡ በርካታ ንጉሳዊ ሥርዓቶች መመስረታቸውና መጠናከራቸው ነበር:: ከእነዚህ መካከል፣ አልሞራቪድ (በሰሜን አፍሪካ - ማግርብ)፣ ሞኖሞታፓ

(በታላቋ ዝምባቡዌ) እና የኢትዮጵያ ንጉሳዊ ሥርዓት (በአፍሪካ ቀንድ) ይጠቀሳሉ። ይህን ክንውን የተለየ የሚያደርገው ምንድን ነው፣ አካባቢያዊ ማንነቶችና ሁሉ-አቀፍ ማንነቶች በሥርዓቶቹ የተካተቱ የነበሩ መሆናቸው ነው። የመሰረተ-ልማት አለመጠናከር በቅኝ-አገዛዝና በድህረ ቅኝ-አገዛዝ የተተገበረው በኃይል በማስገደድ ወይም በማስፈራራት የመግዛት አካሄድ እንዳይቻል ያደረገ ነበር። በወቅቱ የበላይ ባለሥልጣናት ከነበራቸው ኃይል የላቀ ቀጥተኛና ቅርብ የአስተዳደርና የዳኝነት ሥርዓት በመንደር፣ ጎሳ ወይም አውራጃ ይተገበር ነበር።

**ቅኝ አገዛዝና ማንነት**

በ19ኛው ክ/ዘ መጨረሻና በ21ኛው ክ/ዘ መጀመሪያ ላይ እንደተመሰረተው የቅኝ-አገዛዝ፣ የበለጠ በአፍሪካ ማሕበረሰብ ላይ መሰረታዊ ተጽዕኖ ያለው ለውጥ ማሰብ አስቸጋሪ ነው። አፍሪካ በቅኝ-አገዛዝ ስር መውደቋ ከላይ የተቀመጠውን የታሪካዊ ሂደት አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን የለወጠው የድህረ ቅኝ-አገዛዝ የአፍሪካ ማሕበረሰብንና ፖለቲካን ጭምር ነበር። እንዲሁም በርካታ ቅርጽም ያስያዘ ነበር። የቅኝ-አገዛዝ ሥርዓት በአፍሪካ በቀዳሚነት ያስተዋወቀው - አንዱ የተለየ መገለጫው - እምብዛም ጥንካሬ ያልነበራቸውን የድንበር ወሰኖችን ማስመር ነበር።

የአውሮፓ የቅኝ-አገዛዝ ገዥዎች ወደ አፍሪካ ያመጡት፣ የራሳቸውን በግልጽ የተቀመጠ የግዛት ወሰን እሳቤን ነበር። በመሆኑም በመጀመሪያዎቹ ሁለት አስርት ዓመታት፣ የድንበር ማካለልን የሚመለከቱ ድርድሮችና ስምምነቶች በይበልጥ ተከስተው ነበር። ቅኝ-አገዛዝ፣ አንድ የፖለቲካ ማሕበረሰብ እንዲመሰረት ቢያስችልም፣ መንግስታት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማሕበረሰቡ ውስጥ ብሔርተኝነት መስበካቸው እና ማስፋፋታቸው አዳዲስ «ጎሳዎች» ወይም የ«ብሔር ቡድኖች» እንዲፈጠሩም ምክንያት የሆነ ነበር። በዚህ እንግሊዛውያን የተካኑ ነበሩ። ነገር ግን፣ በጣም አስከፊው የብሔር ፈጠራ የነበረው ቤልጅየምያውያን በሩዋንዳና ቡሩንዲ ያስተዋወቁት ነበር። በጀርመንያውያን፣ ፈረንሳውያንና እንግሊዝያውያን በቅኝ-ግዛት ተይዛ የነበረችው ካሜሩን፣ ሶስት የቅኝ አገዛዝ ትውፊቶችን ለመውረስ ተገዳለች። በተለይ ሁለቱ ትውፊቶቿ፣ ስለምን በአገሪቱ ውስጥ በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የሚከሰተው ማብቅያ የሌላቸው የሚመስሉ ወጥረቶች ይከሰታሉ የሚለውን ጥያቄ የሚያብራሩ ናቸው።

የዚህ እሳቤ ትውውቅ ተጣማሪ የነበው፣ በተወሰኑ የግዛት ወሰኖች ውስጥ የነበሩ ነፃ ሕዝቦችን ያቀፉ አዳዲስ አገሮች ብቅ ማለታቸው ነበር። እያንዳንዳቸው በቅኝ-የተያዙ መሬቶች፣ ይህን ሂደት አልፈዋል ማለት ይቻላል። ኢቦ፣ ዩሩባና ሃወሳ ከበርካታ ደርዘን ትናንሽ ቡድኖች ጋር ተጣምረው ናይጄሪያ ተብላ የምትታወቅ የፓለቲካ ማሕበረሰብ ፈጥረዋል። በተመሳሳይ ኩኩዩ፣ ሉኦ እና ማሳይ እንዲሁ ኬሎች ብዙ ትናንሽ ቡድኖች ጋር በመሆን ኬንያን ለመፍጠር በቅተዋል። ተገዥዎቻቸውን፣ የሰፊዋ የፈረንሳይ

ማህበረሰብ አባላ አድርገው የመመልከት ዝንባሌ የነበራቸው ፈረንሳውያን፣ በዚህ ዘገምተኛ የአገሮች የመፍጠር ሂደት ውስጥ ዝቅተኛ ተሳትፎ ነበር የነበራቸው:: ለረዥም ጊዜም ሰፊ የቅኝ ግዛት ወሰናቸውን ያስተዳደሩት በሁለት ትላልቅ ክልላዊ አካላት ሥር በማድረግ ነበር (ፈረንሳይ ምዕራብ አፍሪካ እና ፈረንሳይ ኢኳቶሪያል አፍሪካ):: ሁለቱ ሰፋፊ ግዛቶችን ከበታተነቻቸው በኋላ ነበር አሁን የምናውቃቸው አገሮች የተፈጠሩት:: ቢሆንም፣ እነዚህ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ አገሮች የራሳቸውን የተለየ ማንነት ለመቀዳጀት የተቻላቸው በድህረ ቅኝ-አገዛዝ ወቅት መሆኑ የሚገርመው ነው::

በቅኝ-አገዛዝ ወቅት የድንበሮች መፈጠር፣ የትላልቅ የግዛት መሬቶች መመስረትና መጠናከርን በአንፃራዊነት መልካም ዝግመታዊ ለውጥ ተደርገው ቢወሰዱም፣ እነዚያ ድንበሮች ከአሉታዊ ውጤቶች የፀዱ አልነበሩም:: በመጀመሪያ የሚጠቀሰው፣ የሰዎችን የንግድና የግጦሽ ፍለጋ አሰሳን ማደናቀፋቸው ነው:: የበለጠ አስከፊው፣ «የተከፋፈሉ አፍሪካውያን» በድንበሮቹ መሰመር መፈጠራቸው ነበር::

በተጨማሪ፣ ቅኝ-አገዛዝ በሃይማኖት ማንነት ላይም የራሱ ተጽዕኖ አሳድሯል:: የቅኝ አገዛዝ ዘመን የተፈጠረው የ«ጥቁር እስልምና»፣ ያመላክት የነበረው የበታችነትና የትንሽነት ስሜት፣ ቀለሙንና ለዛውን ከነበረበት ማሕበረሰብ የወሰደ የ«ሴኔጋልያውያን እስልምና» እየተባለ ይጠራ የነበረን ሃይማኖት ያስከተለ ነበር::: ያም ሆኖ፣ ቅኝ-አገዛዝ በትሩን ያሳረፈው፣ በሁለቱም በቅኝ-ገዥውና በቅኝ-ተገዥው እንዲሁም በወንጀል ፈፃሚውና ወንጀል በተፈፀመበት ላይ ነበር:: በቅኝ የያዘቻቸው ግዛቶች ነፃነታቸውን እንዲያውጁ በተካሄደው ሂደት ተሳታፊ ለመሆን እምብዛም ዝግጅት ባላደረገችው ፈረንሳይ፣ ብሔራዊ ማንነት ከቅኝ-ገዥ ሥልጣን እና የአገር ፍቅር ከንጉሣዊ ሥርዓት ጋር እኩል ተደርጎ ይወሰድ ነበረ:: ለዚያም ነበር በመጀመሪያ በኢንዶኔዢያ ቀጥሎ ደግሞ በአልጄሪያ የተከሰተው ከፈረንሳይ ቅኝ-አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የተደረጉ ትግሎች እጅግ አስቸጋሪና ደም አፋሳሽ የነበሩት::

**ድህረ ቅኝ አገዛዝ**

ከቅኝ አገዛዝ ነፃ መውጣት በአፍሪካ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ የከፈተና አፍሪካውያን የራሳቸውን እጣ እንዲወስኑ ያስቻላቸውም ነበር:: ድክመቶቹና አናዳጅነቱ ያለ ቢኖርም፣ አፍሪካውያን ለራሳቸው የተሻለውን ለመወሰን ብቃቱ የላቸውም የተባሉበትን የታሪክ ዘመን ፍፃሜን የሰጠ ነበር:: ሆኖም፣ ነፃነት መቀዳጀት በቅኝ-አገዛዝ ወቅት ከነበሩ ግንኙነቶች ጋር ሙሉ በሙሉ መቆራረጥን የሚጠቁም አይደለም:: እንዲያ ያለ ፍፁም መቆራረጥ ይከሰታል ብሎ መጠበቅ በራሱ ታሪክን የሚፃረር ነው:: የቅኝ አገዛዝ ፈጠራ የሆነው አንድ የፖለቲካ ማሕበረሰብ፣ የማንነት ዋና መገለጫ እንደሆነ ቀጥሏል:: አዳዲስ ባንዲራዎችና ብሔራዊ መዝሙሮች ለዚህ ዓላማ የዋሉ ነበሩ:: የቅኝ አገዛዝ ድንበሮች አይነኬ ተደርገው መታየታቸው የቀጠለ ነው:: በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና ተከትለው በመጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ሕጋዊ ድጋፍም አግኝተዋል:: ይህም

ተቀባይነትን ያገኘበት ምክንያት ድንበሮቹን ዳግም ለመወሰን ሙከራ ማድረግ፣ በራሱ ከፍተኛ ቀወስ ሊያስከትል ይችል የነበረ በመሆኑ ነበር፡፡ ሆነም ቀረ፣ በክልላዊና በአህጉራዊ ደረጃ፣ በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ውህደትንና አንድነትን መፈለግና የቅኝ አገዛዝ የድንበር ወሰኖችን እንዳሉ ለማስቀጠል የሚፈልጉ የአፍሪካ መሪዎች ተቃርኖሽ ግን አሁንም እንደቀጠለ የሚገኝ ነው፡፡

ነፃ አገርንና ማቀንቀን በታሪካዊ ምርምርና ጥናት ላይም ተጽዕኖ ነበረው፡፡ የአገርን ታሪክ መፃፍ የሙሉ ሰዓት ስራ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ በመሆኑም፣ አካባቢያዊ ታሪክንም ብቻ ሳይሆን ድንበር ዘለል ወይም ክልላዊ ታሪክን ወደ መዘንጋት ወይም መናቅ እየተሄደ ያለ እውነታ ነው፡፡ ሰላምና ደህንነትን ከማስፈን ይልቅ፣ ከቅኝ አገዛዝ በኋላ የነበረው የመንግስት ሕይወት፣ ታይተው የማይታወቁ ግጭቶችና የሕዝቦች መፈናቀል የተስተዋለበት ነው፡፡ ድንበር ዘለልና የእርስ በእርስ ግጭቶች አፍሪካን ያጥለቀለቁ ነበሩ፡፡ በተንሰራፉት ግጭቶች ምክንያት፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ስደተኞችና ተፈናቃዬችም ለመሆን ተገደው ያልተረጋጋ ህይወት እንዲመሩ አስገድዷቸዋል፡፡ ሌላ ባሕል/ማንነት ያላቸውን በእጅጉ መጥላት እና የብሔር ጭፍጨፋዎች አስቀያሚ ገፅታቸው ሊከሰቱ ችለዋል፡፡ በአፍሪካ ውስጥ የተከሰቱት ከሌሎች የዓለማችን ክፍሎች የተለዩ አይደሉም፡፡ አብዛኞቹ ግጭቶች ከማንነት እሰጥ አገባዎች የሚመነጩ ወይም የአፍሪካ መንግስታት ብዙ ማንነቶችን ማቀፍ ባለመቻላቸው ምክንያት የተከሰቱና የሚከሰቱ ናቸው ብሎ መግለፅ ማጋነን አይሆንም፡፡

የእነዚህ ችግሮች የስር መንስኤ ሆኖ የቆየው የአስተዳደር ጉዳይ ነው፡፡ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ መውጣት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ወዲያው አላመጣም፡፡ በተፃራሪው፣ የመጀመሪያዎቹ የነፃነት አመታት ከፍተኛ ደስታና ተስፋ፣ ወዲያው በብልሹ አስተዳደርና የአምባገነንነት የተተኩ ነበሩ፡፡ ይህም ኢኮኖሚያዊ ውድቀትን ብቻ ሳይሆን ያስከተለው የተለያዩ ማንነቶች ባላቸው ሰዎች መካከል የለየለት አለመቻቻልንም ነበር፡፡

*/ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፣በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ናቸው/*

# በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያጋጥሙ ፈተናዎችና እድሎች

## (ስለቀጣዩ ብሔራዊ ምርጫዎች እና ስለሌሎች ጉዳዮች)

**በተስፋዬ ሀቢሶ (አምባሳደር)**

የኢትዮጵያ አጭሩ የዴሞክራሲ ተሞክሮና ለሁለት አስርት ዓመታት ያህል፣ የበርካታ ብሔሮች፣ ባሕሎች እና ቋንቋዎች ባለቤት በሆነ የማሕበረሰብ ስብጥር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ለመገንባት አገሪቱ ያደረገቻቸው ሙከራዎች ልክ በትራንስፖርት መሰረተ-ልማቶች፣ በኢኮኖሚያዊ እድገቶችና በማሕበራዊ አገልግሎቶች (ለከተማው ድሀ የጋራ የመኖሪያ ቤቶችንና ለገጠሩ አርሶ አደር ደግሞ ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ ክሊኒኮች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መንገዶችና ወዘተ ማቅረብ) ከተገኙ የሚያበረታት ስኬቶች ጋር ሲነፃፀር ገና ብዙ መስራት ይጠበቅባታል:: ትላንት፣ ዛሬና በመጭ ጊዜያት ዴሞክራሲን በመገንባት ጥረቶች መሰረታዊ እንቅፋቶች ናቸው ተብለው ሊጠቀሱ ከሚችሉ ዋና መንስኤዎች ውስጥ የፖለቲካው ሥርዓቱ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት (ኢሕአዴግ) በበላይነት መያዝ፣ የማሕበረሰቡ የበርካታ ብሔሮች፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ስብጥርነት፣ የብሔር የበላይነት የሚታይበት የፖለቲካ ሥርዓት መስፋፋት፣ አስከፊ ድህነት ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው::

ዴሞክራሲያዊ አሳቤዎችን፣ ሕጐችን፣ ሥነ-ሥርዓቶችንና የሥልጣን ሽግግርን በጠመንጃ አፈሙዝ እንጂ በነፃ፣ በፍትሀዊና ተዓማኒነት ባለው ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች በሰላም የማከናወን ውርስ ያልወረሱ መሪዎች መካከል የፖለቲካ መቻቻል ባሕል ለማጎልበት እንቅፋት የሆኑ ፈተናዎች ዴሞክራሲን አስመልክቶ በተፃፉ በርካታ ወፋፍራም ጥራዞች ውስጥ በቀላሉ ተተይበው እናገኛቸዋለን:: በእነዚህ መንስዔዎች የተነሳ ዴሞክራሲን የማጠናከር ሂደት ፍጥነትና እድገት፣ ወደስኬታማ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሥርዓት ሽግግርና መጠናከር አሁንም በመንገታገት ላይ የሚገኝ ነው::

አብዛኛውን ጊዜ በየወቅቱ የሚካሄዱ ምርጫዎችከመወነጃጀል የጸዱ አይደሉም:: ምርጫዎቹም ሕዝባዊ አለመረጋጋቶችንና ግጭቶችን ያስከተሉ ነበሩ:: በመሆኑም፣ በየወቅቱ በቋሚነት ነፃ፣ ፍትሀዊና ተዓማኒ ምርጫዎችን ማካሄድ፣ የሥነ-ሥርዓት ጥራት፣ የፖለቲካ መብቶች መጠበቅ (ለምሳሌ የመምረጥ፣ የፖለቲካ ፓርቲ የመመስረትና በምርጫዎች የመወዳደር መብቶች)፣ የሲቪል ነፃነቶች መከበር (ለምሳሌ ሀሳብን የመግለጽና የመደራጀት ነፃነት) እና መንግስት ምን ድረስ ተጠያቂ፣ ግልጽና ለሕግ የበላይነት ያለው ክብር ብዙ መስራት የሚጠይቁ ናቸው::

የማህበረሰቡ ዋና ዋና የፖለቲካ መሪዎች/ቡድኖች የዴሞክራሲ ጉልበታ ሂደት ሰኬታማነትና ለሥርዓቱ መጠናከር በሥርዓቱ የጨዋታ ድንጋጌዎች ላይ ካልተስማሙና ለድንጋጌዎቹ ካልተገዙ የተባሉት የዴሞክራሲ ስኬትና የሥርዓት መጠናከር እውን እንደማይሆኑ በርካታ ምሁራን አበክረው ይከራከራሉ:: የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሰረታዊ ድንጋጌዎች አላማ ሙሉና ከእንቅፋት የጸዱ የፖለቲካ ፉክክርና ተሳትፎ እንዲኖሩ ማስቻል ነው:: ስልጡን የማህበረሰቡ አካላት ለዴሞክራሲ የሚሰጡት ድጋፍ በአብዛኛው የሚመነጨው በሁሉም ወይም በተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች መካከለ ከሚደረጉ ስምመነቶች ነው:: ሁሉ አቀፍ ስምምነትም የሚኖረው ወሳኝ የፖለቲካ ቡድኖች በስምምነቱ ሲሳተፉ ነው:: ይህም ሙሉ የፖለቲካ ፉክክር እንዲኖር የሚያስችል ሰፊ እደል አለው ምክነያቱም ዋናዎቹ የፖለቲካ ቡድኖች በምርጫዎቹ ውጤት መሰረት በሚመሰረተው ሥርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ ፉክክር ማድረግ ስለሚቻላቸው ነው::

አንደዚያ ያሉ ስምምነቶች ሁለት ውጤቶች አሏቸው:- አንደኛው፣ ግልጽና ሰላማዊ ፉክክር በየፖለቲካ መሪዎች/ቡድኖች መካከል እንዲካሄድ የሚያስችል ቋሚ ሥርዓት የሚፈጥር መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓቶችን ወደ መረጋጋት በመለወጥ ሥልጣንን በኃይል የመጨበጥ እድልን ያስቀራል እንዲሁም የመከሰታቸውን አጋጣሚ በእጅጉ ያሳንሰዋል:: በተፈጥሮው፣ የዋና ዋና የፖለቲካ ቡድኖች/መሪዎች ስምምነት ውህደት የሌላቸው «በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት» ወደ መመስረት ያሸጋግራቸዋል:: በመሆኑም በፍቃዳቸው ተስማተው የተዋሃዱ የፖለቲካ ቡድኖች/መሪዎች «የተረጋጋና የውክልና ሥርዓትን ይመራሉ»:: «በየወቅቱ በሚካሄዱ የፉክክርና አሳሪ ምርጫዎች» አማካኝነትም የመንግስት ሥልጣን በተለያዩ ሰዎችና አንጃዎች መካከል በሰላማዊ መንገድ ይተላለፋል:: ዘላቂ ዴሞክራሲ የሚያመጣ የሥርዓተ ሽግግር የስምምነት ውጤት ሲሆን ወደ ወደላቀ ዴሞክራሲ የሚያመራ የሥርዓት ሽግግር ደግሞ የስምምነት መታጣት ውጤት ነው::

የዴሞክራሲያዊነት ሂደት በአብዛኛው በተለምዶ ከሚታወቀው በበለጠ በችግሮችና በፈተናዎች የተሞላ ነው:: የዶናልድ ኤል. ሆሮዊትዝ «በጣም በተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ዴሞክራሲ የተለየ ሲሆን በከረሩ የብሔር መከፋፈሎች ፊት ዴሞክራሲ ሕይወት ሊኖረው አይቻለውም» የሚለው ምልከታው በአብዛኛው ተቀባይነት አለው:: ጆን ስቱዋርት ሚል *«Representative Government»* በሚለው መጽሀፉ፣ «ከተለያዩ ብሔሮች በተመሰረተች አገር ውስጥ» ዴሞክራሲ «ስኬታማ መሆን ጭራሽ ከማይቻልበት ደረጃ ዝቅ ያለ ነው» ካለበት ጊዜ አንስቶ እንኳ፣ በርካታ ተቀባይነት ያገኙ ምልከታዎች የጆን ስቱዋርትን አመለካከቶች አራምደዋል:: በተመሳሳይ እይታ፣ ፍራንሲስ ፉኩያማ «The *End of History and the Last Man»* በተባለ መጽሐፋቸው፣ «... በአንድ አገር ውስጥ በሚኖሩ ቡድኖች ያለ ብሔርተኝነት የአገር አንድነት ስሜት እስከማይጋሩበት ደረጃ

ድረስ እና አንዳቸው የሌላኛቸውን መብቶች የማይቀበሉበት ደረጃ ድረስ በጣም ከከረረ በዚያች አገር ውስጥ ዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም:: በመሆኑም፣ ልክ በብሪታኒያ፣ ዩ.ኤስ.አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ጣልያንና ጀርመን ዴሞክራሲ ከመምጣቱ አስቀድሞ ጠንካራ የአገር አንድነት ስሜት ልክ እንደነበረው፣ የተረጋጋ ዴሞክራሲ ከመምጣቱ አስቀድሞ ጠንካራ የአገር አንድነት ስሜት አስፈላጊ ነው:: ሶቭየት ሕብረት ወደ ትናንሽ አገሮች ከመበታተኗ አስቀድሞ የተረጋጋ ዴሞክራሲ ያልመጣበት አንዱ ምክንያት የአገር አንድንት ስሜት ያልነበረ መሆኑ ነው::

ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች የበቀሉት በምዕራቡ ዓለም በስፋት ከነበሩ ሁኔታዎች ነው:: ለሂደታዊ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መወለድ አስፈላጊ ናቸው ተብለው ከሚታመኑ አላባውያን መካከል የኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ ማንበብና መፃፍ የሚችል የህብረተሰብ ክፍል መጨመር፣ የኃብቶች በስፋት መገኘት፣ ከአሉታዊ የውጭ ተጽዕኖዎች ነፃ መሆንና ያለፈውን፣ የአሁኑንና የመጭውን ጊዜ የሚሻገር ርዕይ ያላቸው የፖለቲካ ንድፍ አመንጭዎች ይጠቀሳሉ:: ለአብዛኞቹ ምሁሮች፣ ዴሞክራሲ በርካታ ማህበራዊና ተቋማዊ ቅድመ-ሁኔታዎች የሚጠይቅ ነው:: ዴሞክራሲ ዘጠኝ የሥነ-ልቦና ባህሪዎችን የተላበሰ ሕዝብ ይፈልጋል:: ከባህሪዎቹ መካከል መቻቻል፣ ተጨባጭ እውነታን መቀበል፣ አለማክረርና ሚዛናዊነት የሚጠቀሱ ናቸው:: በተጨማሪ፣ አገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትና ኢኮኖሚያዊ አንድነት እንዲሁም የተማሩ ዜጎች ያሏት መሆን አለባት:: አንድ ሌላ የፖለቲካ ሳይንቲስት አልፍሬድ ዲ ግራዚያ፣ «ጠንካራ ትኩረት ለብዙሃኑ መስጠት»፣ «ከፍተኛ ማህበራዊ ቁርኝት» እና ሌሎች (ከሁለቱ ጋር ዘጠኝ) ለዴሞክራሲ አስፈላጊ ናቸው ያሏቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ::

ሮበርት ዳህል፣ ለመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲ ትግበራ ሶስት አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎችን ያስቀምጣሉ:- 1ኛ፣ ለመንግስትነት፣ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ፣ መጠነ-ሰፊ ፖለቲካዊ ፉክክር ማካሄድ፤ 2ኛ፣ መራጮች በነፃና በፍትሃዊ ምርጫዎች ውሳኔያቸውን ለመስጠት የሚያስችለው የፖለቲካ ተሳትፎ፤ እና 3ኛ፣ ዜጎች የመንግስት ብቀላ ሳይፈሩ ይሁኝታቸውን እንዲገልጹ የሚያስችሏቸው የሲቪልና የፖለቲካ ነፃነቶች:: የ17ኛውንና የ18ኛውን መ/ክ/ዘንን «ሶስተኛ የዴሞክራሲ መጠናከር ማዕበል» አስመልክቶ አሜሪካዊው ሳይንቲስት ሳሙኤል ፒ. ሀቲንግተን በሰጡት ዳሰሳ፣ አገራት ዴሞክራሲን በተለይ ማጎልበት የሚቻላቸው ዝቅተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃ ላይ ሲደርሱ ነው በማለት ይደመድማል:: ብዙ ጊዜ ዴሞክራሲን እንዲሁ በቀላሉ ከሚስተዋል ሚካኒካል ሂደት እኩል ሲታይ ይስተዋላል:: በጉልህ ከሚስተዋሉት መካከል ቋሚ ምርጫዎችን ማካሄድ ይጠቀሳል:: ምርጫዎችን ማካሄድ ወሳኝ ቢሆንም በምንም መንገድ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግርን ሙሉዕ ለማድረግ በቂ አይደሉም:: ምርጫዎች ነፃና ፍትሃዊ ቢሆኑ እንኳን፣ ድምጽ መስጠት ብቻ በራሱ ዴሞክሲን አያመጣም (ሊሊንዲዊ ሲባንዳ):: አንዲት አገር ወደ ዴሞክራሲ

የምታደርገው ሽግግር ተጠናቀቀ የሚባለው «በምርጫ ሥልጣን የሚይዘው መንግስት በበርካታ ወሳኝ ዘርፎች ፖሊሲ የመቅረጽና የመወሰን ሕጋዊና ተጨባጭ ሥልጣን ከያዘ ብቻ ነው።» (ሊንዝና ስቴፈን)። ጉዳዩ የፈለገ ቢሆን እንኳ፣ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር በርካታ ዓመታት ሊወስድ የሚችል ረዥምና አስቸጋሪ ሂደት ነው። አንዴ አገር ወደ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሥርዓት ሽግግር ብታደርግም ወደተረጋጋ ዴሞክራሲ የሚያረገው ጉዞ ደህንነቱ የተጠበቀና የተጠናቀቀ ነው ማለት አይደለም።

ታዲያ መቼ ነው አንዲት አገር ስኬታማ በሁለት እግሮቹ የሚቆም/የጠነከረ ዴሞክራሲያዊት ሆናለች የምትባለው? ዴሞክራሲዋ ተጠናክሯል ማለት የሚቻለውስ መቼ ነው? ዴሞክራሲ ተጠናክሯል የሚባለው በነፃና በፍትሃዊ ምርጫዎች አማካኝነት ሁለት ጊዜ የሥልጣን ሽግግር በሚደረግበት ወቅት ነው የሚሉ የተወሰኑ ምሁራን አሉ። ሌሎች፣ «በከተማው ብቸኛው ጨዋታ» እርሱ ብቻ ሲሆን ነው ይላሉ። ይህም፣ የትኛ ውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ቡድን ሥልጣን ለመጨበጥ ከነፃና ከፍትሃዊ ምርጫዎች በስተቀር ሌላ መንገድ የማይከተል ከሆነ እንደማለት ነው። አሁንም ሌሎች፣ ፉክክር ያለበት ፖለቲካን፣ ሃሳብን በነፃነት መግለጽንና የአናሳዎችን መብቶች ጨምሮ ሲቪል ነፃነቶችን እንደማክበር ያሉ መመዘኛዎችን በመጠቀም አንዲትን አገር ጠንካራ ዴሞክራሲ አጎልብታለች አላጎለበተችም በማለት ያሳካችውን ሕጋዊና ተቋማዊ ገጽታዎች በመመልከት ስኬቷን ይለካሉ። አንዲት አገር ዴሞክራሲያዊ ሽግግር አድርጋ ካጠናቀቀች በኃላ የሚቀረው ለዘላቂ ዴሞክራሲ ወሳኝ የሆነው የዚያ ዴሞክራሲ መጠናር ነው።

የዴሞክራሲ መጠናከር ወደ ዴሞክራሲያዊነት ከሚደረግ ሽግግር የበለጠ አስፈላጊ ሂደት ነው። መንግስት ወደ ዴሞክራሲ ሽግግር ማድረግ ይቻለው ይሆናል። ሆኖም የተባለውን ዴሞክራሲ ካላጠናከረው ራሱን ወደአምባገነንነት ወይም ወደሌላ ዓይነት ዴሞክራሲያዊነት ያልተላበሰ የመንግስት አደረጃጀት ሊለውጥ ይችላል። ዴሞክራሲ «ተጠናክሯል» ለመባል ሌሎች ተጨማሪ መመዘኛዎች መሟላት ያለባቸው ሲሆን አለባቸው እነዚህም፡- 1ኛ፣ ለነፃና ለጠንካራ ሲቪል ማህበረሰብ መጎልበት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች መኖር፤ 2ኛ፣ በአንፃራዊነት ሉዓላዊ የፖለቲካ ማህበረሰብ ሊኖር፤ 3ኛ፣ በጠቅላላ የአገሪቱ ግዛት ውስጥ ሁሉም ዋናዎቹ የፖለቲካ ተዋንያን - በተለይ መንግስትና የመንግስት አካላት - የግለሰብ ነፃነቶችንና መደራጀትን በሚያስጠብቀው የሕግ የበላይነት ስር መንቀሳቀስ፤ 4ኛ፣ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሊጠቀመው የሚችል አሰራር (ቢሮክራሲ)፤ እና 5ኛ፣ የተደራጀ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ናቸው።

በአገራችን እንዳለው ያልተጠናከረና እያደገ ላይ በሚገኘው ዴሞክራሲ ላይ፣ ውጤታቸው የተጭበረበሩ ምርጫዎች ወይም ደካማ አስተዳደር፣ ገዳይ ጉዳትና በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ላይ ሊያደርስ ይችላል። ለዚህ በድህረ-97 የክልላዊና ብሔራዊ የፓርላማ ምርጫዎች ማግስት የተከሰተው አስጠሊታ ሁነት ፍንትው ያለ ምሳሌ ነው። የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ከሰብዓዊ ፍጡር ዕድገት እምብዛም የተለየ አይደለም። ላቅመ

አዳም የደረሰ የሰው ልጅ የሚቋቋማቸው ችግሮች ዳዴ እያለ ያለን የሰው ልጅ ሕይወት ሊቀጥፍ ይችላል:: የመንግስታችንና የማህበረሰባችን መሪዎች እንደመሆናችን ሹመታችን ውድና በማደግ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ጠባቂዎች የሚያደርገን ነው፤ ነንም:: እንደማንኛውም በሥነ-ምግባር እንደታነጸ ወላጅ፣ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በህይወት መቆየትና ጤንነት ስንል ዴሞክራሲውን ከራሳችን ፍላጎት በላይ ማስቀመጥ አለብን:: የትኛውም ወላጅ ሆዱ እንደብራና እስኪወጠር እየተመገበ ልጁን ለረሀብ አያጋልጥም::

እንደተመራጭ ባለሥልጣንነታችን፣ እንደመንግስት ኃላፊነታችን፣ እንደማህበረሰቡ መሪነታችንና እንደታማኝ አገልጋይነታችን፣ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መስራች አባቶችና እናቶች መካከል የምንካተት ነን:: ከደማችን፣ አጥንታችንና ስጋችን እንደወለድናቸው ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ዴሞክሪሲም መልካም ወላጆች እንሁን:: ዴሞክራሲን ወላጅ አልባ አናድርገው:: ዴሞክራሲ በአዲስነቱ ወቅት ለህዝቡ ያለውን ብቃት ማረጋገጥ ያለበት ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው:: አንደ መጠለያ፣ ልብስ፣ ምግብ፣ የጤና ጥበቃ፣ ትምህርት ወዘተ ያሉ ተጨባጭ ፍሬ ማፍራት ከተሳነው እና መጠነኛ ደህንነት፣ ፀጥታ፣ ሥራ እና ነጻነት ለሕዝቡ መስጠት ከተሳነው፣ ሕዝቡ በዚህ ዓይነት የመንግስት አደረጃጀት ጥልቅ መተማመን አይኖረውም:: ስለማይኖረውም ዛፉ ፍሬ አያፈራም ብሎ በመወሰን ወዲያው ምርት የሚሰጥ ወደሚመስል ሌላ ነገር ሊዞር ይችላል:: ተስፋና እምነት ሊሰፍርበት በሚገባበት ስፍራ ግድ የለሽነት፣ አለመተማመንና ራስ ወዳድነት ይበቅላል:: እናም በዚህ አይነት ድባብ ዴሞክራሲ አደጋ ይጋረጥበታል::

እዚህ ጋር በመጀመሪያ እይታ በፊት ከተናገርኩት ተፃራሪ የሚመስል ነገር ልናገር፤ ይህም ምንድን ነው የአገራችን ታሪክ የሚያሳየን ኢትዮጵያ ካለዴሞክራሲ የተወሰነ ጊዜ ልትቀጥል የምትችል መሆኗን ነው:: እርግጥ ነው ኢትዮጵያ - የብሔር፣ ብሔረሰባችና ሕዝቦች ፌዴራላዊት ኢትዮጵያ - እንደ አገር ለመኖሯ ብቸኛው ጠባቂዋ ዴሞክሪሲ ነው:: ነገር ግን፣ አንዲት አገር የኋላ ኋላ ፖለቲካዊ ዴሞክራሲና ዴሞክራሲ የሚያመላክታቸው የግለሰብና የቡድን/ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ መጠናከር ሳይኖራት እንደ አገር ልትጎመራ፣ ልታብብ ወይም ልትበለጽግ እንደማትችል ታሪክ ምንም የማይወጣው ማረጋገጫ ነው:: ይህ ዴሞክራሲ የተባለው ነገር ውስብስብና አንዳንዴ እንደ ደንበራ እንስሳ ነው:: ከሩቁ ሲታይ ብቃት የሌለው አስተዳደራዊ አደረጃጀት ይመስላለ ሆኖም በቅርበት ሲታይ በጣም ሊተገበር የሚችል ነው::

በአምባ-ገነንነት ሥርዓት ውሳኔዎችን ማስተላለፍና መተግበር ቀላል ነው:: አንድ ግለሰብ - አምባ-ገነን/መሪ - እና ጋሻ ጃግሬዎች የሚወጣቸው «እሺ» ወይም «እምቢ»፣ «አድርግ» ወይም «አታድርግ» የሚሉት ቃላት ብቻ ናቸው:: ጉዳዮች እልባት የሚያገኙ -ት በብርሃን ፍጥነት ነው:: ኢ-ፍትዊነት የአወቃቀሩ የጀርባ አጥንት ነው:: ሕግ አውጭውን ወይም ጠቅላላ ሕዝቡን ማነጋገር አስፈጊ አይደለም ወይም ፍርደ ቤቶችን መፍራትና የቀረበው ሃሳብ ሕጋዊነት አያሰስብም:: በጊዜ ሂደት ወደ ፍፁም ጭቆና፣

የተንሰራፋ ሕገ-ወጥ ትግበራና ወዘተ ብልሹ የአስተዳደር መገለጫዎች ሥርዓቱ ይኳዛል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ የአገራችን መፃኢ ሁኔታን የተሳሳተ አቅጣጫ እንዲያዝ የሚያደርግ ነው፡፡ እንደ እኛ ያለ ልማታዊ መንግስት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ዓይነት መንግስት ውጤታማነት፣ ብቃትና ሥነ-ምግባር የተላበሰ ቢሮክራሲ ከሌለው ሊፀና አይቻለውም፡፡ እንዲሁም በወቅቱ ለመላው ሕዝብ ግልጋለቶችና ምርቶችን ማቅረብ አይቻለውም፡፡

በሌላ በኩል ሕገ መንግስታዊ ዴሞክራሲና የሥርዓቱ እርስ በእርስ የመገማገም ወይም አንድ የመንግስት አካል ሌላኛውን የመቆጣጠር ሥርዓት ምርጡ ሥርዓት ነው ምክንያቱም የሰብዓዊ ፍጡር ባህሪ ድክመቶችን በይበልጥ ያገናዘበ በመሆኑ ነው፡፡ የማህበራዊ ህይወት ንድፍ አውጭዎች እንደሚከራከሩት፣ ሁላችንም ፃድቃን ብንሆን ኖሮ መንግስት  አስፈላጊ አይሆንም ነበር፡፡ ግና፣ መላዕክትና ፃድቃን በመሆናችን ምክንያት አይደለም ዴሞክራሲ እውን የሚሆነው፡፡ ዴሞክራሲ አስፈላጊ የሆነው በሁላችንም ውስጥ የሰፈረውን ጋኔን የሚገድብ የተሻለ የመንግስት አደረጃጀት በመሆኑ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀቶችና ተቋማት መኖራቸው ብቻ በራሳቸው ብቁ አያደርጋቸወም፡፡ በእነዚህ ተቋማት አማካኝነት አስተዳደራዊ ግዴታ እንዲወጡ ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች በልባቸውና አእምሮአቸው የዴሞክራሲ እሳቤች ሊያድሬ ይገባል፡፡ ሕገ መንግስት እንዲሁ ጽሑፎች የታተሙበት ወረቀት፤ እና፣  አንድ ወረቀት በውስጡ የታጨቁ ቃላት ለምን የፈለገ ልዩ አይሆኑም፣ በቀላሉ ሊቀዳደድ የሚችል ነው፡፡ መልካም ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን የሚወለደው እውነተኛው ሕገ መንግስት በዚያ ወረቀት ውስጥ አይደለም የሚገኘው - ለሕገ መንግሥት ሕገ መንግሥትነት መንስኤ በሆኑት መንፈሶች፣ ሀሳቦችና ፍልስፍናዎች ውስጥ እንጂ፡፡ እያልኩ ያለሁት ምንድን ነው፣ ለሕገ መንገስት እውነተኝነትና ተዓማኒነት፣ ሕገ መንግሥቱ በአእምሮህ፣ በልብህና በባሕሪህ ውስጥ መታተም አለበት ነው፡፡

ከሁሉም በላይ፣ የሕዝብን ደህንነት/ዋስትና ማስጠበቅ፣ ትርጉም ላለው የትኛውም የመንግስት መዋቀር ወይም የመንግስት አሰራር የተነሳሽነት ኃይል ምንጭነት በቀዳሚነት የሚቀመጥ ነው፣ መሆንም አለበት፡፡ ስለመልካም አስተዳደርና ስለዴሞክራሲ መጽናት፣ «ስለምን ለሥልጣን ትወዳደራለህ?» እና «ስለምን ሕዘቡ ይመርጥሀል?» ለሚሉት ሁለት ጥያቄች የሚሰጠው ምላሽ ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡ እርካታ ማጣትና ችግሮች፣ ምላሾቹ የተለያዩ በሆኑበት በየትም ስፍራና ቦታ ይነግሳሉ፡፡ የምትወዳደረው ራስህን ለማበልፀግ ከሆነና ሕዝቡ የመረጠህ ደግሞ የተሻለ ማሕበራዊ ግልጋሎት ታመጣለህ ብሎ በማሰብ ከሆነ፣ በእርግጠኝነት የተወሰነው የሕዝቡ/ማሕበረሰብ ክፍል መቆጣቱ/ቅር መሰኘቱ አይቀርም፡፡ ሁለት ጌቶችን በአንድ ጊዜ ማገልገል አይቻልህምና መራጮችህን ወይም የራስህን ጥቅሞች ማገልገል አለብህ፡፡ መሰረታዊ አለመግባባት በሌለበትና የፍላጎት መጣጣም ባለበት፣ ለመልካም አስተዳደር ወሳኝ መሰረት ጥለህል

ማለት ነው:: የመንግስት የፖለቲካ መሪ በመሆናችሁ፣ ለህዝቡ የመልካም አስተዳደር ቀዳሚ ምሳሌ መሆን አለባችሁ:: ሁሌ ሕዝብ ከአገሪቱ ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት ላይኖረው ይችላል:: ሆኖም ስራህን በአግባቡ ካከናወንክ፣ ከማህበረሰቡ ጋር የቅርብ ግንኘ ኙነት ይኖርሀል:: በመሆኑም፣ ግዴታህን ለመወጣት እስከታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ድረስ የሚሄድ የዴሞክራሲ ተምሳሌት ትሆናለህ፤ እንዲሁም ራስህ የዴሞክራሲ ጠባቂ ትሆናለህ::

ይህን ታላቅ ተግባር መወጣት ይቻልህ ዘንድ ለመንግስትህ፣ ለወረዳህ፣ ለዞንህ፣ ለመንደርህና ለማህበረሰብ ራዕይ ሊኖርህ ይገባል:: ማህበረሰብህን ለማሻሻል ወይም ለማገልገል ራዕይ፣ ብቃት፣ በቂ ጊዜ፣ ጉልበትና ተነሳሽነት ከሌለህ የሥራ ድርሻህን ለመለወጥ ብታጤን የተሸለ ነው:: ምናልባት ይህ ለአንተ የሚሆን አይደል ይሆናል:: እርግጥ ነው የፌዴራልና ክልላዊ መንግስታት ሁሉንም ነገሮች ለብቻቸው ማከናወን አይቻላቸውም:: ሆኖም፣ ለመረጠህ ሕዝብ መሰረታዊ ግልጋሎቶችን ለማቅረብ ከማሕበረሰብህ ጋር በአብሮነት መስራት ይጠበቅብሀል:: የሕዝብ ፍላጎቶች በምስጢር የተሸበቡ አይደሉም:: ስለመረጡህ የምትጨነቅ ከሆነ፣ ፍላጎታቸውንና ስጋታቸውን በቀላሉ ማገናዘብ ይቻልሀል::

*/ተስፋዬ ሀቢሶ፣በኡጋንዳና በደቡብ አፍሪካ የኢፌዲሪ አምባሳደር ነበሩ/*

# ሞቲቬሽን

# አንድ ተጨማሪ

በተሰማራንበት ማንኛውም ስራዎች ላይ አንድ ተጨማሪ ነገር እስኪ እናድርግ:: የሰራናቸው ስራዎች ላይ ሊሆን ይችላል ወይም የምንጀምራቸው ሊሆኑ ይችላሉ፣ ትንሽ ተጨማሪ ነገር እስኪ ጣል እናድርግባቸው:: ልክ አንድ የስዕል አርቲስት የሚሰራውን ስዕል እሱ እስከሚፈልገው ድረስ እስኪሆን ድረስ ስዕሉን እለት ተእለት፣ በየሰዓቱ እና በየደቂቃው እንደሚያሳምረው ሁሉ የምንሰራቸው ስራዎች ላይ ሁሉ እንደዚህ ዓይነት አቀራረብ ቢኖረን የነዛን ስራዎች እጅግ የተሻለ ውጤት እናያለንም፣ እናሳያለንም:: ይህ ማለት በሰዓሊው ዕርዳታ ስናየው መጀመያ ላይ የተሳለው ስዕል፣ እዛ ስዕል ላይ የተጨመረው ሁለተኛ እና ሶስተኛ ነገሮች ጥሩ አይደሉም ማለት አይደለም ግን ምርጥ የተባለውን የዛን ስዕል ውጤት የምናየው ያንን ስዕል ደግሞ ደጋግሞ በማሻሻል፣ በማሳመር እና በማስዋብ ነው:: ይህን ሲያደረግ በየጊዜው የሚወጣው የስዕሉ ውጤት እያማረበት እና ምርጥ እየሆነ ይሄዳል:: በተመሳሳይ መልኩ እየሰራን ያለውን ስራ አንድ ተጨማሪ ነገር እንጨምርለት እስኪ:: ምን አንድ ተጨማሪ ነገር ብናደርግ ስራውን የበለጠ እንሰራለን ወይም የስራውን የተሻለ ውጤት እናያለን? ምን አንድ ሌላ ተጨሪማ ነገር በናደርግ በፊት ከሰራነው የተሻለ እንሰራለን? ልክ አንድ ሁለት ሶስት

እያልን ቁጥር መቶ ላይ እንደምንደርሰው እና መቶ ቁጥር ላይ ከደረስን በኋላ ቁጥር አንደ ሺህ ላይ ለመድረስ ከፈለግን መቶ አንድ፣ መቶ ሁለት ብለን እንደምንቀጥለው ሁሉ ስራዎቻችን ላይ እንደቁጥሮቹ ወደ ፊት እንድንጓዝ አንድ ሁለት ማለት አለብን:: አንድ ተጨማሪ ነገር ምን እንስራ እዚህ ስራ ላይ፣ ከዛም አንደኛው የጨመርነው ስራ ላይ ምን ሁለተኛ ስራ እንጨምር እያልን ከሄድን ማንኛውም ስራዎች መሻሻል እድል ያገኛሉ:: እድልም ካገኙ ይሻሻሉ እናም ባሉበት አይቆሙም:: ግን ይንን ለማድረግ ሁልጊዜ አንድ ተጨማሪ ነገር ምን እናድርግ ብለን መጠየቀ አለብን፣ አንድ ተጨማሪ ነገር ብለን ካልጠየቅን ሁለተኛ ተጨማሪ ነገር ምን እናድርግ ብለን አንጠይቅም:: እንደዚህ ብለን እየጠየቅን ከሄድን ስሪዎች ባለቡት ሳይሻሻሉ የመቆም እድል አይኖራቸውም:: መሻሻል ይኖራል፣ ማደግ ይኖራል እናም ለራሳችንም ለስራዎቻችንም ማድረግ የምንችለውን ትልቅ ነገር እናደርጋለን::

አንድ ተጨማሪ ነገር ምን ላድርግ ብሎ ራስን መጠየቅ ስራን ለማሻሻል ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነገር ያገለግላል:: ለቤተሰቤ ትላንት ካሳየሁት ፍቅር ዛሬ ምን ተጨማሪ ፍቅር ሰጥቼያለሁ? ከስራ ባልደረቦቼ ጋር ትላንት ከነበረኝ ግንኙነት ዛሬ ያንን ግንኘ ኑነታችን ለማሻሻል ምን አዲስ ተጨማሪ ነገር አድርጌያለሁ? ዛሬ ለሰራተኞቼ ከማደርግላቸው በተጨማሪ ነገ ምን ላደርግ አስቤለሁ? ከጓደኞቼ ጋረር ትላንት ከነበረን ተወዳጅ ግንኙነት ዛሬ ምን ተጨማሪ ነገር እኔ ለማድረግ አስቤያለሁ? የመሳሰሉት:: ሁሉ ነገር ላይ እንደዚህ ብለን ከጠየቅን እና ካደረግን የበለጠ የተሻለ ነገር እናገኛለን:: ብዙ ፍቅር፣ የተሻለ ግንኙነት፣ የተሻሉ ስራዎች የመሳሰሉት ነገሮች ተጨማሪ ነገሮችን ሁሌም ቢሆነ በማድረግ ይገኛሉ:: መልካም ነገሮች ማብቂያ የላቸውምና እዚህ ላይ ይበቃናል፣ እዚህ ድረስ ነው የምንችለው አንበል:: ካልን የበለጠ ሊያምሩ፣ የበለጠ ሊሰሩና የበለጠ ሊደረጉ የሚችሉ ነገሮችን ሁለ እናጣለን::

በቀን ውሰጥ የምናደርጋቸው እያንዳንዱ ስራዎች ላይ አንድ አንድ ትንንሽ ነገሮች እንጨምርባቸው:: በዛ ቀን ውስጥ ልንሰራ ካሰብነው በላይ ተጨማሪ ነገር እንጣልበት:: በእርግጥ በቅድሚያ ለመስራት ያሰብነውን ማንኛውንም ነገር መስራት አለብን:: ከሰራነው በኋላ ግን ስራውን ብናጠናቅቀውም እንደገና እንመልከተው:: መስራት እስካለበት ደረጃ ድረስ ነው የተሰራው? ልናሻሽለው የምንችለው ምንም ነገር የለምን? ስራውን የተመረጠ ለማድረግ ተጨማሪ ማድርግ የምንችለው ምንም ነገር የለምን? እነዚህን ጥያቄዎች ራሳችን መመለስ ካቃተንና ምንም ልናሻሽለው የምንችለው ነገር ያለ መስሎ ካልታየን ሌሎች የፋራ ባልደረቦቻችን እንጠይቅ:: እኛ ያልታየን ነገር እነሱ ሊታያቸው ይችላል:: እነሱ ያልታያቸው ነገር ለእኛ ሊታን ይችላል:: እናም ሁሌም ቢሆን ልንጨምራቸው የምንችላቸውን ነገሮች በማሰብና በማድረግ አንድ ደረጃ ሁለት ደረጃ እያልን ወደፊት እንሂድ::